

"አሥራ አንድ ቤተሰቦቼ ከግንቦት
ሠባት ጋር ኤርትራ በረሃ ናቸው"

አንዱአለም አያሌው

በሃይማኖት ካባ
የዘረኝነት ደባ

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

ከህወሓት ጠርሙስ ውስጥ
ያመለጠው "ጂኒ" እና
የጠቅላይ ሚኒስትሩ እርምጃዎች

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 10 ሰኔ 2010 ዓ.ም ዋጋ 14.99



## "የድብቅ ፖለቲካ ካሁን በኋላ በቃ"

ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ

በተለየ ለግዮን

## "ለውጡን እንደግፍ፤ ዲሞክራሲን እናበራታታ"

ከሠላማዊ ሠልፉ አስተባባሪዎች ጋር የተደረገ ቆይታ

## "ህወሐቶች አማራንና ኦሮሞን የማጋጨት ፍላጐታቸው ተዘጋ"

አክቲቪስት ጃዋር መሐመድ (ከአሜሪካ)

ግዮን
ቅጽ 1 ቁጥር 10 ቅዳሜ ሰኔ 16 2010 ዓ.ም



**ቀጣይ ዕትም ቅዳሜ ሰኔ 23 ይጠብቁን!**




**ቁጥር 9 ዕትም**


# 14 "ሥርዓቱን ፍርክስክሱን ያወጣው ቄሮ ነው"

## "ጠ/ሚ ዐቢይ ጽፍረትና ፍጥነት ያለው ሰው ነው"

**አክቲቪስት ጃዋር መሐመድ (ከአሜሪካ)**

**በተለይ ለግዮን**

18 መሪዎች ፍቅርና በጎ ሕሊና ያስፈልጋቸዋል!!
ተረፈ ወርቁ

23 "አሥራ አንድ ቤተሰቦቼ ከግንቦት ሠባት ጋር ኤርትራ በረሃ ናቸው"
አንዱአለም አያሌው



2 "የድብቅ ፖለቲካ ካሁን በኋላ በቃ"

5 ከህወሓት ጠርሙስ ውስጥ ያመለጠው "ጂኒ" እና የጠቅላይ ሚኒስትሩ እርምጃዎች

8 <<ለውጡን እንደግፍ፤ ዲሞክራሲን እናበሬታታ>> ከሠላማዊ ሠልፉ አስተባባሪዎች ጋር የተደረገ ቆይታ

10 የብሔር ግጭቶች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል

11 ወደየትም የማያስሄደው የዘረኞችና የሌቦች ሴራ
ሁሴን ከድር

12 የአቶ መለስና የጠ/ሚ ዐቢይ የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ ንጽጽሮች
ታምራት መርጊያ

20 ወላይታዊ ኢትዮጵያዊነቴ፣ ክብር ለወገኔ ክብር ለሀገሬ
አካለወርቅ መንገሻ (ረ/ፕ)

22 የኢትዮጵያ ዕድሏ ያሳዝናል
ደረጀ መላኩ

26 በሃይማኖት ካባ የዘረኝነት ደባ
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

28 የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

# “የድብቅ ፖለቲካ ካሁን በኋላ በቃ”



ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ

## “ሚዲያዎች የህዝብ ድምጽ እንዲሆኑ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል”

## “በሃይማኖት ተቋማት ከፍተኛ ሌብነት አለ”

ሰኔ 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ፣ በደቡብ ክልል ስለተፈጠረው ግጭት ድርጊቱን አውግዘው መግለጫ መስጠታቸው የሚታወስ ነው፡፡ በማግስቱም ወደ ሞቃዲሾ በመሄድ ከሱማሊያ መንግሥት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ስምምነት ማድረጋቸውን በተመለከተ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ከአንድ ቀን በኋላም ሰኞ ዕለት በፓርላማ የሥራ ሪፖርት በማቅረብ ከአባላቱ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል፤ እኛም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተለያዩ ክስተቶችና ጉዳዮች ዙሪያ የተናገሯቸውን ንግግሮች ቀንጭበን አቅርበናል፡፡

### ስለፀረ ሽብር እና የይቅርታ ሕጉ አፈጻጸም

ሰዉ ጭንቅላቱ መቀየር አለበት፤ ለዘለዓለም እንደማይኖር አውቆ በሕግና በሕግ ብቻ መግዛት፣ ማስተዳደር፣ መቀየር መቻል አለበት፡፡... ልባችንን ሰፋ እናድርግ፤ አንዳንዶቹን [በወንጀል የተፈረደባቸውን] የምንፈታበት ምክንያት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያ ውጥረት የተመላ (tense-ful) በጥላቻ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ አካሔድ የዘር እልቂት ሊያመጣ እየሔደ ነው፡፡

ሁሉ በዘር ነው፡፡ ፖሊቲካ ብቻ አይደለም፤ ሃይማኖትም፡፡ አሜሪካ ያለው ሲኖዶስ እና እዚህ ያለው ሲኖዶስ ኦርቶዶክስ ብቻ አይደለም፤ ከኋላው ብሔር አለ፤ መቆም አለበት ይኼ፤ አይጠቅምም፡፡ አየነው፤ አየነው፤ ኪሳራ ነው፡፡

አሁን የሚያዋጣው ነገር፣ ብሔር ማግኘት የሚገባውን ክብር ካገኘ በኋላ እንደ ሀገር አብሮ ለመኖር ግን የማይቸገር መሆን አለበት፡፡ ሁለተኛው ሰላም በሰላም ብቻ ነው የሚገኘው፡፡ ሰላም በማሰር፣ በማሳደድ አይገኝም፤ ያብሰዋል ጉዳዩን፡፡

ይህ አገር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ ያገባኛል፤ የእኔ ነው፤ ይሆነኛል፤ ብሎ እንዲሳተፍ መፍቀድ ያስፈልጋል፡፡ መንገዱ ይለያይ ይሆናል እንጅ፣ ሁሉም አገሩን የሚወድ፣ የአገሩን ዕድገት የሚመኝ፣ ለአገር ታላቅነት አልማለሁ ብሎ ለአገሩ የሚሠራ መሆኑን ማመን አለብን፡፡ እኛ ብቻ አይደለንም የምንቆረቆረው ለኢትዮጵያ፤ ሁሉም ይቆረቆራል፡፡

ሲቆረቆር በስሕተት መንገድ እንዳይሔድ፤ በግጭት እንዳይሔድ፤ በጥላቻ እንዳይሔድ፣ ብሔርን ከብሔር በሚያጋጭ መንገድ እንዳይሔድ፤ ትላንት ተበድያለሁ፣ ነገም ስለምበደል አልፈልግም በሚል መንገድ እንዳይሔድ፤ የበሰለ (matured ያደረገ) የፖለቲካ ውይይት ያስፈልጋል ብሎ ማሰብ ጥሩ ነው የሚሆነው፡፡ አሁን የእኛ ድርሻ ሜዳውን ማስፋት ነው፤ ሁሉም እንዲወዳደር፤ ሁሉም ሐሳቡ እንዲደመጥ ማስፋት ነው፡፡

ኤርትራ ያላችሁ ሁሉ ወደ ሀገራችሁ ግቡ፤ እንደራደራለን፡፡ የግንቦት ሠባት፣ የኦነግ፣ የኦብነግ ሰዎች በይቅርታ እንገናኝ፤ የትጥቅ ትግል አሮጌ ፋሽን ነው፡፡ የቂም በቀል ፖለቲካ ይቁም፡፡ በሌሎች ሀገራት ውስጥ ያሉትን ለምነን እያስፈታን በሀገር ውስጥ ያሉ ፍትሕ ያጡ ወገኖች ለምን ተፈቱ ተብሎ ጽንፍ መያዝ ተገቢ አይደለም፡፡

ጃንሆይን አፍኖ መግደል መልካም እንዳልሆነ ከመንግሥቱ መማር አለብን፡፡ ቤተ መንግሥት የኮሎኔል መንግሥቱ መግረፊያ አለ፡፡ ይህ የጥላቻ ታሪክ ያብቃ፡፡ እኛ ደቡብ አፍሪካም ደቡብ ክልልም መታሰር የለብንም፡፡ ከወላይታ የመጣ ሕፃን እኩል በየትም ቦታ ማደግ፣ መኖር አለበት፡፡ ተዘግተው የነበሩ ድረ-ገጾች ተከፍተዋል፡፡ እንዳይጽፉ ተከልክለው የነበሩ ዓምደኞች በነጻነት እንዲጽፉ ለማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ሚዲያዎች የህዝብ ድምጽ እንዲሆኑ የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በቀጣይ የህዝብ ድምጽ እንዲሆኑም እንሠራለን፡፡

### ስለፀረ ሙስና ሕጉ አፈጻጸም

ሙስና የሚባለው ካንሰር ዋነኛ የጭቆና እና የዘረፋ መሣሪያ እየሆነ ነው፡፡ ሙስና አምስተኛ መንግሥት ነው የተባለበት ምክንያት፣ በተደራጀ መንገድ ያሻውን ነገር እጅን ጠምዝዞ ስለሚያስፈጽም ነው፡፡ ሰርቆ መብላት ብቻ አይደለም፤ ሰርቆ ከፍላጎቱ ዝንፍ ስትል አንቆ ወደ ፍላጎቱ ማምጣትን ጭምር እንደ መንግሥት መተግበር ስለሚችል ነው፡፡ እንደ እኛ ባላደገ አገር የኢኮኖሚ ውድቀት ብቻ ሳይሆን፣ መደለል የማይችሉ አቅም የሌላቸውን ድሆች በእጅጉ ይጎዳል፡፡ ፍላጎታቸው በሌሎች ፍላጎቶች የተዋጠና የተገዛ ይኾናል፡፡ ይህን አይቶ ምላሽ መስጠት ተገቢና አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የሙስና መንሥኤ መዋቅራዊ መሆኑን ማየት ተገቢ ነው፡፡ ላለፉት ዐሥር ዓመታት የሆኑ የሆኑ ሰዎች ስናስር ሙስናው ለምንድን ነው እየጨመረ የሔደው? እየቀነሰ አልመጣም፤ እየጨመረ፣ እየሰፋ ነው የሔደው፤ ዋናውን ምንጩን በሚደፈጥጥ አግባብና አቅም እየሔድን አይደለም ማለት ነው፡፡...

የፍትሕ ዕጦት፣ የፍትሕ ችግር፣ በገንዘብ ማሰር፣ በገንዘብ መፍታት የሚቻል ከሆነ ሙስና ይስፋፋል፡፡ ሙስና፥ በፍትሕ ሥርዐት፣ በግዥ፣ በገቢ፣ በፋይናንስ አስተዳደር ምን ያህል ትስስርና ጉድኝት እንዳለው ማየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ፥ ሙስና ሲባል ለሆነ ግሩፕ የመስጠት ዝንባሌም አደገኛ በሽታ ነው፡፡ መጠኑ ይስፋ ይብዛ እንጅ፣ ሌብነት ከጫፍ ጫፍ ባህል ሆኗል፡፡ ይህንም በሚያስተካክል አግባብ የሙስናን ጉዳይ አይቶ፣ ከመሠረቱ አጥንቶ መፍትሔ ማበጀት ይገባል፡፡ ያን ማድረግ የማንችል ከሆነ፣ ቅድም የፈራነው ጥላቻ፣ ቅድም የፈራነው ቁርሾ፣ ይሄም አጀንዳ ኾኖ ልክ እንደ ሃይማኖት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

በሃይማኖት ተቋማት ከፍተኛ ሌብነት አለ፤ ኦዲት አይደረጉም፤ በትምህርት ተቋማት ከፍተኛ ሌብነት አለ፤ ግሬድን ጨምሮ፡፡ እነዚህን ሁሉ በጥቅሉ ፈትተን የምናስተካክልበት መንገድ መከተል ያስፈልጋል፡፡

የመንግሥት ሓላፊዎች ደግሞ ተጨማሪ ሓላፊነት አለባቸው፡፡ በመንግሥት ሥልጣን የሕዝብን ሀብት መስረቅ ጸያፍ ወንጀል፣ ከወንጀልም በላይ አሳፋሪ ወንጀል ስለሆነ የመንግሥት ባለሥልጣናት መነገድና ሀብታም መኾን ከፈለጉ ቢሯቸውን እየለቀቁ መሔድ አለባቸው፡፡ ቢሮ ሆኖ፣ የመንግሥት አለቃም ነጋዴ ሀብታም መሆን አይቻልም at a time.

የፈታናቸውን ሰዎች መረጃ ካገኘን መልሰን ማሰራችን አይቀርም፡፡ ይቅርታ እንጂ ምህረት አላደረግንም፡፡ ሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ እንዲፈታ የሚፈልግ አለ፡፡ ይህ እይታ መንግሥት ሆኖ ካለማወቅ የሚመነጭ ችግር ነው፡፡ ይህን ለማድረግ አሠራሮችን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡ የሚፈቱት ሰዎች ጋር በተያያዘ በደም ማየት ተገቢ አይደለም፡፡ በሌሎች ሀገራት ውስጥ ያሉትን ለምነን እያስፈታን በሀገር ውስጥ ያሉ ፍትሕ ያጡ ወገኖች ለምን ተፈቱ ተብሎ ጽንፍ መያዝ ተገቢ አይደለም፡፡

ህዝቡን በዚህ አጋጣሚ እለምናለሁ፤ የትግራይ ህዝብ ለሰላም ዋጋ ከፍሏል፡፡ ኦሮሚያ፣ ደቡብ እና አማራ ያላችሁ የትግራይን ህዝብ ተረዱት፡፡ በስሙ በጥቂቶች ተነግዶበታል፡፡ ብዙኃኑን የሚያጥላላ ፖለቲካ የትም አያደርስም፡፡ ህወሓትን ከትግራይ ህዝብ ለዩት፡፡ ህወሓት ማለት የትግራይ ህዝብ ማለት አይደለም፤ ጥላቻ እና ቂም ይብቃ፡፡ የትግራይ ህዝብ ብዙ የመልካም አስተዳደር ችግር አለበት፡፡ ውሃ መጠጣት እንኳን የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

ሕገ መንግሥቱ ጨለማ ቤት አስቀምጣችሁ ግረፉ፤ አሰቃዩ አይልም፡፡ አሸባሪ እኛ ነን፡፡ ኢህአዴግ ይቅርታ ጠይቋል፤ ህዝቡም ይቅር ብሎናል፤ ህዝቡ እኛን ማሰር ነበረት፡፡ የግንቦት ሰባት፣ የኦነግ፣ የኦብነግ ሰዎች በይቅርታ እንገናኝ፡፡ የትጥቅ ትግል አሮጌ ፋሽን ነው፡፡ የቂም በቀል ፖለቲካ ይቁም፡፡

### ስለኤርትራና ኢትዮጵያ

ደቡብ እና ሰሜን ኮርያ አንድ እየሆኑ ነው፡፡ ኤርትራ እና ኢትዮጵያም መቀራረብ አለባቸው፡፡ ለብሔራዊ ጥቅም እንተጋለን፡፡ የኤርትራ ህዝብ ወንድማችን ነው፡፡ ህዝብ ጠይቋል፡፡ ስለዚህ የተመለሰው የህዝብ ጥያቄ ነው፡፡ የድብቅ ፖለቲካ ካሁን በኋላ በቃ፡፡ የሥራ አስፈጻሚው ውሳኔ ለህዝባችን ቶሎ መሰማት አለበት፡፡

ከህዝባችን የሚደበቅ ነገር የለም፡፡ የወንድሜ ልጅ ባድመ ላይ ሞቷል፡፡፡ ዋጋ ተከፍሏል፡፡ መረብ ምላሽ ባረንቱ ላይም ሞተናል፡፡ የመሞት ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ ሀብት አፍስሰናል፡፡ አሁን ወደ ሰላም እንመጣለን፡፡ የሰላም ዋጋን እንከፍላለን፡፡

የአማራ እና የትግራይን፣ የኦሮሞ እና የደቡብ ወሰን ጉዳዮችን በዘላቂነት እንመልሳለን በኢትዮጵያ እና በኤርትራ ለ18 ዓመት ዓመታት ነግሶ የቆየውን ሞት አልባ ጦርነት ለማቆም የመፍትሔ እርምጃ እየተወሰደ ነው፡፡ የሰላም ጥሪም ለኤርትራ ቀርቧል፡፡ ለሦስት ዓመት ሰፍኖ የቆየው አለመረጋጋት መሻሻል አሳይቷል፡፡ አንዳንድ ቡድኖች ለውጡን አልደገፉም፡፡ ይሁን እንጂ መንግሥት ለሀገር አንድነት የሚሠራ ይሆናል፡፡ ሰሚ ያጣ የመሰለው ህዝብ ሰሚ ይፈልጋል፡፡ በቀጣይ በትኩረት የምንሰራ ይሆናል፡፡ አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት እንሰራለን፡፡

### ስለ የመንግሥትን ተቋማት በአክሲዮን ስለመሸጥ

በአብሮነታችን ለቀጣዩ ትውልድ ፍቅርን እናወርሳለን:: ሰው ሲፈታ አይናችን የሚቀላ በቀለኞች አንሁን:: ኢትዮጵያ በቂ ሀገር ናት:: ጠንካራ ተቋም እናቋቁማለን:: የአፍሪካ መሪዎች ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካ አየር መንገድ አንድ እንዲሆን ተፈርሟል:: የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ የብዙ ሀገራትን ገዝቷል:: ስለዚህ መንግሥት ብቻውን መያዝ የለበትም:: የግል ባለሐብቱም መጠቀም አለበት:: ይህ ለተጨማሪ ትርፍ ይጠቅመናል:: ሥራችንንም ያቀላጥፍልናል::

ከመንግሥት ወደ ግል ዝውውር ሲሠራ በጥናት ላይ ተመስርቶ ነው:: የተሸጡ የመንግሥት ሐብቶች ከዚህ ቀደም ያለውድድር የነበሩ ስለሆነ አላደጉም:: አሁን ሁሉም ሐብቶች በውድድር ይሆናሉ:: የቴሌኮም ገቢ ከውጭ ገቢ አላደገም:: የሐብት ብክነትም አለ:: ኔትወርክም ጥራት የለውም:: 12 ሚሊየን ህዝብ ያላት ሶማሊያ እንኳን ትበልጠናለች:: ስለዚህ በውድድር ለግሉ ዘርፍ እንሰጣለን:: በአንዴ ሳይሆን በጥናት ተመስርተን የቴሌኮምዩኒኬሽንን ጉዳይ እልባት እንሰጣለን::

### ስለ ደቡብ ክልል ግጭት

የአፍሪካ መሪዎች አፍሪካውያን ያለቪዛ በነጻ እንዲንቀሳቀሱ ሊያደርጉ ነው:: አማራ በኦሮሞ፣ ትግራይ በአማራ ክልል በነጻ መንቀሳቀስ ካልቻለ ስለ አፍሪካ አንድነት ለማውራት አንችልም:: ድንበር እና ወሰን ማምታታት አለ:: አማራ እና ኦሮሞ፣ አማራ እና ትግራይ ድንበር የላቸውም፤ ወሰን ነው:: ድንበራችን ከኬንያ ጋር ነው::፡ አንድ አማራ ነቀምት፣ አንድ ኦሮሞ ጅጂጋ ላይ መኖር ካልቻለ ከባድ ነው:: የትም ቦታ የመኖር መብት አለን:: የፌዴራሊዝም ሥርዓቱ ትልልቅ ችግርን እንጂ ትንንሽ ችግሮችን ማቆም አይችልም:: በአመራርነት ይስተካከላል::

### ከሞቃዲሾ መልስ ከተናገሩት

ሶማሊያ እና ኢትዮጵያ ወደ አንድ ሀገርነት ልንመጣ ነው:: ትልቅ ሀገር ለመሆን በጋራ እንደመራለን:: ትንንሽ ደሀ ሀገር መሆን የለብንም:: የአልጀርስ ስምምነት በፓርላማው ቀድሞ የጸደቀ ነው:: ለአፍሪካ መሪዎችም ደርሷል:: ዓለምም ያውቀዋል:: መሆን የማይገባውን ጦርነት አድርገናል:: አስከፊ ጦርነት ነው:: ጦርነት እያስታመምን አንኖርም:: የሎጂስቲክስ ሥራችን ኋላቀር ነው:: ከዓለም 160ኛ ነን:: መርከቦቻችን ቆመው ነው የሚውሉት:: ጎረቤት ሀገራት ይበልጡናል:: ወደ ኋላ መቅረት የለበትም:: የሎጂስቲክስ ዘርፉ ካልተስተካከለ ፈጣን ኢኮኖሚን መሸከም አንችልም:: የውጭ ምንዛሬን ለማስተካከልም የሎጂስቲክስ ዘርፉ ለግል ባለሐብቱ ይሠጣል::

በደቡብ ክልል ስለተፈጠረው ግጭት ከተናገሩት

በየአካባቢው የተፈጠረው ግጭት በምንም መሥፈርት ህብረተሰቡን የማይወክልና የተጀመረው የለውጥ ሂደት ባልተዋጠላቸው አካላት ጠንሳሽነት እየተመራ እንደሆነ ከወዲሁ መገንዘብ ይቻላል::

በመንግሥት የለውጥ መሪነት ከቀውስ ለመውጣት የተጀመረው ጥረት እየሰመረ፣ ነፍጥ አንስተው ሲፋለሙ የነበሩ ወገኖቻችን ሳይቀሩ የሰላም ጥሪ ተቀብለው ለአገር ግንባታ መሰለፍ በጀመሩበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት የግል ጥቅምን ታሳቢ አድርገው ህዝብን ከህዝብ ለማጋጨት የሚያደርጉትን ሩጫ መግታት ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ወቅታዊ ተግባር ነው::

# ቴዲ አፍሮ ጠ/ሚ ዐቢይን መደገፍ አስፈላጊ ነው አለ

ለሀገር “ፍቅርና አንድነት” ወሳኝ እንደሆነ ሁሌም በይፋ የሚናገረውና በጥበብ ስራዎቹ ውስጥ የህዝብን ስሜት ትርጉም ባለው መንገድ በመግለጽ የሚታወቀው ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ለጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሕብረተሰቡ ድጋፍ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ገልጿል።

በአሁኑ ሠዐት በስራ ምክንያት አሜሪካን የሚገኘው ቴዲ አፍሮ ለሀያ ሰባት ዓመታት ኢትዮጵያዊነትን በማፈንና ብሔራዊ ስሜትን በማደብዘዝ ላይ ከነበረው ሥርዓት ለመላቀቅ የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አካሄድ ወሳኝ እንደሆነ ገልፆ ቅዳሜ ስለሚደረገው ሠልፍ ተከታዩን መልዕክት አስተላልፏል።

“ለተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች በቅድሚያ የከበረ ሠላምታዬን እያቀረብኩኝ ላለፉት 27 ዓመታት ኢትዮጵያዊነትን በማፈንና ብሄራዊ ስሜትን በማደብዘዝ አገራችንን ለአደጋ ከዳረገው ሥርዓት ለመላቀቅና በምትኩ አንድነትን፣ መተባበርን እና ፍትህን ለማስፈን ከምንም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ለማዳን በተለያየ አቅጣጫ ብዙ እንቅስቃሴዎች በሚካሄድበት በአሁኑ ወቅት፦

በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ኢትዮጵያዊነትን እና ይቅር መባባልን ይዘው ብቅ ላሉት



አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድና ባልደረቦቻቸው አጭር በሚባል የሥልጣን ቆይታቸው ለወሰዷቸው በጎ እርምጃዎች እና ላሳዩን ኢትዮጵያዊ አለኝታነት አጋርነትን ማሳየት እና ከጎናቸው መቆም ጊዜው የሚጠይቀው አስፈላጊ ተግባር መሆኑን ስገልፅ በሚደረጉት የድጋፍ እንቅስቃሴዎች ላይ በሥራ አጋጣሚ በቦታው ባልገኝም በመንፈስ አብሬያችሁ መሆኔን ሳረጋግጥ በታላቅ ኢትዮጵያዊ ስሜት ነው።”

ድል ለኢትዮጵያዊነት<br>
ፍቅር ያሸንፋል<br>
ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)

# የሙስሊም መፍትሔ አስፈላጊ ኮሚቴ መግለጫ አወጣ

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሙስሊሙን ጥያቄ ለመመለስ ዝግጁ መሆናቸውን በማረጋገጣቸው የምስጋና መግለጫ አውጥቷል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የዒድ አልፈጥርን በዐል ምክንያት በማድረግ ለህዝበ ሙስሊሙ ያቀረቡትን ጥያቄ ተከትሎ ለጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት ደብዳቤ ያስገቡት የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ዘላቂና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የህዝበ ሙስሊሙ መብት እንዲከበር ለመነጋገር እየተጠባበቁ መሆናቸውን በመግለጫቸው አስታውቀዋል።

ካለፉት ሁለት ወራት ወዲህ በሀገሪቱ እየተስተዋለ ያለው የለውጥ መንፈስና ተስፋ ሊደነቅ እንደሚገባው ያተተው መግለጫው የሕዝብ ጥያቄና ጉጉት በአፍራሽ ኃይሎች እንዳይደናቀፍ በጥፋት መንገድ ለመሰለፍ አሰፍስፈው የሚጠብቁ የጥፋት ቡድኖችን ከእንቅስቃሴያቸው ለመግታት ዘወትር ከመላው ሕዝብ ጋር በንቃት እንደሚሰሩም ጠቁመዋል።

# ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ ልዑካን ቡድን ወደ አዲስ አበባ ሊልኩ ነው

የኤርትራው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ዘለቄታዊና ጠንካራ ግንኙነት ለመመስረት የልዑካን ቡድን ወደ አዲስ አበባ እንደሚልኩ ገልፀዋል። የሀገሪቱ የሰማዕታት ቀን በዐል ላይ ባደረጉት ንግግር የሁለቱ ህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነትና እድገት ላይ ለመስራት በሀገራቸው በኩል ጽኑ ፍላጎት እንዳለ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያና ኤርትራ ያካሄዱት ጦርነት ከፍተኛ መስዋዕትነት ያስከፈለ እንደነበር ያስታወሱት ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሠዐት በለውጥ የሽግግር መድረክ ላይ እንደምትገኝ ጠቁመው በወቅቱ እየተነሱ ያሉ ሃሳቦችም ተገቢውን ትኩረት የሚጠይቁ በመሆናቸው ልዑካን ቡድናቸውን ወደ ኢትጵያ እንደሚልኩ አረጋግጠዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በፓርላማ ባደረጉት ንግግር ከኤርትራ ጋር ሰላም ለማውረድ እንደሚፈልጉ ደጋግመው ማስታወቃቸው አይዘነጋም።

ርዕስ አንቀጽ

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድን መደገፍ ኢትዮጵያዊነት ነው !

ባለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት የድርጅት ስሜት እንጂ የሀገር ፍቅር የተጠናወታቸው መሪዎችን ለማየት አልታደልንም ነበር። ህወሓት/ኢህአዴግ መላ ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ማግስት ተግቶ የሠራበት "ኢትዮጵያዊነትን የመሸርሸር" ተግባር ወደ ብሔር ክፍፍልና ጎጠኝነት አድጎ ሀገሪቷ የነበራት ግርማ ሞገስ ሙሉ በሙሉ ባይናድና የአንድነት ስሜቱ በብዙኃኑ ሕብረተሰብ ጨርሶ ባይጠፋም በእነዚህ ዓመታት ግልጽ በሆነ መልኩ ኢትዮጵያዊነት በመሪዎች ተረስቶ ሰንብቷል።
የሥርዓቱ ግፍ የተሞላበት አገዛዝ፣ በደልና ጭቆና ገፍቷቸው አደባባይ የወጡ ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ትግል ውስጥ ብቅ ያሉት አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ግን ከተመረጡበት ጊዜ አንሥቶ ለሀገርና ለሕዝብ ያላቸውን ፍቅር በግልጽ አሳይተዋል። አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ የተወለዱትና ያደጉት ኢህአዴግ ጉያ ውስጥ እስኪመስል ድረስ ያን ሁሉ ዓመታት ስለሀገር ከማውራት ይልቅ ስለ ድርጅታቸው ትግልና ህልውና ብቻ ያለመታከት ሲለፈልፉ ቆይተዋል።

ለውጥ ሊመጣ የሚችለው በአንድነት፣ በፍቅርና በይቅርታ መሆኑን በተግባር ያረጋገጡት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ በተመረጡ ማግስት በአምባገነኑ የደህንነት መ/ቤት እያፈነ ለእስር የዳረጋቸውን የኮማንድ ፖስት እስረኞችን ጨምሮ ለዓመታት ያለአግባብ በማረሚያ ቤቶች ሲጉላሉ የነበሩ ብዙ የፖለቲካ እስረኞችን ፈትተዋል፡ ፡ ከዘህ ባሻገር ለዘለቄታው ጠቃሚ በሆኑ መልኩ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት እንደሚሠሩም አረጋግጠዋል።

ይህን መሰሉ የጠ/ሚኒስትሩ የሀገር ፍቅር ስሜት ያልተዋጠላቸው የህወሓት ሰዎች ከጅምሩ የእኚህን ታላቅ መሪ እንቅስቃሴ ለመገደብና አቅጣጫ ለማሳት ብርቱ ትግል ጀምረዋል። ኢትዮጵያን እንደልብ ሲዘርፏት የከረሙት ወገኖች "ጥቅማችን ተጓደለ" በማለት ያዙኝ ልቀቁኝ እያሉ ነው። ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጉዳይ መፍትሔ እንዲያመጣ ከኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ጋር ባደረጉት ውይይት እና ውሳኔ ላይ ግልጽ የሆነ ክህደት በህወሓት ሰዎች ተፈጽሞባቸዋል። በጉባኤው ላይ ጉዳዩን አብረው ያነሡትና የተነጋገሩበት እነዚህ ጥቂት የህወሓት ሰዎች በሌላ መንገድ በመጓዝ ጠ/ሚኒስትሩን ከትግራይና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለማጣላት ጥረት አድርገዋል። እነዚህ ሰዎች እንደ ጣዖት ሲያመልኳቸው የኖሩት ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር የኢትዮ ኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ አልጀርስ ላይ ከ16 ዓመት በፊት ተፈራርመው ሲመጡ አሜን ብለው ተቀብለው ነበር። ቀድሞ ላለቀና በራሳቸው ሰው ለተፈጸመ ስምምነት ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድን ተጠያቂ ለማድረግ የሚኳትኑት ሩጫ የጥፋት መልእክተኞች መሆናቸውን ያረጋግጣል።

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ከተመረጡበት ዕለት አንስቶ ስለአንድነትና ፍቅር ሰብከውናል። በባዕድ ሀገር የታሰሩት ዜጎቻችንን ወደ እናት ምድራቸው መልሰውልናል። በባህር ማዶ ቆይታቸው ኢትዮጵያውያንን ከማስፈታት ባሻገር ያለብንን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ሊቀርፍ በሚችል መልኩ ከዱባይ የ1 ቢሊዮን ዶላር እርዳታ አስገኝተዋል። የዱባይ ባለሀብቶች 2 ቢሊዮን ዶላር በሚያወጣ ኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ ማረጋገጫ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትራችን አሁንም ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። መዝረፍ የለመዱ የኢህአዴግ ሰዎች በእርዳታ የተገኘውን ዶላር እንዳያባክኑ አሠራሩ በእሳቸው ቀጥታ ዕይታ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት ደግመን ደጋግመን እንናገራለን። በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን መሰል ታላቅ ሥራ የሠሩትን ጠቅላይ ሚኒስትሩን መደገፍና ማድነቅ የዜግነት ግዴታችንም ነው፤ በተሳሳተ መንገድ እየሄዱ ያሉትን የጥፋት ኃይሎችም እውነታውን በግልጽ ካስተዋሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩን መደገፍ፤ መሸነፍ አለመሆኑን ይረዱታል ብለን እናምናለን። በክፋት መንገድ ከመሄድ ይልቅ አብሮ መሥራት ለሀገር ይበጃል። አምባገነንነትና የአንድ ብሔር የበላይነት ወደተስተዋለበት ወደኋለኛው አስከፊ ዘመን መመለስ ከዚህ በኋላ ቅዥት ብቻ ይሆናል። በመሆኑም ቅዳሜ፣ ሰኔ 16 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የሚካሄደውና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመደገፍ መሰረት ያደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ሙሉ በሙሉ እንደግፋለን። ርቆን የነበረውን የአንድነት መንፈስ እንደ አዲስ የገነቡልንን፣ አፈር ልሶ የተነሣውን ኢትዮጵያዊነት የመለሱልንን፣ በድፍረት የሀገሪቱ የፀጥታ ተቋማት ብሎም የበላይ አመራሩ ሕዝብን ሲያሸብር እንደነበር በአደባባይ የመሰከሩልንን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድን መደገፍ በትክክልም ኢትዮጵያዊነት ነው።


ግዮን መጽሔት
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየ 15 ቀኑ ለኅትመት**
**የምትበቃ መጽሔት**

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

ዋና አዘጋጅ
ፍቅር ሠይድ
አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር 314

አዘጋጆች
ሮቤል ምትኩ
ብሩክ መኮንን

አምደኞች
አበባው አያሌው
ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ
ተረፈ ወርቁ
መስፍን ጌታቸው
ሁሴን ከድር
በህይሉ ገ/እግዚአብሔር
ሠሎሞን ለማ

ክርኤቲቭ ዲዛይን
ሀብታሙ መኮንን

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 951693
ኢ-ሜይል፡
Gihon2010meg@gmail.com
enqu2013@ gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu

አታሚ
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤
አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10
የቤ.ቁ. 066/ሀ



ጠ/ሚ ዐቢይ አሕመድ

# ከህወሐት ጠርሙስ ውስጥ ያመለጠው “ጂኒ” እና የጠቅላይ ሚኒስትሩ እርምጃዎች

የዘመናዊው የአረብ ስነ ጽሑፍ መዝገበ ቃላት እንደሚያስረዳው ጂኒ የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም “ጀንነ” ማለትም ‘ተሰወረ፣ ተደበቀ’ ከሚል ግስ የመጣ ሲሆን “ስውር፣ የማይታይ፣ ድብቅ” የሚል ፍቺ አለው። ጂኒ ነጠላ ቃል ሲሆን ሲበዛ “ጂን” ይሆናል።

ጂኒ የሚለውን የአረብኛ ቃል በተለምዷዊ ፍቺ ሰይጣን ወይም ጋኔን ለሚለው ቃል ወኪል አድርገው የሚጠቀሙ ብዙዎች ናቸው። የእስልምና አስተምህሮ ግን ጂንን በተመለከተ ይህን ይላል። “ጂን በሥጋ የማይታይና በመንፈስ የሚኖር አካል ነው። ልክ የሰዎች ዓለም፤ ማህበረሰብ እንዳለ ሁሉ የጂኒዎች ዓለምና ማህበረሰብም አለ። ጂንና የሰው ልጅ አንድ ምድር ላይ ቢኖሩም ሰው እነሱን፣ እነሱም ሰውን ማየት ሳይችሉ ነገር ግን አብረው ይኖራሉ። አላህ በቁርዐኑ "ጂኒንም ሆነ የሰውን ልጅ የፈጠርኩት ለእኔ እንዲገዙልኝ እንጂ ለሌላ ዓላማ አይደለም" እንዳለው ልክ እንደሰው ፈጣሪን የሚፈሩ፣ ትዕዛዛትን የሚያከብሩ፣ ከሰውም ሆነ እርስ በርሳቸው ከመጠቃቃት የምፅአት ቀንን ማስጠንቀቂያ ፈርተው ከመጥፎ ድርጊታቸው ታቅበው የሚኖሩ ጂኒዎች አሉ። በተቃራኒው ደግሞ አመፀኞችና ለፈጣሪ ትዕዛዝ ያላደሩ፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ከሰው ጋርም ይሁን እርስ በርሳቸው የሚጠቃቁ አሉ። ጂኒ ከሞተ በኋላ ልክ እንደሰው በጽድቅና ኩነኔው ልክ የሚፀድቅና የሚቀጣ ነው።

አረቢያን ናይት ተብሎ በሚታወቀው የአረቦች ተረት መጽሐፍ ስለጂኒዎች ብዙ የተጻፈ ሲሆን በአረቦች አፈ ታሪክ እንደሚነገረው ደግሞ ጠርሙስ ውስጥ እንዲገባ ተደርጎ የተዘጋበትና ወደባህር ተጥሎ ለዘለዓለም ከዚያ እንዳይወጣ የተፈረደበት ጂኒ አለ። ይህ ጂኒ ►

መልካምም መጥፎም የማድረግ ከፍተኛ ኃይል ያለው ነው ተብሎም ይታመናል፡፡ በዚህ ሳቢያ ያለበት ድረስ መጥተው ለሚጠይቁት ሁሉ የሚፈልጉትን ሁሉ ያደርግላቸዋል ተብሎ ይነገራል፡፡ ነገር ግን ጂኒው አምልጦ አንዴ ከጠርሙሱ ከወጣ በኋላ በየትኛውም ኃይል መልሶ ወደጠርሙሱ ማስገባትና ማሰር ፈጽሞ አይቻልም፡፡ ስለሆነም ይህን ኃይሉን የሚፈሩና ካመለጠ ጥፋት ያስከትላል ብለው የሚሰጉ ከጠርሙሱ እንዳይወጣ ይጠብቃሉ፡፡

## የጠርሙሱ ጂኒ እንደ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ማንጸሪያ

የኛኑ መለስ ዜናዊን ጨምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች፣ በንግግሮቻቸው ውስጥ በተለያየ አግባብ ቢሆንም "ስለጠርሙሱ ጂኒ" ሲያነሱ ተደምጠዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ መንግሥታትና ፓርቲዎች የማይፈልጓቸውን ሐሳቦች፣ የሚፈሯቸውን እንቅስቃሴዎች ህዝብ ጋር ቢደርሱ የሚያመጡትን በጎም ይሁን አሉታዊ ለውጥ ከወዲሁ በመገመት እንዳይባዛና እንዳይሰፉ ከወዲሁ ያፍናሉ፣ ያግዳሉ፣ ወይም ጠቅልለው በማሰር እንደጂኒው ወደማይሰሙበትና ወደማይታዩበት ጥልቅ ውስጥ በመጨመር እንዳያመልጥ በንቃት ይጠብቃሉ፡፡

ይህ ሐሳብ ወይም እንቅስቃሴ ከታሰረበት አፈትልኮ የወጣ ቀን ሊመልሱት እንደማይቻላቸውና [አሳሪዎቹ እነርሱ ስለሆኑም] ህልውናቸው እንደሚያከትም ስለሚገነዘቡ ማንኛውንም የሕግ፣ የፖለቲካ ወይም የኃይል አማራጭ በሙሉ ይጠቀማሉ፡፡

በእኛ ሀገርም ዘንድሮ የሆነው ይህ ነው፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ ባለፉት 27 ዓመታት የፊጥኝ አስሮ ወደጥልቁ የወረወረው የሐሳብ ነጻነት ጂኒ፣ የአንድነት ጂኒ፣ የይቅር ባይነት ጂኒ፣ የፍቅር ጂኒ፣ የሀገራዊ መግባባት ጂኒ፣ የመደማመጥ ጂኒ፣ የመተማመን ጂኒ፣ የጭቆና ተቃውሞ ጂኒ፣ የሰላም ፍላጎት ጂኒ፣ የእኩልነት ጂኒ፣ የመደመጥ ጥያቄ ጂኒ …ይህ ሁሉ ከጠርሙሱ ውስጥ ባልተጠበቀ ወቅትና ባልተገመተ ፍጥነት አምልጦ ወጥቷል፡፡

የ17 ዓመቱን ደርግ በጠመንጃ ጥሎ ሥልጣን የያዘው የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ለ27 ዓመታት ሲከተለው በኖረው የተሳሳተ አመራር እና ፖሊሲ የሥልጣን ባለቤት ነህ የተባለውና የዚህችን ሀገር ዕጣ ፈንታ መወሰን የሚችለው ህዝብ በብርቱ ተበድሏል፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ በቋንቋ ድንበር፣ በብሔር ፌዴራሊዝም የከፋፈለው ህዝብ፣ እንደህዝብ አንድ ሆኖ መቆም ተስኖት ልዩነቱን በጸብና በጥል ተቋስሏል፡፡ በተግባር አንድ ሀገር የሚባል ነገር ደብዝዞ ሁሉም ስለየራሱ ክልል የሚጨነቅ ሆኗል፡፡ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ ጠፍቶ የብሔር ዛር ሰፍኗል፡፡ ኢትዮጵያ በመሳፍንት አገዛዝ ዘመን እንኳን ባልታየባት የህዝብ ለህዝብ ግጭት ውስጥ ገብታለች፡፡

ህዝብ ያየውን ስለተናገረ ታስሯል፣ ስለተቃወመ ተገድሏል፣ ስለጻፈ ተንገላትቷል፣ ሀገሬ ብሎ ስለተጣራ ምላሱ ተቆልፏል፣ አማራጭ ፓርቲ ስለደገፈ ጣቱ ተቆርጧል፣ አማራጭ ሃሳብ ስላቀረበ በጨለማ ቤት ተዘግቶበታል፡፡ 27 ዓመት በዚህ መልክ በስህተት ፖለቲካና በተሳሳቱ ባለሥልጣናት ሲመራ የኖረው ህዝብ በዴሞክራሲ ጭንብል ጠመንጃ በነገሠባት ሀገሩ ላይ ታላቅ ህዝባዊ ቁጣ አቀጣጥሏል፡፡ መልካም ነገሮች ታስረው የከፉ ስህተቶች ጎልተው በመውጣታቸው እነዚያን የታሰሩ መብቶች ለማስመለስ ከዳር ዳር ህዝባዊ አመጽ ተቀስቅሷል፡፡

ታላቁ የፈረንሳይ የስነ ጽሑፍ ሰው ቪክቶር ሁጎ "ወራሪ ጠላትን መቋቋም ይቻል ይሆናል፣ ጊዜው የደረሰ ሀሳብን ግን በፍጹም መቋቋም አይቻልም" እንዳለው በኢትዮጵያ ለ27 ዓመታት ታፍኖ ሲብላላ የኖረው የህዝብ ጥያቄ ጊዜው ደርሶ ነበርና ቁጣ ሆኖ ፈንድቷል፡፡

ህወሓት/ኢህአዴግ በበኩሉ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ በአግአዚ ጥይት፣ በጸረ ሽብር ሕግ ያመለጠውን ጂኒ ወደጠርሙሱ ሊመልስ ብዙ ቢታገልም አልተሳካለትም፡፡ ይህ ፓርቲ ከመፈራረስ ለመትረፍ የነበረው የመጨረሻ አማራጭ ራሱን ቁጭ ብሎ መፈተሽ እና የሠራውን ስህተት መመርመር ነበርና ይህንኑ አደረገ፡፡

## የኢህአዴግን 'ሜሎዲ' በአዳዲስ 'ኖታዎች'

ህዝብ ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ በህወሓት የበላይነት ሲመራ የሚያውቀው ግንባር ባልተጠበቀ መንገድ የአባል ፓርቲዎች ድምጽ ሲሰማበት መታዘብ ቻለ፡፡ የራሱ የኢህአዴግን የኖረ 'ሜሎዲ' ቀይረው በአዳዲስ 'ኖታዎች' መጫወት የቻሉ ድምጾች ተፈጠሩ፡፡ የውስጥና የውጭ ግፊት ሰቅዞ የያዘው ህወሓት/ኢህአዴግ እንደፊኛ ከመፈንዳቱ በፊት መስመሩን ለማስተካከል ከ17 ቀናት በላይ የፈጀ "ጥልቅ ተሐድሶ" ውስጥ ተቀምጦ በተመለሰ ጊዜ ደግሞ ታሪክ መልኩን የቀየረ መሰለ፡፡ ያኔ ከራሱ ከኢህአዴግ ውስጥ ከየትኛውም አቅጣጫ ያልተጠበቁ፣ በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግምት ውስጥ ያልነበሩ፣ የህዝብ ድምጽ መስማት የቻሉ፣ የጊዜው ጥያቄ የተገለጠላቸው የለውጥ አርአያዎች ጎልተው ብቅ አሉ፡፡ ግዑዙን የ27 ዓመት ገዢ ፓርቲ ፊት በሌላ መልክ የቀየሩ በራሱ በኢህአዴግ መሰላል ላይ የተሻገሩና ከህዝብ የተቀላቀሉ መሪዎች ተከሰቱ፡፡ ዶክተር ዐቢይ አህመድ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆኑበት ዕለት ጀምሮ ህወሓት/ኢህአዴግ ጠፍንጎ አስሮ "የለውጥ ሐዋርያት በማይደርሱበት ቦታ" ያኖረውን ጂኒ ከጠርሙሱ ፈትተው ለቀቁት፡፡ እነሆ መንፈሱ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ውስጥ ገብቶ መስገሩን ቀጥሏል፡፡

## ያመለጠው 'ጂኒ' አሳሪዎቹን ሲያሳፍር

ህወሓት ግና ከጅምሩ የህዝቡን ድምጽ በማስተጋባት ወደሥልጣነ መንበሩ እየተጠጉ የነበሩትን የኦህዴዶቹን የአቶ ለማንና የዶ/ር ዐቢይን ጉዞ በማደናቀፍ ወደጠርሙሱ ለመመለስ [ራሳቸው ዶክተር ዐቢይ እንዳሉት የእስር ትዕዛዝ አውጥቶ ለማሰር] ጥረት አድርጎ የነበረ ቢሆንም ጊዜና ዕድል ፊታቸውን ስላዞሩበት ግን የሆነውን ሁሉ በዓይኑ ቆሞ ለማየት ችሏል፡፡

በ17 ቀናቱ የሥራ አስፈጻሚው ስብሰባ የፖለቲካ እስረኞችን ለመፍታት ፓርቲው ያሳለፈው ውሳኔ መፈጸም ሲጀምር በቁጥቁጥ የነበረ ቢሆንም ዶክተር ዐቢይ በብዙ ፍትጊያና ትግል ውስጥ አልፈው ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆኑ በኋላ ህወሓት "በመቃብሬ ላይ" ያላቸውንም አንዳርጋቸው ጽጌንና ሌሎች የእድሜ ይፍታህና ሞት ፍርደኛ ጭምር አካትተው ከ1 ሺህ በላይ የፖለቲካ እስረኞችን ፈቱ፡፡ በውጭ ሀገራት እስርና ግድያን ሸሽተው የተሰደዱ በህወሓት/ኢህአዴግ አሸባሪ ተብለው የተፈረጁ ግለሰቦችንና ፓርቲዎችን ለሰላም ጠሩ፡፡ የተመሰረተባቸውንም ክስ አነሡ፡፡ በተመሳሳይ በውጭ ሀገር ስለኢትዮጵያ በመወትወታቸውና ገዢውን ፓርቲ በተለይም ህወሓትን በመቃወማቸው በሽብርተኛ ድርጅት ዝርዝር ውስጥ የገቡትን የመገናኛ ብዙኃንን ክስ ነጻ አደረጉ፡፡ በየትኛውም ፖለቲካዊ ምክንያት ሀገር ጥለው የተሰደዱትን ሁሉ ጠሩ፡፡ ከዚህ በኋላ በእያንዳንዷ ዕለት የነበሩት አዳዲስ "ሰርፕራይዞች" በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ እንዲህ በአጭር ጊዜ ሊከሰት ይችላል ተብሎ በማንም ያልታሰበ፤ በአንጻሩ ግን የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ልብ በኩራትና በተስፋ ያሞቀ ድርጊት ሆነ፡፡

ከአይነኬዎቹ የህወሓት እድሜ ጠገብ ባለሥልጣናት የጡረታ ስንብትን ተከትሎ የፓርቲው ጉምቱ አመራሮች የማይደፈሩ ናቸው ከተባሉት የህወሓት ቁልፍ የጡንቻ እና የገቢ ምንጭ ከሆኑት መከላከያ፣ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ)፣ የደህንነት መሥሪያ ቤት፣ የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) እና መሰል ተቋማት ውስጥ ቀስ በቀስ እየተነቀሉ መውጣታቸው ያስኮረፈው ህወሓት በህዝብ ፊት ራቁቱን የቀረው ባለፈው ሳምንት በተካሄደው የፓርላማው ስብሰባ ላይ ነው፡፡

## የሰኔ 11 የፓርላማ ውሎ

ይህ ስብሰባ በኢትዮጵያ ታሪክ የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነንነት በይፋ ማክተሙ የታወጀበት፣ አንዳንዶች እንደሚናገሩትም ባለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ህዝብ እና ኢትዮጵያ በምትባለው ሀገር ላይ ለደረሰው ከባድ ጥፋት ዋነኛ ድርሻውን ይወስዳል የሚባለው ህወሓት ራቁቱን የቀረበት ቀን ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ካቢኔያቸውን ካዋቀሩ በኋላ በሁለት ወራት ያከናወኗቸውን አበይት ተግባራት በዝርዝር አስረድተዋል፡፡ ህዝብ 27 ዓመት ሰምቶት የማያውቀው ቃልና ተግባር ተጣምሮ ታይቷል፡፡ ከምንም በላይ ፍቅርና አንድነት እንደሀገር ቆሞ ለመሄድ አማራጭ የሌላቸው መፍትሔዎች መሆናቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ውስጥ ቁልፍ ቦታ የያዙ ሐሳቦች ነበሩ፡፡ ከኢኮኖሚና ፖለቲካ ሪፖርቱ በላይ የህዝቡን ቀልብ የገዛው ግን በውስጥ ፖለቲካ መስክ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የወሰዷቸው እርምጃዎችና ወደፊትም የሚጓዙበትን መንገድ ያመላከቱበት ሐሳብ ነው፡፡ በዚህ ገለጻቸው ማን በየትኛው ጠርዝ ላይ እንደቆመ፣ ማን ለጋራ ሰላምና ለመደመር ፖለቲካ ጀርባውን እንደሰጠ ቁልጭ አድርገው አሳይተዋል፡፡ በተለይ ህወሓት እንደፓርቲ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የሪፎርሜሽን ጉዞዎች በተቃራኒ መቆሙን በአንዳንዶች አነጋገርም "ማኩረፉን" ብዙዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁልጭ ያለ ንግግር ገምተዋል፡፡

ኢትዮ -ኤርትራ

## ሕዝብን እንደፖለቲካ አጀንዳ መሸሸጊያ

ህወሓት ሙሉ ድጋፉን ሰጥቶ በመለስ ዜናዊ የተፈረመውንና የጸደቀውን፣ ፓርላማውም ተወያይቶ ያጸደቀውን የአልጀርሱን ስምምነት ሆን ብሎ ሳይተገብር 12 ዓመታት ተቀምጧል፡፡ በኋላም ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ ዛሬ የሰላም ሐሳብ ሲያነሱና



የኢትዮጵያ መንግሥት ያጸደቀውን የኢትዮ-ኤርትራ ድንበር ማካለል ወደተግባር ለመቀየር ሲወስኑ፣ መንግሥትም ውሳኔውን ለማስፈጸም መነሣቱን ሲገልጽ አብሮ የነበረውና ድጋፉን የሰጠው ህወሓት፤ መቀሌ ሄዶ እንደአዲስ “ውሳኔው የህዝብ ይሁንታ የለውም” ብሎ መግለጫ አውጥቷል። ይህ አካሄድ ተራ የፖለቲካ ቁማር መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግልጽ ተናግረውታል።

“በውስጥም በውጭም ያሉ ህዝብ ችግር እንዳለው አስመስለው የሚሠሩ ኃይሎች ከዚህ ድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል። ይህ የኪሳራ ፖለቲካ ሐሳብ ስለሆነ በዚህ የሚገኝ ትርፍ የለም። ከዚህ ወጥቶ ይቅርታን የሚያስተምር፣ ፍቅርን የሚያስተምር፣ አብሮ መሥራትን የሚያስተምር ሐሳብ መያዝ ይበልጥ ይጠቅማል” ነው ያሉት።

አስከትለውም፣ “ይህ ችግር መቆም አለበት፤ ለፖለቲካ ፍጆታ መዋል የለበትም። ይህ ሐሳብ አንዳንዶች ፖለቲካን ለማጣመም የሚጠቀሙበት መሆን የለበትም” በማለት የተቃውሞ አካሄዱ ትክክል እንዳልነበር ተችተዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን ህወሓት አብሮ የወሰነው የሥራ አስፈጻሚው ውሳኔ በሚዲያ መገለጹን መቃወሙ ትክክል እንዳልሆነና ከዚህ በኋላ እንደያኔው ከህዝብ ተደብቆ የሚያልፍ አንዳች ነገር እንደሌለ አስረግጠው ተናግረዋል። “የድበቃ ፖለቲካ ከዚህ ወዲያ ኢትዮጵያ ውስጥ አይሠራም!” በማለት።

ህወሓት በመግለጫው “ህዝብ ሳይወያይበት የተወሰነ” ላለውም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፓርላማው ጥያቄ ጋር በማያያዝ ግልጽና የማያሻማ መልስ ሰጥተዋል።

“አሰብን ስንሰጥ መች ተወያየን፤ እንዲህ አይነት ሎጂካዊ ያልሆነ መከራከሪያ ለጊዜያዊ ፖለቲካ ትርፍ የሚጠቅም ብቻ እንጂ አይጠቅምም። ውሳኔው አስቀድሞ የተወሰነ ነው። አሁን እዚህ ላይ ስንደርስ አይደለም ውይይትን አጀንዳ አድርገን የምናነሣው”

በህወሓት የማስመሰልና “ህዝቡን ካንተ ጋ ነኝ” አይነት መግለጫ የተበሳጩ መሆኑ የሚያስታውቅባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ይህንን የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የተሸረበ ሴራ ሳይወርፉት አላለፉትም።

“ …አብዛኛው ጥያቄውን የሚያነሣውና የሚያራግበው ኃይል፣ ስብስብ፣ ምን ያህል የሞራል ልዕልና እንዳለው አላውቅም! …ውሳኔው [የባድመ ውሳኔ ተደርጎ] ኃላፊነት የማይሰማው ውሳኔ ተደርጎ ለፖለቲካ ፍጆታ መሸጥ የለበትም። ”

## የ “አሸባሪው ማነው?” አያዎ

በፓርላማው የህወሓት ተወካይ የሆኑት ወይዘሮ ያቀረቡት ጥያቄ፣ “ሰው የገደሉ ሰዎች ለምን ይፈታሉ? የጸረ ሽብር ሕጉ ተጥሷል! በሽብር ተከስሰው የተፈረደባቸውን መፍታት ተገቢ አይደለም” የሚል ሐሳብ ያዘለ ነበር። ይህ ጥያቄ የተወካይዋ የግላቸው ብቻ ሳይሆን የፓርቲያቸውም ሐሳብ መሆኑን የሚያረጋግጠው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ቢቢሲ ላይ ቀርበው ከጠ/ሚ ዐቢይ ጋር ስለነበራቸው ውይይት የተናገሩት ነገር ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ “አንዳርጋቸውን ካልፈታን ሥራዬን እለቃለሁ ብዬ ነው እንድትፈታ የተወሰነው” ብለውኛል ብለዋል። ይህ መረጃ ህወሓት የአንዳርጋቸውን መፈታት በጥብቅ ይቃወም እንደነበርና ጠቅላይ ሚኒስትሩንም ሥልጣን እስከመልቀቅ ያደረሰ ትግል ገጥሟቸው እንደነበር ያመለክታል። ራሳቸውም በንግግራቸው አስምረውበታል።

“ለእርቅ የማንተባበር፣ ሰው ሲፈታ ዓይናችን የሚቀላ፣ ይህ ነገር አደገኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ለኢትዮጵያ አይጠቅማትም፣ የሚያስፈልገን እርቅ፣ ይቅርታ ሰላም ነው”

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለተወካይዋ ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፣ በተለይ አሸባሪው ኃይል ሲጠቀምና ሰዎችን ያለመረጃ አስሮ ሲያንገላታ የኖረው የኢህአዴግ መንግሥት እንጂ የነጻነት እና የመብት ጥያቄ ያነሣው ህዝብ አለመሆኑን ለሁሉም በሚገባ ቋንቋ አስቀምጠውታል።

“ሽብር ሥልጣን ላይ ለመቆየት ኢ-ሕገ መንግሥታዊ በሆነ መንገድ ኃይል መጠቀምን ይጨምራል። ሥልጣን ለመያዝ አላግባብ ኃይል መጠቀምን ይጨምራል። … የደህንነት ኃይሎችን፣ መከላከያውን ጨምሮ ያደራጀናቸው ከፖለቲካ ገለልተኛ አድርገን ካልሆነ ኢ-ህገ መንግሥታዊ ተቋም ፈጥረናል ማለት ነው። ሕገ መንግሥቱ በፍርድ ቤት የታሰረ ሰው ግረፉ፣ ጨለማ ቤት አስቀምጡ ይላል? አይልም። መግረፍ ጨለማ ቤት ማስቀመጥ አካል ማጉደል የኛ የአሸባሪነት ተግባር ነው።”

## ሌብነትና የህወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣናት

ግሎባል ፋይናንሻል ኢንቴግሪቲ (Global Financial Integrity) የተባለው ዓለም አቀፋዊ ተቋም በቅርቡ ባወጣው ዘገባ መሰረት እ.ኤ.አ. ከ2000 ዓ.ም. ጀምሮ በሕገ ወጥ ምስጢር የገንዘብ ዝውውር ምክንያት ኢትዮጵያ ወደ 12 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ አጥታለች፡ ፡ ታላላቅ የህዝብ ሥራዎችን እና የፕሮጀክቶች ኮንትራቶችን የውሸት ካባ በማልበስ በድብቅ ለገዥው አካል ደጋፊዎች እና ሎሌዎች በመስጠት በምስጢር ሙስናው ተጧጡፏል። የገዥው አካል ተዋንያኖች ከሁሉም ባለሀብቶች እና ከሚሰጧቸው የግዥ ስምምነቶች ባለድርሻ አካላት ጋር ምስጢራዊ (ድብቅ) ስምምነቶች እንዳላቸው ይጠረጠራል።

ብዙዎች እንደሚገምቱት በተለይ ጡረታ የወጡ እና ከሓላፊነታቸው የተገለሉ የህወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣናትን ያሳሰባቸው ጉዳይ የህዝብ ችግር ሳይሆን ይህ የራሳቸው የሙስና ወንጀል ሊጋለጥና እስርም ሊመጣ የሚችል መሆኑ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በግልጽ የተናገሩትም ሌቦች ማስረጃ ሲጠናቀር “ወደቃሊቲ እንደሚወርዱ” ነው። ይህ አቋም በሙስናና ገንዘብ ማሸሽ የሚጠረጠሩ የህወሓት ጡረተኛ ባለሥልጣናትን ቢያስጨንቅና ለተቃውሞ ቢያነሣሣ አይገርምም።

“…በመንግሥት ሥልጣን የህዝብን ሀብት መስረቅ ጸያፍ ብቻ ሳይሆን ከወንጀልም በላይ አስቀያሚ ወንጀል ነው። በመንግስት ሥልጣን ላይ ተቀምጦ ነጋዴ፣ ሀብታም መሆን አይቻልም። …የህዝብ ሀብት የዘረፉ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ። መዝረፍ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ በርካታ ሀብት በተለያዩ ሀገራት ተከማችቷል። ይህንን እንዳትጠራጠሩ። ሁለት ምርጫ ነው ያለው። እንደዚህ ቀደሙ በሂደት ማስረጃ ይመጣል ብለን ሰብስበን ማሰር፤ አልያም የተሟላ ማስረጃ እስክንይዝ ሰዎቹን ዓይናችን እንዳረፈባቸው አቆይተን የተሟላ ነገር ስናገኝ አጣርተን ብናስር ይሻላል ብለን ነው።”

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ብቻ አላበቁም። የህወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣናት ህዝብ በግልጽ በሚያውቀው ሁኔታ ሌብነታቸው እየተገመተ እና አሁንም በውጭ ሀገራት ትብብር የዘረፉት ገንዘብ መረጃ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር እየደረሰ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በሌላ የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ በመክተት ርካሽ የፖለቲካ ጨዋታ ላይ መጠመዳቸው ያናደዳቸው ይመስላል።

“…መረጃ ስናገኝ ብናስር ይሻላል ብለን እንጂ ሌቦች የሉም ብለን አይደከለም። ሌቦች መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ሌብነታቸው ያስታወቀባቸው አካላት ሲሸርቡና ሲዶልቱ መዋላቸው ደግሞ ተጨማሪ በሽታ ነው። ሰርቆ ዝምም ጥሩ ነው፣ ከዚያ ሲሻገር ግን ጥሩ አይደለም”

## “ጂኒው አምልጧል!”

አሁን ሌብነትን የመደበቅ፣ የፖለቲካ ቁማር ጨዋታን የማጋለጥ፣ ሀገርን የማሳደግ፣ ሰላምና ፍቅርን የማምጣት፣ የመተባበርና የመደመር፤ በአጠቃላይ የኢትዮጵያዊነት ጂኒ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጠርሙስ ውስጥ አምልጧል። መልሶ ወደጠርሙሱ መክተት በፍጹም አይቻልም። ቢቻልም የመጨረሻ ውጤቱ ጠርሙሱን ማፈንዳት ይሆናል። ያም ሆኖ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንገድ ለነጻ እርምጃ ቀላልና የተደላደለ እንዲሆን አይጠበቅም። ነገር ግን ጊዜ ይፈጅ ካልሆነ በቀር በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ህዝብን ከጎኑ ያደረገ ማንም ቢሆን ሁሌም አሸናፊ ነው።

# <<ለውጡን እንደግፋ፤ ዴሞክራሲን እናበረታታ>>


## ከሠላማዊ ሠልፉ አስተባባሪዎቹ ጋር የተደረገ ቆይታ



ስዩም ተሾመ



አበበ ቀስቶ



ስንታየሁ ቸኮል

ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ በአጭር የስልጣን ዘመናቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተደናቂነትን አግኝተዋል:: ግለሰቡ በማለዳው ይህን ክብር ያተረፉት በገዢዎች መንፈስ ውስጥ ጠፍቶ የነበረውን ኢትዮጵያዊነት ስሜት በከፍትኛ ሁነታ በማስተጋባታቸው ነው:: ለዘመናት አንድነቱን ጠብቆ የኖረው የሀገራችን ሕዝብ ለኢትዮጵያዊነት ያለው ክብር እንዲህ በቀላል የሚገለጽ ባይሆንም በተለይም ደርግ ከወደቀ በኋላ ሥልጣን ላይ የመጣው ኢህአዴግ ሀገራዊ ፍቅርን አሽቀንጥሮ በመጣል ጽንፍ የያዘ የብሔር የበላይንትን ሲያቀነቅን ኖሯል::

ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊነት ከማዳፈን ባሻገር ዜጎቹ ላይ ኢ- ሰብአዊ ድርጊት መፈጸሙን ሥራዬ ብሎ ተያይዞት ከርሟል:: ሕዝብ ሥርዓቱን "በቃህ" በማለት ወደ ለውጥ ጎዳና ሲመራው ባልተጠበቀ ሁኔታ ከአህአዴግ ጉያ የወጡት ጠቅላይ ሚኒቴር አብይ አህመድ የማንነታችን መገለጫ የሆነውን ኢትዮጵያዊነታችን ዳግም እንዲያንሰራራ አድርገዋል::

በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዝብ ከመሪው ጎን መቆሙን ለማረጋገጥ ሙሉ መሰናዶው ተጠናቋል:: ይህ ታሪካዊ ድጋፍ እንደ ከዚህ ቀደሙ በመንግስት ጥሪ ወይም በተፎካካሪ ፓርዎች ገፋፊነት አይደለም የሚካሄደው:: በሕዝብ ፅኑ ፍላጎትና እውነተኛ ስሜት እንጂ::

ይህንን ሠልፍ ያዘጋጁ አካላትን በማነጋገር ስለ ጉዳዩ አንዳንድ መረጃዎችን ለማግኘት ሞክረናል:: ጠ/ሚኒስቴር አብይ አህመድ ጊዜው የፍቅርና አንድነት መሆኑን በተናገሩት መሠረት መሪያችን ያሰቡትን ከግብ ያደርሱ ዘንድ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው አዘጋጆቹ ያምናሉ:: "ለውጥን እንደግፍ፤ዲሞክራሲ እናበረታታ" በሚል መርህ ወደ ተግባር ከገቡት ሕዝባዊ የድጋፍ ሠልፍ አዘጋጆች መሀል መምህር ስዩም ተሾመ የታየው ጅምር ለውጥ ዘለቄታዊነት እንዲኖረው ለማበረታታትና ድጋፍ ለመስጠት ሕዝባዊ ሰላማዊ ሠልፍ አሁን በሀገሪቱ ውስጥ ዲሞከራሲን ለመገንባት የሚደረገው ጅምር ጥረት ወደፊት እንዲቀጥል መደገፍና ማበረታታት ይኖርብናል ይላል::

የለውጥ ጅምር እንቅስቃሴውን ከፊት ሆነው እየመሩ ያሉት አብይ አህመድን አድናቆት መስጠትና ማክበር ማበረታት መደገፍ፣ የተጀመረውን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የተደረገውንም ጥረት በግልጽ ማድነቅ በቀጣይነት በሕብረተሰባችን ውስጥ መለመድ ይኖርበታል::

ሠላማዊ ሠልፍ በመውጣት፣ ተወጥቶም ሃሳብን በነጻነት መግለጽ ዲሞክራሲያዊ መብታችን በመሆኑን ያንን እያደረግን ነው የሚለው መመህርና አክቲቪስት ስዩም ተሾመ ለጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ የተዘጋጀውን የድጋፍ ሠልፍ ያስተባበሩት አካላት በተደጋሚ በሥርዓቱ የታሰሩ ቢሆንም በገሀድ የታየውን እውነታ ማድነቅ ግን አትዮጵያዊነት ግዴታችን ነው ብሎ ያምናል::

‹‹እስከዛሬ ደረስ የለውጥ እንቅስቃሴ እንዳይደረግ ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርአት እንዳይዘረጋ፣ የመብት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ በሀይል ሲታፈን፣ በጉልበት ሲዳፈን የነበረ ማህበረሰብ ነው ይህን የድጋፍ ሠልፍ ያዘጋጀው:: አብዛኞቻችን በሥርአቱ በደል ሲደርስብን የነበርን ሰዎች ነን:: አሁን እኛ በፊት ስንጠይቅ የነበረው ነገር መስመር መያዝ ጀምሯል::

ጠ/ሚኒስቴሩ በፓርላማ በይፋ እንደተናገሩት ሕዝብ ተሸብሮ ነው አደባባይ የወጣው:: ህዝብን ያሸበረው መንግስት ነው፣ ጥፋቱ የመንግስት ነው፣ ይሄ ነገር መቀየር አለበት:: ስለ እዚህ የታገልንለት፣ የታሰርንለት ነገር መስመር ሲይዝልን ስላየን ነው እየደገፍን ያለነው:: በደልና ጭቆናው ተመልሶ ከመጣና ሥርአቱ ካልተቀየረ ተመልሰን ተቃውሞ ውስጥ ልንከርም ነው:: ለውጥን መደገፍና ማበረታታት ስላልለመድን ይሄ ነገር አዲስ ሊሆን ይችላል እንጂ ያደርገነው ነገር መሆን ያለበትን ነው›› በማለት ስዩም ተሾመ ስለ አዘጋጆቹ አጠቃላይ ስሜትና እምነት ለዝግጅት ክፍላችን ገልጾልናል::

ቅዳሜ ሰኔ 16 ቀን የሚካሄደው የድጋፍ ሠልፍ ሕዝብ የመሰብሰብ ፣ የመደራጀት ሠላማዊ ሠልፍ አድርጎ አቤቱታን የማስተጋባት ▶

መብት እንዳለው በተግባር የሚያረጋግጥበት፣ ላለፉት አስራ ሶስት አመታት ዜጎች ይሄን ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን በተግባር እንዳያረጋግጡ በጉልበት ታፍነው ነበር የሚለው መምህር ስዩም አስተባባሪዎች በዚህ ሠላማዊ ሠልፍ ለበርካታ አመታት ዜጎች የታሰሩበትን የፍርሃት ቆፈን እየሰበርን እንደሆነ የምናረጋግጥበት ጅምር እንቅስቃሴ ነው ሲል አረጋግጧል::

ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ውስጥ በመንግስትና በተፎካከሪ ፓርቲ ደረጃ የተለያዩ ሠላማዊ ሠልፎች ተካሂደው የነበር ቢሆንም በ1997 ዓ.ም ቅንጅት ከጠራው ሠላማዊ ሰልፍ ቀጥሎ የቅዳሜው ጠ/ሚንስትር አብይ አህመድን የሚደግፈው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ትልቁ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ ግምቱን ያስቀመጠው ሌለው የዝግጅቱ አስተባባሪ አክቲቪስት ስንታያሁ ቸኮል ለአመታት ዜጎች ታፈነው ከነበረበት የጨለማ ጉዞ ለማውጣት በመተመረጡ ማግስት ድንቅ እንቅስቃሴ እያደረጉ የሚገኙት ጠ/ሚኒስቴር አብይ አህመድን መደገፍ ኢትዮጵያዊነት ነው ብሎ ያምናል::

እንደ ስንታየሁ ገለጻ ከሆነ ጠ/ሚኒስትር አቢይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡ በኂላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በመሪ ደረጃ በሕዝብ ጆሮ ውስጥ ያልተሰሙ አዳዲስ ክስተቶችን እያስተጋቡ ነው ያሉት:: በመነጋገር የሚያምን መሪ በ27 አመት ውስጥ እንዳልታየና ወጣቱ የሀገር መሪ ራዕይ ግን ከኢህአዴግ ሰዎች በተለየ መልኩ አንድነትና ፍቅርን ከመስበክ ባሻገር በተግባር አሳይቶናል:: ሁልጊዜ በተቃውሞ መንገድ መወነጃጀል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን ከፍ አድርጎ በንግግር የሚያምን መሪ ሲመጣ ማመስገንን መልምድ አለብን:: እሰራለሁ ብሎ የሚማጣ ሰው በርታ ብሎ ከመደገፍ በተጨማሪ ከጎኑ መቆማችንን በገሀድ ማሳየትን መልመድ ይኖርብናል የሚለው ወጣቱ አክቲቪስት ስንታየሁ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቃል ደረጃ ለሕዝብ የተናገሯቸውን ነገሮች ወደ መሬት አውርደው እንዲተገብሩ፤ ብሎም የጀመሩትን እንቅስቃሴ ሊያደናቅፉ ለሚፈልጉ ኃይሎች አርፋችሁ ተቀመጡ መልእክቱን ይዞ ሰልፉ እንደሚካሄድ ገልጾልናል::

ሠላማዊ ሠልፉ ስርዓቱን የመደገፍ ሀሳብ ይዞ ሳይሆን ጠቅላይ ሚነስቴሩ ይዘው የመጡትን ሃሳብ በማክበር ነው:: ወጣቱ መሪ የዘውት የመጡት ሃሳብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃሳብ ነው፡ኢትዮጵያን ሊያድን የሚችል ሃሳብ ደግሞ በተግባር ሊደነቅ ይገባዋል:: ባለፉት አመታት አንድም ቀን ኢትዮጵያን ሳያነሱ የሚጓዙ መሪዎች ነበሩ፤ አሁንም ደሞ ኢትዮጵያን ማንሳት ብቻ ሳይሆን ከሕዝቡ ጋር የሚያለቅሱ መሪ ተገኝተዋል:: እናም እኚህን ሰው "በርቱ" ማለት ጤናማ አስተሳሰብ ነው ይላል ስንታየሁ ቸኮል::

‹‹አንዳንድ ወገኖች አቢይን ለማድነቅ ቸኮላችሁ የሚሉት ነግር ብዙም የሚያስኬድ አይመስለኝም፤ እሳቸው ኢትዮጵያዊነትን ከመመለስ ባሻገር በዚህ የሶስት ወር እድሜ ውስጥ የሰሩትንና ያሳዩንን በጎ ጅምር ሌሎቹ የኢህአዲግ ሰዎች በሩብ ክፍለ ዘመን ውስጥ አላከናወኑትም:: ሰው በየትኛውም አቅጣጫ ጥሩ ሃሳብ ይዞ ሲመጣ ሊበረታታ ይገባል::እኛ ያንን ነው የሰራነው:: የእሳቸው አካሄድ የማይመቻቸው ሰዎች ደሞ በእርምጃቸው ፊት ለመቆም ብዙ ነገር ሊሉ ይችላሉ::እኛ ጠቅላይ ሚኒስቴሩን ስንደግፍ የእነዚህን ሰዎች እኩይ ተግባራቸውን እንቃወማለን::

ከዚህ በኂላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በመሳሪያ አፈሙዝ ወደ ስልጣን የሚመጣ አይኖርም:: ይህ አካሄድ እንደቀረ ሊገባቸው የሚገባ አካላት አሉ:: በዚህ ዘመን የሚጠቅመውም ሕዝብ የሚፈልገውም የብሔር መከፋፈልን ሳይሆን አንድነትንና ኢትዮጵያዊነትን ነው:: ለአመታት እርቦን የነበረውን ይህንን ቅን መንፈስ እንደመጡ የመገቡን ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ናቸው:: ስለዚህ ለእሳቸው ክብር ስንል ይህንን የድጋፍ ሰልፍ አዘጋጅተናል:: ከላይ በገለጸኩት መልኩ ሠልፉ የድጋፍ መንፈስ ቢሆንም ሕዝብ ከተለያየ አቅጣጫ በራሱ ተነሳሽነት የሚመጣ በመሆኑ የተለያዩ መፈክሮችንና ቲሸርቶችን ሊጠቀም ይችላል፤፤ይህ ደሞ መብት ነው:: እኛ በዋነናነት በቦታው ላስቀመጥናቸው አስተባበሪዎች ቲሸርትና ባጅ አዘጋጅተናል:: ከዚያ ውጭ ያለው ነገር የአዘጋጆቹን አቋም አይገልጽም፤ ግን የትኛውን ያህል ህዝብ ቢበዛና ቢወጣም ሕብረተሳበችን ጨዋነትን በተላበሰ መልኩ ሠላማዊ ሠልፉን ያጠናቅቃል›› የሚል እምነት አለኝ ሲል ስንታየሁ ከዝግፍጅት ክፍላችን ጋር ያደረገውን ቆይታ አጠናቋል::

በታሪክ በሕዝብ ተነሳሽነት የተዘጋጀው ይህ ሰላማዊ ሰልፍ በኢትዮጵያ ሕዝብ ልዩ ድጋፍ ይደምቃል ተብሎ ይጠበቃል:: ጠቅላይ ሚኒስቴሩን መደገፍ ኢትዮጵያዊነት ነው በሚል ስሜት ከደሴ፣ከድሬደዋና ከጅማ እንዲሁም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ወጣቶች በተለያየ መንገድ በመዋቀር በሰላማዊ ሰልፉ ላይ ለመሳተፍና ለመሪያችን ድጋፍ ለመስጠት ሙሉ መሰናዷቸውን አጠናቀው በሳምንቱ መጨረሻ አዲስ አበባ ይገባሉ ተ ብ ሎ ይጠበቃል::



በኢህአዴግ ሥርአት በተደጋጋሚ ለእስር የተዳረገውና "አሸባሪ" ተበሎ ከ6 አመት በላይ በእስር አሳልፎ ከወራት በፊት የተፈታው ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) ሌላኛው የእዚህ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አስተባባሪ ነው:: የበደሉህን ሰዎች ይቅር በማለት ነው ልታስተምራቸው የሚለው አቤ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ ይዘው የመጡት ሀሳብ እሱና ጓደኞቹ ለዘመናት ለእስር እንዲዳረጉ ያስገደዳቸውን ጭቆና የሚያወግዝና ዲሞራክሲን የሚያለመልም በመሆኑ ይህንን ሁኔታ በአደባባይ ለመመስከር እንዳነሳሳው ይናገራል::

ቴዲአፍሮ በአሁኑ ሰዓት ከሚገኝበት አሜሪካ ሆኖ ባወጣው መግለጫ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድን መደገፍ አግባብ እንደሆነ ከተናገረ በኂላ በሕዝብ ዘንድ ቅዳሜ በመስቀል አደባባይ ለመገኘት የበለጠ መነሳሳቱን የጠቆመው አበበ ቀስቶ በዚህ ታሪካዊ ቀን ላይ ኢትዮጵያዊነት ያለው ዋጋ በግልጽ ከመታየቱ ባሻገር ሕዝብ የሚያስብለትና ሀገራዊ ስሜትን የሚገነባለት መሪ ካገኘ ለማድነቅ ወደኂላ እንደማይል ያረጋግጣል ተብሎ ይጠበቃል ሲል ይናገራል::

"ከከተማው መስተዳደር በፍጥነት ፍቃዱን ለማግኘት ያልቻልነው ከፀጥታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ነው፤ በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ከ ሶስት እስከ አራት ሚሊየን የሚደርስ ህዝብ ይወጣል የሚል ግምት በእኛ ዘንድ ስለነበር ይህንን ሁሉ ሰው እንዴት ልትቆጣጠሩት ትችላላችሁ የሚለው ነገር በእነሱ ዘንድ መደራደሪያ ነበር፤ እኛም ሕዝብ እራሱን በራሱ እንደሚጠበቅና ምንም አይነት አስጊ ነገር ሊኖር እንደማይችል አረጋግጠንላቸዋል::

ይህንን ታሪካዊ ሰልፍ ለማድረግ ያነሳሳን በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡ በኂላ ያሳዩን ሀገራዊና ሕዝባዊ ፍቅር የይቅርታና የአንድንት መንፈስ ነው:: ሰዎች ይህንን ሰላማዊ ሰለፍ ላድረግ ገንዘቡን ከየት አመጣችሁት? ይሉናል ግን ይህን ስራ በአብዛኛው በነጻ ትብብር ነው የሰራነው:: ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠንበት ኢሊሌ ሆቴልን ጨምሮ በርካታ ነገሮችን ሰዎች በፈቃደኝነት ተባብረውናል:: እኛ ዝግጁቱን ለሚያስተባብሩ ሰዎች ቲሸርት ማሳተም ብቻ ነው የሚጠበቅብን ያንን እናደርጋለን›› የሚለው የሰላማዊ ሰልፉ አስተባባሪ አበበ ቀስቶ ቅዳሜ ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ ሕዝብ የድጋፍ ሰልፉ ላይ በመገኘት ኢትዮጵያዊነትን ከማስተጋባት ባሻገር ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለማድነቅና ለማመስገን በመስቀል አደባባይ እንዲገኙ ጥሪ አቅርቧል::

ልዩ ዘገባ

# የብሔር ግጭቶች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል

የለውጥ አራማጁን የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድን ሥልጣንና የሚያከናውናቸውን እረፍት አልባ መልካም ተግባራት ያልተመቻቸው ወገኖች በሀገሪቱ ውስጥ ትርምስ በመፍጠር በለመዱት የትርምስና የጎሳ ግጭት ፖሊሲያቸው በቁልቁለት መንገድ ሀገሪቷን ይዞ ለመንጎድ ከፍተኛ ትግል እያደረጉ መሆኑን እየተነገረ ይገኛል:: ይህን ጉዟቸውን ለመግታት ደግሞ ጠ/ሚ ዐቢይ ሰኔ 8 ቀን 2010 ዓ.ም. ምሽት (ከአረቡ ንጉሥ 3 ቢሊየን ዶላር ድጋፍ ከተቀበሉ በኋላ) በደቡብ ክልል የፍቼ ጨምበላላን በዓል አስታኮ የተፈጠረውን የብሔር ግጭት አስመልክተው ይፋዊ መግለጫ ለህዝቡ አስተላልፈዋል:: በዚህ መግለጫቸው፣ "…ይህ ችግር እኛን አባልተው ሊበሉን ያሰቡ 'የቀን ጅቦች' የፈጠሩት ችግር ነው!…" በማለት ገልጸዋቸዋል::

"ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሀገር ማረጋጋት አልቻሉም" በሚል ምኞት ከሥልጣናቸው ለመገፍተር እየተሠራ ያለ ሥራ መኖሩን በራሳቸው በጠ/ሚኒስትሩ ጨምሮ በብዙዎች እየተነገረ ይገኛል:: የጠ/ሚ ዐቢይን መንግሥት ሀገሪቷን በሰላም የማስተዳደር ዐቅም ስለሌለው… የሚል አንድምታ ለመፍጠር የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች (የቀን ጅቦች) በሀገር መከላከያው እና በደህንነቱ ውስጥ ተከማችተው እንደሚገኙም ደጋግሞ እየተገለፀ ይገኛል:: የጠ/ሚ ዐቢይ ዋናዎቹ የአስተዳደር ፈተናዎቻቸው ደግሞ እንደርሳቸው አገላለጽ እነዚሁ የቀን ጅቦች ናቸው:: ረዳት ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና "ትልቁ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈተና ሀገርን ማስተዳደር ሳይሆን ኢህአዴግን ማስተዳደር ነው" ያሉት ነገር አሁን ፍንትው ብሎ እየታየ መሆኑን የፖለቲካ ተንታኞች ደጋግመው ይናገራሉ::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት የቀን ጅቦቹ አባልተው ሊበሉን ተዘጋጅተዋል:: ሀገሪቱን በብሔር ከፋፍለው ኢኮኖሚውን በአጥንቱ እስኪቀር ሲግጡ የነበሩት የቀን ጅቦች፣ "ዝርፊያችንና ኢትዮጵያን መበታተናችን ለምን ተደናቀፈብን?" በሚል እብሪት ከክልል ክልል እየተክለፈለፉ የእልቂት መርዝ ለመርጨት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ይገልፃሉ::

ገና የሦስት ወር የጠቅላይ ሚኒስትርነት እድሜ ላይ ሆነው በማይታመን ፍጥነት ብዙ ተስፋ ሰጪ እርምጃዎች እያሳዩ ያሉትን የጠ/ሚ ዐቢይን ሥልጣን ለማኮሰስ (Undermine) በየአቅጣጫው የሚለኩሷቸውን የግጭት እሳቶች "በማስተዋል" እና "በአንድነት" ውሃ ሊቸለስባቸው ይገባል የሚሉ የ"ዐቢይን እንደግፍ" ዘመቻም ተጀምሯል::

በሶማሌ ስም ኦሮሞን በማጥቃት የብሔር ግጭት ፖሊሲያቸውን ሲያስፈፅሙ የንጹሐን ዜጎችን ሕይወት ከመቅጠፉ ባሻገር ከግማሽ ሚሊየን በላይ የኦሮሞ ህዝብ ተፈናቅሎበታል:: በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልልም የሰው ሕይወት የጠፋበት እና ንብረት የወደመበት ማፈናቀል በቅርቡ ድጋሚ የተከሰተ ሲሆን ከ500 በላይ የሚሆኑ የአማራ ብሄር ተወላጅ የሆኑ ተፈናቃዮችም በባህር ዳር ከተማ መከተማቸውን መገናኛ ብዙሃን ሲዘግቡት ከርመዋል:: ይኼው የቤንሻንጉል ደም ሳይደርቅ በኦሮሞ ስም አማራን በማጥቃት የሁለቱን ታላላቅ ክልሎች ህዝብ ለማጋጨት ደባና የጎሳ መርዛቸውን አምቦ ላይ መርጨታቸውን ቀጠሉ:: እነ ኦቦ ለማ ለዘመናት የቀን ጅቦች አፈራርሰነዋል ያሉትን የኢትዮጵያዊነት አንድነትና የፍቅር ግንብ እንደገና ለመገንባት በሚያደርጉት "ጊዜ አይሰጤ" ሩጫ ላይ ከፊት እየቀደሙ ለማደናቀፍ ከኢትዮ ሱማሊና ቤንሻንጉል የተረፉቸውን እሳት ይዘው ኦሮሚያ ክልል ሰተት ብለው ገቡ::

የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ኃላፊ ዶ/ር ነገሪ ሌንጮ "የተፈናቀለ የለም" በሚል ከካዱ ከሳምንታት በኋላ ዘግይቶም ቢሆን የአቶ ለማ አስተዳደር በኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ የአማራ ተወላጆችን አፈናቅላችኋል፣ ወይም ለማፈናቀል ሞክራችኋል፣ ጥላቻን ዘርታችኋል፣ ወይም ህዝብ ለህዝብ እንዲጣላ ምክንያት ሆናችኋል የተባሉ የዞን፣ የወረዳ፣ የቀበሌ አመራሮችን አሰናብተዋል፣ የአንዳንዶቹም በሕግ እንዲታይ በማድረግ ፈጣንና ድንገተኛ እርምጃ ወስደዋል:: ኦቦ ለማ መገርሳ የቀን ጅቦቹ እንደፈለጉ በገንዘባቸው የሚያሽከረክሯቸውን ሁለት መቶ የኦሮሚያ አመራሮች አባርረው የግጭት ኔትወርካቸውን ስለበጣጠሱባቸው ካደረባቸው ቁጭት በላይ "ለአማራ እንዴት እንዲህ ጠበቃና ከለላ ይሆናል? በሚል በንዴት ተወራጭተዋል::

የተከበሩ አቶ ለማ "…የአማራ ህዝቦች ወንድሞቻችን ናቸው፣ ያለ እነሱ እነሱም ያለኛ… ወይም አንዳችን ያለ አንዳችን መኖር አንችልም…በቅርቡ የመጣውን ለውጥ እንኳን ተመልከቱ፣ የሁለቱ ክልል ህዝቦች ትግል ነው…አሁን የምታዩት ለውጥ የመጣው… የኦሮሚያ ክልል ተወላጆች በአማራ ክልል ያለምንም ችግር እየኖሩ ነው፣ ስለሆነም ወንድሞቻችን በኦሮሚያ ክልል ያለምንም ሥጋት ሠርተው ራሳቸውን መለወጥ፣ ሀብት ማከማቸት ይችላሉ፣ አንዳንዶች በኦሮሚያና በአማራ ክልል ተወላጆች ላይ አለመተማመንን ለመፍጠር እየተሯሯጡ እንደሆነ በዚህ ሳምንት የታየ ድርጊት መሆኑን አረጋግጫለሁ፣ ስለዚህ የሁለቱ ክልል ህዝቦች ይህንን ሤራ መመከት ያስፈልጋል…" የሚለው የኦቦ ለማ መገርሳ ንግግር ነው:: ባለፈው ሳምንትም በኦቦ ለማ ትዕዛዝ ሰጪነት ዶ/ር ነገሪ ሌንጮ የሚመሩት ቡድን ባህር ዳር ከተማና ራያ ቆቦ በመሄድ የተፈናቀሉትን የአማራ ተወላጆች ሰብስበው ይቅርታ በመጠየቅና መልሰው ወደ መኖሪያቸው በሚመለሱበት ሁኔታ ላይ በመምከር አስፈላጊውን ድጋፍ ክልሉ እንደሚያደርግ በምስልና በድምጽ አስደግፈው የአማራና የኦሮሚያ መገናኛ ብዙኃን ዘግበውታል::

ይህ የለማ ቡድን እርምጃ የእግር እሳት የሆነባቸው የጥፋት ኃይሎች በእልህና በቂም በቀልነት ደም እያሰከራቸው የተጓዙት ወደ ደቡብ ሀዋሳ፣ ወልቂጤና ወላይታ ከተሞች ነው:: "ለጅቦቹ ዕድል አንስጣቸው" ያሉት ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ፤ "በኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደው "የአመራር ለውጥን" ተከትሎ መንግሥት እየሠራ ያለውን የሰላምና መረጋጋት ሥራዎች "ወደኋላ ለመመለስ የሚጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖች" እንዳሉ ሰኔ 11 ቀን 2010 ዓ.ም. በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ላይ ተናግረዋል::

የቀን ጅቦቹ ሰሞኑን ማለትም ሰኔ 5 ቀን 2010 ዓ.ም የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ በዓል በሀዋሳ ከተማ በሚከበርበት ዕለት ባስነሡት ግጭት እና ቀጥለው በመጡ ሁለት ቀናት በተፈጠሩ ውጥረቶች 10 ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉን፣ 9 ሰዎች ከባድ፣ 80 ደግሞ ቀላል ጉዳት እንደደረሰባቸው የክልሉ መንግሥት የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ አስታውቋል። ከ50 በላይ ብሔረሰቦች የሚኖሩበት የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ክልል ለተለያዩ የብሔር እና ጎሳ ግጭቶች እንግዳ ባይሆንም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሲዳማ እና ወላይታ ብሔሮች መካካል የተፈጠረ ቁርሾ የውጥረት ምንጭነቱ እንደጎላ ነዋሪዎች ለመገናኛ ብዙኃን ሲናገሩ ተደምጧል።

በሀዋሳው ግጭት ማግስት ሰኔ 8 /2010 ዓ.ም. "የወላይታ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ብሔር ተኮር የነፍስ ማጥፋት እና ንብረት ማውደም ይቁም" የሚል እና ሌሎችንም መፈክሮች የያዙ ሰልፈኞች ወደ ጎዳና ወጥተዋል። ሆኖም ሰላማዊ ሰልፉ ከቆይታ በኋላ ወደግጭት ተለውጧል። ማርያም ሰፈር ከሚባለው ስፍራ የተነሱ ሰልፈኞች በመጀመሪያ 'ጥቅማችንን እያስጠበቀ አይደለም!' ያሉትን የዞን አስተዳዳሪ ለማጥቃት ወደመኖሪያ ቤታቸው እንዳቀኑ፣ በመንገዳቸውም ላይ ያገኟቸውን የግብርና መምሪያ፣ የገጠር ቴክኖሎጂ ተቋምና የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ላይ እንዲሁም የተለያዩ የመንግሥት እና የግል ተቋማት ላይ ጉዳት እንዳደረሱ የዓይን ምስክሮች በምስል እና ቪዲዮ አስደግፈው ለቢቢሲ ገልፀዋል። በዚህ ግጭት 3 ሰዎች ሕይወታቸውን እንዳጡም የክልሉ መንግሥት አስታውቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በሀዋሳና በወላይታ ሶዶ በተነሱት ግጭቶች ዙሪያ ከኅብረተሰቡ ጋራ ለመወያየት ባሳለፍነው ሳምንት ወደ ሥፍራው አቅንተው "የመልካም አስተዳደር ችግርን የሚፈጥሩት የፖለቲካ ነጋዴዎች ናቸው፤ ከዚህ ተግባራቸው ሊቆጠቡ ይገባልም" ብለዋል። አንዱን ብሔር ከሌላው በማጋጨት ሀገር መገንባት እንደማይቻል ጠቅሰው፥ የዜጎችን ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ የመሥራት መብት ከማስጠበቅ አንጻር የተሠሩ ሥራዎች ውስን መሆናቸውን ገልጸዋል። ከዚህ አንጻርም መንግሥት ይህን ለመቅረፍ የሚያስችል ሥራ እንደሚሠራ አስረድተዋል።



ሁሴን ከድር

# ወደየትም የማያስኬደው የዘረኞችና የሌቦች ሴራ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ሰኞ ዕለት ለፓርላማ አባላት ያደረጉትን ንግግር ደጋግመን አዳመጥን:: ቀን በቀጥታ ስርጭት፣ ምሽት ደግሞ ቅጂውን:: ከዚህ ቀደም የመሪዎችንም ሆነ የታላላቅ ሹማምንት የፓርላማ ገለጻ ለነቆራ፣ ለትችት፣ ለማሽሟጠጥ ካልሆነ ብዙም ትኩረት ሰጥተን አናዳምጥም ነበር:: ምክንያቱም ከላይ እስከ ታች ሹም በሚዲያ ከቀረበ ከዚህ ቀደም የሠራው ወንጀል ፊት ለፊት ድቅን ስለሚልብን ምክሩም ገለጻውም አይጥመንም ነበር:: የጠ/ሚ ዐቢይን ገለጻ ተገደን ሳይሆን ወደንና ፈቅደን ያደመጥነው በመሆኑ አልጎረበጠንም::

በጠ/ሚ ዐቢይ ንግግር ውስጥ በጨረፍታም ቢሆን የሃይማኖት ተቋማት በሌብነት ሲጠረጠሩ የሃይማኖት መሪዎች ጥፋታቸውን ያምናሉ እንጂ ዝም አይሉም ብለን ስንጠብቅ በፓርላማ ተኮፍሰው ስናይ አፍረንም ተሸማቀንም አልበቃንም:: አንድ የሃይማኖት ድርጅት ሌብነትን ከታላላቅ ኃጢአቶች እንደአንዱ እያስተማረ፣ "አንተ ራስህ ሌባ ነህ" ሲባል እንዴት ለክርክር እንኳ አይቃጣም? በርግጥ ሌባ ከሆነ የትኛውን ምእመን ነው ሕገ ፈጣሪን በማስተማር ሥነ-ምግባርን የሚሰብከው? ሃይማኖቶች ሥነ-ምግባርን ከማስተማር ውጪ ሌላ እሴት የላቸውምና:: ሌብነትን መከላከል ቀርቶ ማውገዝ እንኳን አለመቻላቸው በሃይማኖት ተቋሞቻችን ላይ ቅንጣት እምነት እንዳይኖረን ይገፋፋናል::

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትችት አብዛኞቹ የኢህአዴግ ሹማምንት ጎጠኝነትና ሙስና ኒሻናቸው እንደሆነ ተረድተናል:: ትችታቸውም ሰው አልባ ፓርቲ እያስመረራቸው እንደሆነ ነው ያስጠረጠረን:: ይህን የሰማ ግልገል ሹም "ከቶም ከዚህ በኋላ ከሀገሩ ለመስረቅ የሚያደባ ሊፈጠር ቀርቶ ሲያስበው ይሸማቀቃል" ብዬ ገምቼ ነበር:: ግና "መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል" የሚለው ብሂል ሲታወሰኝ የጠ/ሚ ዐቢይ ድካም አሳዘነኝ::

ዘረኛን እንጂ ልማደኛ ሌባን በምክር ማቆም የሚቸግር ይመስለኛል:: ሌባን ከተግባራዊ ተግሣጽ ወጪ ምክር አያስተምረውም:: ምንጩን እያደረቁ፣ ሲቻል የዘረፈውን ቀምቶ፣ ክብርና ማእረጉንም ገፍፎ ተገቢውን የሕግ ቅጣት አከናንቦ መቀጣጫ ማድረጉ ነው የሚያዋጣው::

የዚህችን ድሃ ሀገር ድህነት አባባሾች በየደረጃው ያሉ አመራሮች መሆናቸው ሲታሰብ ሀገሪቷ አስተምራ ሌባ በማፍራቷ "መች ይሆን ሰው አፍርታ ሌሎች ሀገሮች ከደረሱበት የምትደርሰው" የሚለው ምኞታችን ፍሬ አፍርቶ የምናይበት ቀን ይናፍቀናል::

"ሊቼንሳ" ካላቸው ሌቦች መለስ ብለን ገመናቸውን እንዲሸፍንላቸውና ትኩረት እንዲነሣላቸው ጭቁኖችን በጎጥ አቧድነው እንዲጫረሱ መሣርያ አቀባዮችን ስናይ የትናንት ቅኝ ገዢዎቻችን ተንኮል በ21ኛው ክፍለ ዘመን አፈሩን አራግፎ መነሣቱ ይበልጥ ያስጨንቀናል:: የጠባብ ብሔርተኝነት በሽታ ዛሬም የ21ኛው ክፍለ ዘመን አጀንዳ መሆኑ ያሳዝናል:: አጀንዳውንም ፖለቲከኞች ከፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚጠቀሙበት ሴራ እንደሆነ ጠ/ሚ ዐቢይ ነግረውናል:: የፖለቲካ ቁማርተኞች ሰዎችን በብሔር፣በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በድንበር፣ በሀገርና በኢኮኖሚ ደረጃ መዳድበው በልዩነት እንዲተያይና ራሱን የተለየ አድርጎ እንዲስል ሲያደርጉት ኖረዋል:: ሰዎችም ለጊዜያዊ ጥቅማቸው ዘለቄታዊ ጉዳቱን ባለመረዳት የሴረኞች ተባባሪ ይሆናሉ::

ከሰሞኑ በሀገራችን ተከሰቱ የተባሉት ግጭቶች በአንድ ጊዜ በብዙ ቦታ በፍጥነት እንዲዛመቱ መደረጉና የከፋ ጉዳት እንዲደርስ መደረጉ የፖለቲካ ቁማርተኞቹ ሕልውናቸውን ለማስጠበቅ የሕዝብ ደም ማፍሰስ ቅንጣት እንደማይረብሻቸው ማየታችን እንድናፍር አድርጎናል::

ኢትዮጵያዊ ለወገኑ የሚያስብና የሚሳሳ እንጂ፤ ለጥቅሙ ሕዝብን በማፋጀት አይታወቅም:: ስለሆነም የአንዳንድ ግለሰቦችን የክፋትና የተንኮል ተግባር የኢትዮጵያዊ መገለጫ አድርገን ልንወስድ አይገባም:: ዛሬ ጠ/ሚ ዐቢይ የኢትዮጵያውያንን የቆየ እሴት ለማስመለስ ሲነሣ በብጥብጥና በሁከት ሲያተርፍ የኖረ ሁሉ የሕዝቡን ባሕል አፍርሶ ወረቱን ለማሳደግ ቢጥር ሰሚ እንደማያገኝ ሊነገረው ይገባል::

በያዝነው ዓመት የመጀመርያ ወራት እጅግ አስጊ ድባብ ውስጥ እንደነበርን አይዘነጋም:: የዘርና የሃይማኖት ካርድ መዘዘው ሊያናችፉን ያሰፈሰፉ ጠላቶቻችን ጥቂት በማይባሉ የሀገራችን አካባቢዎች ፊሽካ በመንፋት የእልቂት ጨዋታውን ለማስጀመር ዳር ደርሰው ነበር:: የሳይንስ ምሑራን ሳይቀሩ ከዚህ ቀደም ሚናውን የማያጎሉትን ፈጣሪ ስሙን በመደጋገም፣ "እግዚአብሔር ነው ይህቺን ሀገር የታደጋት፣ አላህ ነው የደረሰላት" እስከማለት ደርሰው ነበር:: የለማ ቲም ከቲም ገዱ ጋር ሕብረት በመፍጠር የተንኮለኞችን ሴራ አክሽፈው ስናይ ተአምሩ በርግጥ ሁላችንንም አስደምሞን አልፏል:: ይህ የተንኮል ወጥመድም ዳግም የሚጠመድበት ሜዳ እንደሌለ ማሳየት ትናንት ተንኮሉን ያከሸፈው አመራር ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ድርሻ ሊሆን ይገባዋል::

ጉዳዩ ለሀገር ጥቅም ተብሎ ነው ቢባል እንኳን ወገን በወገኑ ላይ እጁን ማንሳቱ ሊታመን አይችልም:: የዘረኝነት መርዝ ከሃይማኖትም በመክፋቱ ቤንዚን አርከፍካፊ የመርዝ ብልቃጦች ከመተቸት ባለፈ የእጃቸውን የሚያገኙ ነበር የመሰለን:: የዘውጌ ብሔርተኝነት ሴራ በዓለም ላይ ለኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሲሉ ከተጋጩት በላይ የተደረገ ነው:: ሂትለር በአይሁዶች ላይ የወሰደው እርምጃ አንዱ ማሳያ ነው::

የማኅበረሰብ ለውጥ አራማጆች ነብዩ ሙሐመድ፣ ኔልሰን ማንዴላና ማህተመ ጋንዲ የዘረኞችን ቅስማቸውን በመስበር ዘመን ተሻጋሪ ሀሳብ አኑረው አልፈዋል:: በአንድ ወቅት ቢላልን አንድ የነቢዩ ባልደረባ አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚያሳምም የዘረኝነት ስድብ ይሰድበዋል:: በዚህ ስድብ ክፉኛ የተበሳጨው ቢላልም፣ የተባለውን ሳይቀንስ ሳይጨምር ለነቢዩ ሙሐመድ ይነግራቸዋል:: ነቢዩም ቢላል የባርያ ልጅ መባሉ ከንክኗቸው ተሳዳቢውን አስጠርተው "አንተ የመሀይምነት ዘመን አስተሳሰብ ዛሬም ከጭንቅላትህ አልወጣም?" ይሉታል:: ይህች ንግግር ይህንን ታላቅ ሰው በቃሉ እንዲሸማቀቅ አደረገችው:: ለሦስት ቀናትም ቢላል ቤት በር ላይ ተደፍቶ እንዲያድርና በእግሩ ጭንቅላቱን ካልረገጠው ይቅር እንዳለው እንደማይቆጥረው ነገረው:: ቢላልንም ምነው ያን ዕለት ለነቢዩ ባልነገርኳቸው እስከማለት አድርሶት ነበር:: "የተከበረውን ጭንቅላትህን አልረግጥም፤ ከልቤ ይቅር ብዬሃለሁ" በማለት እርቀ ሰላሙን አውርዶ ነበር::

ነብዩ ሙሐመድ ሰዎች ለሀገራቸው ክብር እንዲሰጡ ለስማቸው ተቀጽላ ሀገራቸውን ያደርጉ ነበር:: ለምሳሌ፡- ቢላል አልሀበሽ፣ ሰልማን አልፋሪሲ.... የመካ ሹማምንት በስተመጨረሻ እስልምናን ከተቀበሉ በኋላ የቀደመ ክብራቸውን ይዘው ለመኮፈስ ፈልገው ነበር:: ነቢዩ ግን ዘርና ተወላጅነት ሳይሆን የተግባር ልዕልና ነው ሰውን የሚያስከብረው በሚል ታላላቅ ክብርና ዝና አለን ከሚሉ ኩፍሶች ለቢላልና ለሰልማን ቅድሚያ ይሰጡ ነበር::

ኔልሰን ማንዴላ ዘረኝነትን በመዋጋት ብዙ መሥዋዕትነት ከፍለው እንደነበር የሚታወስ ነው:: ለ27 ዓመታት ታስረው ከወጡ በኋላ ግን ለሰፊው ሕዝባቸው ጥቅም ሲሉ ቁስላቸውን ውጠው፣ ብሶታቸውን አፍነው ሕዝባቸውን ነጻ አውጥተዋል:: እርቆ አስተዋይ የህዝብ አገልጋይ ፖለቲከኛ ለወገኑ እድገትና የወደፊት ራዕይ ብሶትና በደሉን ዋጥ ያደርጋል እንጂ፣ ከሕዝብ የዘረፈውን ለመብላት በሚል እንደሀገራችን ጠባብ ብሔርተኞች ከሕዝብ የዘረፈውን ለመቀራመት አንዱን ከሌላው በማጋጨት ኋላ ቀር ምኞቱን አያራምድም:: መሪ ለወገኑ መሥዋዕት ይሆናል እንጂ ለጥቅም ሕዝቡን አይማግድም::

የሰላም አባቱ ጋንዲ በአንድ ወቅት የትግሉን ሂደት የሚያደናቅፍ ሁኔታ አጋጠመው:: ሙስሊሞችና ሂንዱዎች በመጋጨት የጋንዲን ሀገር አቀፍ ትግል አደናቀፉ:: በዚህም ጋንዲ ሁለቱ እስኪታረቁ አልበላም፣ አልጠጣም፣ ቤቴም አልተኛም ብለው በረንዳቸው ላይ ይተኛሉ:: ሁለት ቀን፣ ሦስት ቀን አለፈ:: ከሀገር ጥቅም ውስጣዊ መቆረቋቆስን ያስቀደሙት ሂንዱዎችና ሙስሊሞች የሀገር "አይከኑ" ጋንዲ በነሱ ምክንያት ሊሞት መወሰኑ አስጨነቃቸው፤ እጅ ለእጅ በመያያዝም "ይኸው ታርቀናል፣ አብረን እንብላ፣ ቤትህም ግባ" በማለት የጋንዲን ሕይወት ታድገዋል::

መሪና ሕዝብ እንዲህ ሲተሳሰብ ሀገር ከእድገት ጫፍ ትደርሳለች:: ይህ ካልሆነ ዘላለም ድህነትን መርገም እንጂ አንድ እርምጃ ወደፊት መራመድ አይቻልም:: ይህን ልብ በማለት ሁላችንም ለኢትዮጵያ ልዕልና እጅ ለእጅ ተያይዘን በእድገት ጎዳና ልንጓዝ ይገባል::

ቸር እንሰንብት



ታምራት መርጊያ

# የአቶ መለስና የጠ/ሚ ዐቢይ የልማታዊ መንግሥት አስተሳሰብ ንጽጽሮች

ላለፉት 27 ዓመታት ሀገሪቱን በጠንካራ መዳፉ ሥር አስገብቶ ሲያስተዳድራት የቆየው ኢህአዴግ፤ ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ነበር ሀገሪቱን በልማታዊ መንግሥት መርህ (Developmental State path) እንደሚያስተዳድራት በይፋ ያሳወቀው።

ይሁን እንጂ ከቃላት ባለፈ የዚህን ንድፈ ሐሳብ ፍሬ ነገር ከወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊና ምናልባትም በጣት ከሚቆጠሩ የአገዛዙ ሹማምንቶች በዘለለ፥ በዉል የተረዱ የአገዛዙ ባለሥልጣናትና የቢሮክራሲው አካላት ነበሩ ብሎ መናገር እጅግ አዳጋች ነው።

ይህን አስመልክቶ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ፥ "ዳንዲ፡- የነጋሶ መንገድ" ባሉት መጽሐፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት፤ በቤተ መንግሥት ሕይወታቸው ይህንን ንድፈ ሐሳብ እንደመለስ ዜናዊ በአግባቡ የተረዳና መልሶ ማስረዳት የሚችል የአገዛዙ ሰው እንዳልገጠማቸው አመላክተዋል። በመሆኑም ይህ ጽንሰ ሐሳብ፣ በተለይም የአቶ መለስን ህልፈተ ሕይወት ተከትሎ በኢህአዴግና በሚመራው መንግሥት፣ እንዲሁም በጠቅላላው የህብረተሰብ ክፍል ዘንድ አሻሚ ከመሆን አልፎ ብዙ ጊዜ ብዥታን እየፈጠረና ለትግበራ አዳጋች ሆኖ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።


በዚህ መንስኤም፣ ከልማታዊ መንግሥት የሚጠበቁ፣ ለሀገር የሚበጁ በጎ እሳቤዎችና ባህርያት ውስጥ፦

- ብቃት ያለውና ከወገንተኝነት ነፃ የሆነ የቢሮክራሲ ሥርዓት መገንባት (capable and autonomous beurocratic system)፤
- ቁርጠኛ የፖለቲካ አመራር ( Commitment among political leadership)፤
- ብቃትን መሠረት ባደረገ ቅጥር የሚሾም የህዝብ አገልጋይ ሥርዓት መዘርጋት (Merit based civil service system)፤
- ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር (creating nationwide consensus)፤
- የመንግሥትና የንግድ ግንኙነት (state-business relation) ወዘተ…

እነዚህን የተመለከቱ ሐሳቦች ይጠበቁ የነበረ ቢሆንም፣ በተጨባጭ መሬት ላይ ወርደው መታየት ባለመቻላቸው ለበረቱና ለተበራከቱ ሕዝባዊ ምሬትና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ብሎም ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች ምንጭ



ጠ/ሚ አብይ አሕመድ



የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ

በመሆን፣ ሀገሪቱን እስከ መበተን ሊያደስር የሚችል ከፍተኛ ሀገራዊ አደጋ ደግነው መቆየታቸውም የሚዘነጋ ጉዳይ አይደለም። የሆነው ሆኖ፣ ምስጋና እንደነ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ፣ አቶ ለማ መገርሳ እና አቶ ገዱ አንዳርጋቸው አይነት የለውጥ አራማጅ ኢህአዴጋውያንን ላፈራው የህዝብ ትግል ይሁንና፣ በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎች ያለው ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሀገሪቱ ውስጥ አንፃራዊ ሰላምና የለውጥ ጭላንጭል ለመታየት ችሏል።

እንደሚታወቀው ልማታዊ መንግሥት (Developmental state) ወይም (hard state) በግርድፉ ሲተረጎም "መንግሥት መራሽ ሀገር አቀፍ የምጣኔ ሀብት እቅድ (state-led macroeconomic planning)" ማለት ነው።

የዚህ ፅንሰ ሐሳብ ወጣኒና አመንጪ ተደርጎ የሚነገርለት "ቻልመርስ ጆንሰን" የተሰኘ አሜሪካዊ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና፥ ቀድሞ በአሜሪካ የስለላ ተቋም በሆነው ሲ..አይ.ኤ ውስጥ አማካሪ የነበረ ሰው እንደሆነ ይነገራል።

ይህ ፅንሠ ሐሳብ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት አንስቶ እስከ 1970ዎቹ የዘለቀ የ20ኛው ክፍለ ዘመን ልማታዊ መንግሥት ሞዴል እና ከዚያ ቀጥሎ ካሉት ጊዜያት ጀምሮ ደግሞ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የልማታዊ መንግስት ሞዴል የተሰኙ ሁለት አይነት መልክና ምዕራፎች ያሉት ሲሆን፣ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ከ1952 ዓ.ም. ጀምሮ ቀድመው የተገበሩት ሀገራት የምስራቅ ኤዥያዎቹ ደቡብ ኮርያ፣ ጃፖን፣ ታይዋን እና ሆንግ ኮንግ እንደሆኑ ይነገራል።

እነዚህ ሀገራት በልማታዊ መንግሥት ፍልስፍና እና መርህ በመመራት እጅግ ከፍተኛ የሚባል እድገትና ብልፅግና ማስመዝገባቸው በስፋት ይገለጻል። በተጨማሪም ከሠላሣ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥም ደሀና ጎስቋላ የነበረውን ህዝባቸውን ኑሮ በበጎ መልኩ ቀይረው፣ ዛሬ በዓለም በኢኮኖሚያቸው ቁንጮ ከሚባሉት ሀገራት ተርታ መሰለፍ ችለዋል።

በዋነኝነት የልማታዊ መንግሥት ፍልስፍና አስተሳሰብ ማጠንጠኛና መነሻ ተደርጎ የሚወሰደው ሐሳብ፣ የገበያ ኃይሎች (the market forces) ተብለው የሚታወቁት "ፍላጎት እና አቅርቦት" (demand and supply) የአንድን ሀገር ሀብትና ▶

የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ፍትሐዊና ለሁሉም ዜጎች እኩል ተደራሽ በሆነ መልኩ ማዳረስ አይችሉም የሚል ሲሆን፤ ይህንን ክፍተት ለመሙላትና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ መንግሥት የግድ በገበያ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ በመንቀሣቀስ ዋና ዋና የሆኑና የተመረጡ የንግድ ተግባራትን በማካሄድ ፍትሐዊ የአቅርቦት ተደራሽነትና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደሚገባው ይመክራል፡፡

እንደሚታወቀው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ በሚከተሉ በተለይም ኒዎሊበራል በሚባሉት የምዕራቡ ዓለም ሀገራት ውስጥ መንግሥት በገበያ እንቅስቃሴ ውስጥ ምንም አይነት ሚና አይኖረውም፡፡ ከዚህ ባሻገርም መንግሥት ፈፅሞ በገበያ እንቅስቃሴ ውስጥ ጣልቃ አይገባም፡፡ በነዚህ ሀገራት ውስጥ በዋናነት የመንግሥት ሚና የሚሆነው፣ እንደ ቀረጥ መሠብሠብ፣ የሀገርን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ፣ ሕግ የማስከበርና ፖሊሲ የማውጣት ወዘተ... ተግባራት ሲሆኑ፤ ገበያው የሚመራው ራሱን ችሎ በፍላጎት እና አቅርቦት መጣጣም ምክንያት (demand and supply factors) ብቻ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በልማታዊ መንግሥት መስመር መጓዝ አዋጭ ነው ብሎ ያመነውና በቀድሞው ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የኢትዮጵያ መንገስት፥ ይህን አስተሳሰብ በመላው መንግስታዊና የፖርቲ መዋቅሮቹ ውስጥ ገዢ የፓለቲካና የኢኮኖሚ እሳቤው አድርጎታል፡፡

ይሁንና፣ ንድፈ ሐሳቡን በውል የተረዱትን የአቶ መለስ ዜናዊን ህልፈት ተከትሎ፤ ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት፤ አስተሳሰቡን ለመተግበርም ሆነ ለማስቀጠል ድህረ መለስ ዜናዊ ያሉት ጊዜያት እጅጉን አዳጋች ሆኖበት መቆየቱ የተስተዋለ ጉዳይ ነው፡፡

ሰሞኑን ስብሰባ ያካሄደው የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ከዚህ አስተሳሰብ ወጣ ያለ በሚመስል መልኩ፣ በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉ በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙትም ሆነ በግንባታ ላይ ያሉ የባቡር፣ የስኳር ልማት፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የሆቴልና የተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በአክሲዮን ሽያጭ ወደ ግል ዘርፍ እንዲተላለፉ (privatization)፤ እንዲሁም ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች እና የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ድርጅት ትልቁን የአክስዮን ድርሻ መንግሥት ይዞ ቀሪው አክሲዮን ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብቶች እንዲተላለፍ መወሰኑን ማሳወቁ በከፍተኛ ደረጃ መነጋገሪያና ትኩረትን የሳበ ጉዳይ ሆኗል፡፡

በርግጥ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ባወጣው መግለጫ አፈፃፀሙ የልማታዊ መንግሥት ባህርያትን በሚያስጠበቅ ጥብቅ ዲሲፒሊን ተግባራዊ እንደሚደረግ ቢገልጽም፤ ብዙዎች ግን ይህ ውሳኔ ያለተለመደና ያልተጠበቀ እንደሆነ በመግለጽ ጉዳዩን ከፖሊሲና ከርዕዮተ ዓለማዊ ለውጥ ጋር እያያዙ ሲገልጹ ተስተውሏል፡፡

ይህን አስመልክቶ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ሰኔ 11፣ ቀን 2010 ዓ.ም. ለፓርላማ አባላት ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስና ማብራሪያ ላይ እንደገለጹት፣ ይህ ጉዳይ "የኢኮኖሚክስ መሰረታዊ ሐሳብ (Fundamental Economic Concept) እንጂ ከርዕዮተ ዓለምም ይሁን ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑን አፅንዖት በመስጠት ተናግረዋል፡፡

**አቶ መለስ በመንግሥት እጅና ሞኖፖሊ መቆየት እንዳለባቸው በጽኑ የሚያምኗቸው እንደ ቴሌኮም፣ አየር መንገድና የመብራት አገልግሎቶች ባሉት ላይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ የተለየ መሆኑን መረዳት ይቻላል**

የሆነው ሆኖ ጠ/ሚ ዐቢይ አህመድ፣ የልማታዊ መንግሥትን ሐሳብ ያብራሩበት መንገድና ያላቸው አረዳድ፥ ከቀዳሚያቸው ከአቶ መለስ ዜናዊ አንጻር ሲታይ በመሰረታዊነት በጽንሰ ሐሳባዊ ግብ ልዩነት እንዳላቸው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚህ ረገድ የሁለቱን መሪዎች የልማታዊ መንግሥት ትንተና በአጭሩ በመቃኘት የልዩነቶቻቸውን ምንጭ ለመመልከት እንሞክር፡፡

በአንድ ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ተጋብዘው "Dead Ends and New Beginnings" በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ጥናታዊ ጽሑፍ ሲያብራሩ እንደገለፁት፣"ኒዮሊበራሊዝም በአፍሪካ፣ የጨነገፈ ወይም በተግባር የወደቀ ንድፈ ሐሳብ ነው፤ ስለሆነም የንድፈ ሐሳብ ወይም የሞዴል ለውጥ ያስፈልጋል" ("...The neo-liberal paradigm failed in Africa, thus a paradigm shift is needed...") በማለት ነበር የኒዮሊበራሉ ዓለም ካፒታሊስታዊ ሥርዓት መዳረሻ የሆነውን የኒዮሊበራሊዝም ሐሳብ የተቹት፡፡

በአንጻሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ በልማታዊ መንግሥትና በኒዮሊበራሊዝም መካከል ያካሂዱ እንጂ የግብ ልዩነት እንደሌለ በማስቀመጥ ከአቶ መለስ ይልቅ ለዘብ ያለ አመለካከት በኒዮሊበራሊዝም አስተሳሰብ ላይ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡

በሌላ በኩል አቶ መለስ ዜናዊ አጥብቀዉ የሚተቹት የኒዮሊበራሊዝምን ንድፈ ሐሳብ ሲተነትኑ፣ የዋሽንግተን ስምምነት (Washington consensuses) እና የገበያ አክራሪነት (Market fundamentalism) በሚሉ ተለዋጭ ስያሜዎች ይጠሩታል፡፡ የዚህ ንድፈ ሐሳብ ተከታዮች እምነት ገበያ የመጨረሻው ዳኛ ነው፤ የመንግሥት በገበያ ውስጥ ጣልቃ መግባት የገበያን ቅልጥፍና ይጎዳል፤ ለመንግሥታዊ ሙስናም በር ከፋች በመሆን የገበያ ምስቅልቅል እና የኪራይ ሰብሳቢነት ባህርይን (Rent seeking behavior) ይፈጥራል ከሚል አመክንዮአዊ መሰረት መነሻነት፣ መንግሥት ሕግ ከማስከበር አልፎ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ፈፅሞ ጣልቃ ገብ መሆን እንደሌለበት ይመክራሉ፡፡

አቶ መለስ ግን ገበያውና ባለሐብቶች የሚጫወቱት የማይተካ ሚና እንዳለ ሁሉ፣ መንግሥትም በገበያ ውስጥ ድርሻ ሊኖረው እንደሚገባ አጽንዖት ሰጥተው ያስቀምጣሉ፡፡ በተለይም የገበያ ጉድለት ወይም "Market failure" በሚኖርበት ወቅት ገበያው ራሱን ችሎ እነዚህን ጉድለቶች መሙላት ስለማይችል፤ ይህንን ጉድለት ሊሞላ የሚችለውም ሆነ መሸፈን ያለበት መንግሥት እንደሆነ አበክረው ይከራከራሉ፡፡ በመሆኑም የልማታዊ መንግሥት ንድፈ ሐሳብ እንደሚመክረው መንግሥት በተወሰነና በተመረጠ አኳኋን የገበያ ጉድለት የሚያጋጥማቸው የኢኮኖሚ ክፍሎች ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደሚኖርበትም የአቶ መለስ ጽኑ እምነት ነው፡፡

በርግጥ አቶ መለስ በልማታዊ መንግሥት አሠራር እድገትና ልማትን ከማምጣት ባለፈ ምን ያህል ርቀትና እስከመቼ መጓዝ እንደሚቻል ያስቀመጡትን የመጨረሻ ግብ (End goal) ባይገልፁም፣ ከዚህ መነሻ በየትኛውም ኢኮኖሚ ውስጥ እንደሚያጋጥም የሚያምኑት የገበያ ጉድለት (Market Failure) ያለመንግሥት ጣልቃ ገብነት መሙላት ከቶውንም ሊታሰብ አይችልም የሚል ጠንካራ እምነት እንዳላቸው ተሳቢ በማድረግ፣ ይህንን ጣልቃ ገብነት የሚፈቅደውን የልማታዊ መንግሥት ንድፈ ሐሳብ በመከተል የሚመጣን የልማትና የእድገት ውጤት እንደመጨረሻ ግብ እንደሚወስዱት በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አቶ መለስ ሐሳባቸውን ለማጠናከር ያቀረቡት የምስራቅ ኤዥያ ሀገራትን አስተማማኝና ያልተቋረጠ እድገት፤ ከኒዮሊበራሊዝም ተከታይ ሀገራት ከገጠማቸው የኢኮኖሚ ውድቀት የሚለውን ንጻሬ ስንመለከት፤ ሰውየው የልማታዊ መንግሥትን መስመር እንደ መጨረሻ ግብ አድርገው እንደሚወስዱት በጉልህ ሊያሳይ የሚችል ነው፡፡

በአንጻሩ በንድፈ ሐሳባዊ ትንተና ደረጃ እምብዛም የተለየ ሐሳብ ያላቸው የማይመስሉት ጠቅላይ ሚነስትር ዐቢይ አህመድ፣ በግብ ደረጃ ግን ከአቶ መለስ የተለዩ መሆናቸውን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ የልማታዊ መንግሥትን ርዕዮተ ዓለማዊና ፖለቲካዊ ትንተና አቆይተን ስንመለከት፣ በኢኮኖሚያዊ ምልከታቸው እንኳን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የልማታዊ መንግሥትን ፍልስፍና የሚቀበሉት እንደ ድልድይና መሻገሪያ እንጂ እንደ መጨረሻ ግብ እንዳልሆነ ሰኔ 11/2010 ዓ.ም ለተወካዮች ምክር ቤት ያቀረቡት ማብራሪያ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም አቶ መለስ በመንግሥት እጅና ሞኖፖሊ መቆየት እንዳለባቸው በጽኑ የሚያምኗቸው እንደ ቴሌኮም፣ አየር መንገድና የመብራት አገልግሎቶች ባሉት ላይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ የተለየ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ከአቶ መለስ ይልቅ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለሊበራሉ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የቀረበ አመለካከት ያላቸው መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ የትኛው አመለካከት ለአገር ይበጃል የሚለውን ለመደምደም ሰፊ ጥናትና ትንተና የሚጠይቅ መሆኑ ባያጠያይቅም፣ እዚህ ላይ ደፍሮ መናገር የሚቻለው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይና እርሳቸው የሚመሩት መንግሥት የአቶ መለስን ሌጋሲ የሚያስቀጥል ሳይሆን፤ በአዲስ የኢኮኖሚ አቀራረብ የሚጓዝ መሆኑን ነው፡፡



# “ሥርዓቱን ፍርክስክሱን ያወጣው ቄሮ ነው”

## “ጠ/ሚ ዐቢይ ጽፍረትና ፍጥነት ያለው ሰው ነው”

### አክቲቪስት ጃዋር መሐመድ (ከአሜሪካ)

በተስፋ አግዮን

**ጃዋር መሐመድ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በተለይም በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው ነው፡፡ ወጣቱ አክቲቪስት ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ውስጥ ወጥ በሆነ ሁኔታ የቀጠለውንና ከፍተኛ መሥዋእትነት የተከፈለበትን የኦሮሚያ ክልል የለውጥ እንቅስቃሴ በዋነኝነት መርቷል፡፡ ቄሮዎች ገንነው እንዲወጡና የትግል ስልታቸው ግቡን እንዲመታ የስትራቴጂክ አማካሪ በመሆን አመፁ ከዳር ዳር እንዲቀጣጠል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በወቅታዊ የሀገራችን ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ ወደ አሜሪካ ስልክ በመደወል አነጋግሮታል፡፡**

***ግዮን፡- ቆይታችንን ከሀገር ከወጣህበት ጊዜ ብንጀምር፤ መቼና እንዴት ነበር ከኢትዮጵያ የወጣኸው?***

ጃዋር፡- ከሀገር ከወጣሁ ቆየሁ፡፡ እ.ኤ.አ. በ2003 በእኛ 1995 ዓ.ም. አሥረኛ ክፍልን ጨርሼ አስራ አንደኛ ክፍልን እየተማርኩ ስኮላርሽፕ አግኝቼ ነው በሰዓቱ ወደ ሲንጋፖር የሄድሁት፡፡

***ግዮን፡- ሲንጋፖር በቀጥታ እንደሄድህ ወደ ትምህርት ዓለም ነው የገባኸው?***

ጃዋር፡- አካሄዴ ለትምህርት በመሆኑ ሁለት ዓመት እዚያ ቆየሁ፤ በኋላ በቀጥታ ወደአሜሪካ በመጓዝ ኑሮዬን በዚያ ካደረግሁ ሰነበትሁ፡፡

***ግዮን፡- ያን ጊዜ ከወጣህ በኋላ ወደሀገር ቤት ተመልሰህ መጥተህ ታውቃለህ?***

ጃዋር፡- ብዙ ጊዜ መጥቻለሁ፡፡ ሲንጋፖር እንደጨረስሁ ወደአሜሪካ ከመምጣቴ በፊት ለሁለት ወር ኢትዮጵያ ነበርሁ፣ ከዚያ በኋላ የመጀመሪያ ዲግሪዬን እስክጨርስ ድረስ በየዓመቱ ወደ ሀገር ቤት እመላለስ ነበር፡፡ ክረምት ክረምት ሪሰርች እዚያ ነበር የምሠራው፤ በኋላ ላይ ነገሮች ከረር እያሉ እኔና የኢትዮጵያ መንግሥት መፋጠጥ ስንጀምር እዚሁ መቅረት መጣ፡፡

***ግዮን፡- ለመጨረሻ ጊዜ ኢትዮጵያ የመጣኸው መቼ ነው?***

ጃዋር፡- እ.ኤ.አ. በ2008 ዓ.ም. ነው፡፡ ►

**ግዮን፡- ኑሮህን በአሜሪካ ካደረግህ በኋላ ባለህ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የትኛውን ፓርቲ ነው የተቀላቀልከው?**

ጃዋር፡- የማንም ፓርቲ አባል ሆኜ አላውቅም፤ አይደለሁምም:: ወደፊትም የየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል አልሆንም::

**ግዮን፡- እስኪ ስለግል ሕይወትህ እናውራ፤ ትዳር የመሰረትከው መቼ ነው?**

ጃዋር፡- ትዳር የመሠረትሁት እ.ኤ.አ. 2009 ላይ ነው:: አሁን ዘጠኝ ዓመት ሆነው:: እንደ ቀልድ ጊዜው ነጎደ:: ባለቤቴ ኢፋሴ ገመዳ ትባላለች:: አንድ ልጅም አፍርተናል::

**ግዮን፡- ለምንድን ነው የኦሮሞ ብሔር መብት ተሟጋች ብቻ የሆንከው?**

ጃዋር፡- የኦሮሞ ብቻ አይደለሁም:: በርግጥ በቅድሚያ እዚያ ላይ ነው የሠራሁት:: ይህ የሆነበት ምክንያት እኔ ያደግኩበት አካባቢ ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ ጭቆና ይደረግበት ነበር፤ ከልጅነቴ አንስቶም ይህን በደል ሲፈፀም ሳይና ስሰማ ነው የኖርሁት:: በዚያ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የመብት ተጋድሎ ተደርጐበታል::

አብዛኛዎቹ የኦነግ አመራሮችና የኦነግ ኮማንደሮች ከእኛ አካባቢ የወጡ ናቸው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ከልጅነቴ ጀምሮ የኦነግ ወታደሮችን አውቃቸዋለሁ፤ ከእነሱ ሥር ሆኜ ፖለቲካን ተምሬያለሁ:: ከልጅነቴ አንስቶ ቅርጽ አስይዘውኛል:: ግን የኦሮሞን ሕዝብ ትግል ብቻ አይደለም:: ለምሳሌ ትዝ ካለህ የሙስሊሞች እንቅስቃሴ ሲካሄድ ስትራቴጂክ አድቫይዘር ነበርሁ:: ሠላማዊ ትግል እንዲያካሂዱ ብዙ ነገር አማክራቸው ነበር:: ያ የሙስሊሞች ትግል ከመንገድ ወጥቶ ወደወታደራዊ ፍጥጫና ሀገር ሊጐዳ ወደሚችል ነገር እንዳይሄድ ንቅናቄው በሠላማዊ ትግል ብቻ ላይ እንዲሆን በማድረጉ ረገድ ሚናዬ ከፍተኛ ነበር:: የተማርሁትም ያጠናሁትም ስለሆነ::

ሙስሊሞች ደግሞ ኦሮሞዎች ብቻ አይደሉም፤ ከሁሉም ብሔረሰብ የሚውጣጡ ናቸው:: ይህ ብቻ አይደለም በኢንቫይሮመንትና በተለያዩ ጉዳዮች ላይም አስገነዝባለሁ፣ እናገራለሁ:: ሆኖም ግን የኦሮምያን ጉዳይ መፍታት ማለት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ችግር መፍታት ማለት ነው:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ ቀውስ ከ1950ዎቹ ጀምሮ የኤርትራ ችግርና የኦሮሚያ ችግር ነው:: የሁለቱን ጉዳይ አግባብ ባለው መልኩ መፍታት ማለት ለሌሎች ብሔሮችም መፍትሔ ማምጣት ነው:: አንድ ምሳሌ ላንሳልህ:: የኦሮሞ ሕዝብ ሲታገልበት ከነበረው ነገር አንዱ በራሱ ቋንቋ የመጠቀም መብት ነው:: ይህንን መብት በ1991 ሲጐናፀፍ የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ አይደለም በራሱ ቋንቋ መናገርን የተጎናፀፈው:: ወላይታው፣ ሲዳማው፣ ሐረሪው፣ አፋሩ፣ ትግሬው የዕድሉ ተጠቃሚ ነው የሆነው:: ኦሮሞ ትልቅ እንደመሆኑ መጠን በመንግሥት ላይ የሚያደርሰው በትር ከፍተኛ ስለሆነ መንግሥት ተዳክሞ እጅ በሰጠ ቁጥር ለኦሮሞ ሳይሆን ለሁሉም እየተረፈ ነው::

**ግዮን፡- ይህ ለሌላው ብሔር የተትረፈረፈው ፖለቲካዊ ድል ምን አይነት ነው?**

ጃዋር፡- ላለፉት አራት ዓመታት እኔ ባደረግሁት እንቅስቃሴ እንኳን ነገሮች ከተለኩ እኔን የሚተቹኝ ሰዎች ዛሬ የውጤቱ ተጠቃሚ ናቸው:: ከእኔ በተቃራኒ የሆኑና ከእኛ በጣም የተለየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች የኦሮሞ ወጣቶች ባደረጉት ትግል ከእስር ቤት ወጥተዋል:: ስለዚህ የትግሉ ውጤት ሁሌም ሌሎችን የሚጠቅም ስለሆነ ኦሮሞን ያማከለ ትግል እናድርግ:: ኦሮሞ ብቻውን የሚጠቀመው ልማት አይኖርም፣ ኦሮሞ ብቻውን የሚጠቀመው ነፃነት አይኖርም፣ ኦሮሞ ብቻውን የሚጠቀመው ሠላም አይኖርም::

የኦሮሞ ሕዝብ የሚታገልላቸው እነዚህ ሦስት ነገሮች ብቻውን የሚጠቀማቸው ሳይሆኑ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጐት ጋር የተቆራኙ ናቸው:: እኔ ራሴን የማየው እንደ ኦሮሞ ሕዝብ ታጋይ ቢሆንም የእኔም ሆነ የሌሎች ኦሮሞ ታጋዮች ውጤት ግን ለሁሉም ሕዝብ በረከት እንደሆነ ነው የሚገባኝ::

**ግዮን፡- ሙሉ ለሙሉ ወደፖለቲካው ዓለም በመግባት ሠላማዊ ትግል ለማድረግ የወሰንከው መቼ ነው?**

ጃዋር፡- ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ለፖለቲካው ዝንባሌ ነበረኝ፤ ት/ቤት እያለን ልጆች አሰልፍ ነበር:: በዚያ ዕድሜዬ የፖለቲካ አክቲቪስት ነበርኩ:: የሚገርምህ ያኔ የሳይንስ ተማሪ ነበርኩ፣ በኋላ ግን ወደ ሶሻል ሳይንስ በመግባት ፖለቲካውን ማጥናትና በዚህ ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊ ነው ብዬ አመንሁኝ:: በተለይ አሰላና አዳማ ከመጣሁ በኋላ ያየኋቸው ነገሮች፤ ሥርዓቱ ለኦሮሞ ሕዝብ የነበረው አመለካከት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የነበሩ ፀረ ኦሮሞ የሆኑ አመለካከቶች፣ በኦሮሞዎች በኩል በራሳቸው ላይ የነበረውን ኮንፊደንስ የማጣት ሁኔታ ስመለከት ይህ ነገር መለወጥ እንዳለበት ተገነዘብሁ::

ለኦሮሞ ሕዝብም ሆነ ለአካባቢው ይህ ሁኔታ አደገኛ ነው፤ ጭቆናው መገልበጥ፣ ፎቢያው መሰበር አለበት፤ የኦሮሞ ሕዝብ እንደማንኛውም ሕዝብ ራሱን አስከብሮ ሌላውን አክብሮ መኖር አለበት:: ለዚህ ደግሞ ያለው ሥርዓት ባህርዩ መለወጥ አለበት:: ወይ ሥርዓቱ መፈንገል አለበት፣ ወይ ሥርዓቱ ወደትክክለኛው መንገድ ተመልሶ የኦሮሞ ሕዝቦችን መብት እያከበረ እንዲሄድ መደረግ አለበት የሚል ድምዳሜ ላይ የደረስሁት አሥረኛ ክፍል እያለሁ ነው::

**ግዮን፡- በዚያ ዕድሜ ላይ ሆነህ በትክክለኛው የፖለቲካ መንገድ ነገሮችን መጋፈጥ አይከብድም?**

ጃዋር፡- ፈፅሞ አይከብድም:: የምታየው ግልፅ የሆነ ጭቆና አለ:: አሥረኛ ክፍል ሆኜ ወደፖለቲካ ውስጥ ብገባም በቀጣዩ ዓመት ወደ ሲንጋፖር መሄዴ የፖለቲካ ዕውቀቴን የበለጠ አሳድጐታል:: እንደ ሲሪላንካና ማሌዢያ ያሉ ከፍተኛ የሆነ የብሔር ግጭት የተካሄደባቸው ሀገራት የብሔር ግጭቶችን አስወግደው፣ ሕብረ ብሔር በመሆን የተረጋጋ የፖለቲካ ሲስተም ማቋቋም ችለዋል:: እንደሲንጋፖር ያሉ የአንድ ብሔር የበላይነት ካለባቸው ነገር ግን የአናሳ ብሔሮች መብት ተከብሮ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት በተገኘባቸው፤ እንዲሁም እንደቻይና አምባገነን ሆነው ኢኮኖሚያቸውን ባበለፀጉ ሀገሮች እየዞርሁ ከአመራሮቻቸውና ከምሁራኖቻቸው ጋር ስወያይ ስለነበረ ያንን ያካበትሁትን ልምድ ወደሥራ መለወጥ አለብኝ በሚል እምነት ነው የገባሁት::

**ግዮን፡- OMN (ኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ) መቼ ነበር የተቋቋመው? የአንተ ሓላፊነትስ ምንድን ነው?**

ጃዋር፡- አልጀዚራ ላይ "ኦሮሞ ፈርስት" ካልሁ በኋላ የተነሣውን ቁጣ ወደአድቮንቴጅ ለወጥነውና የሚወረወረውን ድንጋይ ሰብስበን ኦ.ኤም.ኤንን አቋቋምንበት:: ከዚያ በፊት እ.ኤ.አ. 2012 አካባቢ የኦሮሞ ሕዝብ ሚዲያ ሊኖረው ይገባል፣ በመንግሥት በኩል የሚዲያ የበላይነት ስላለ ትግሉ አድቫንቴጅ ቢኖረውም ጠንካራ የሆነ ሚዲያ መቋቋም አለበት የሚል አቋም ነበረን፤ ከጓደኞቼ ጋራ:: በዚያ በ"ኦሮሞ ፈርስት" አድቫንቴጅ መነሻነት በዓለም ላይ ከፍተኛ ዘመቻ በማካሄድ ገንዘብ አሰባስበን በማርች 1፣ 2014 በኦ.ኤም.ኤን አማካይነት የኦሮሚያን አየር ከወያኔ ቁጥጥር ነፃ አወጣነው::

**ግዮን፡- በኦሮሞ ወጣቶች ዘንድ ጃዋር መሐመድ ከፍተኛ ተቀባይነት አለው ይባላል፤ ለምን ይመስልሃል?**

ጃዋር፡- ብዙም በዕድሜ የማልበልጣቸው ወንድማቸው ነኝ፤ ከዛም አልፎ እነሱ እንደሚሉት ጐል ኪፐራቸው ነኝ:: እነሱ ለሚያደርጉት ትግል የእኔ ሚና ሁለት ነው:: አንዱ በእኛ ሚዲያም ሆነ በሌሎች ሚዲያዎች ላይ ወጥቶ እነሱ የሚያገኙት ሥራ አድማጭ እንዲያገኝ፣ እንቅስቃሴያቸው በጠላት ላይ የሥነ-ልቦና ጫና እንዲፈጥር በደጋፊ ሕዝብ ላይ መበረታታትንና ድጋፍን እንዲጨምር፣ በሦስተኛ ወገን ማለትም በኢንተርናሽናል ኮሚኒቲው ደግሞ ርህራሔ እንዲያገኙ ብዙ የሽፋን ተኩስ በማድረግ እረዳቸዋለሁ::

በሁለተኛ ደረጃ ያጠናሁትም ፖለቲክስ ስለሆነ፣ ሠላማዊ ትግል ላይ የስትራቴጂ ምክር እሰጣቸዋለሁ:: ባለፉት አራት ዓመታት ምንም እንኳን ከእነሱ ጋር ባልሠራና መንገድ ውስጥ ባልኖርም ሌት ተቀን አብሬያቸው ስሠራ ስለነበረ፤ በተለይ ደግሞ በፈለጉት ጊዜ ስለሚያገኙኝ እንደአንድ የፖለቲካ መሪ ሳይሆን ከእነሱ ጋር እንዳለ አንድ ወታደር አድርገው ስለሚያዩኝ ነው የበለጠ ያቀራረበን::

እንደፈለጋቸው ሊናገሩኝና ሊቆጡኝ ይችላሉ:: ሀሳባቸውንና ውስጣቸውን በደንብ እረዳዋለሁ:: እኔም የምነግራቸውና የማሳያቸው መንገድ የሚጠቅማቸውን ስለሆነ ነው መግባባትና መደማመጡ ሊኖር የቻለው::

**ግዮን፡- የቄሮዎች እንቅስቃሴ ጎልቶ የወጣው መቼ ነበር? ስያሜውንስ ማነው የሰጣቸው?**

ጃዋር፡- ቄሮ ከተቋቋመ ቆይቷል:: በ1969 እ.ኤ.አ. ሜጫ ቱለማ ከተዘጋና የባሌው እንቅስቃሴ አደጋ ላይ ከወደቀ በኋላ የትጥቅ ትግልን በተቀናጀ መልኩ ለማቋቋም ሲሉ በአረብ ሀገራትና (ኤደን) በተለያዩ ቦታዎች የነበሩ የኦሮሞ ወጣቶች ተደራጅተው፣ 36 የሚሆኑትም ሠልጥነው፣ ታጥቀው ሀገር ሊገቡ ሲሉ በሶማሌ መንግሥት ተይዘው እስር ቤት ታሰሩ:: እነዚያ የታሰሩት 36 ወጣቶች ቄሮ ገነማ (የጠዋቱ ቄሮ) ይባሉ ነበረ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቄሮ በሚለው ሥር ሲካሄድ የነበረው በወጣቶች የሚደረገው እንቅስቃሴ ገንኖ የወጣው ባለፉት ሦስት አራት ዓመታት ውስጥ ነው:: በተለይ ደግሞ ድል እያደረጉ በመጡ ቁጥር የስትራቴጂ የበላይነት በሥርአቱ ላይ እያገኙ በመምጣታቸው፤ ያላቸው የትግል ዲሲፕሊን በጣም የላቀ በመሆኑና የሀገሪቱ ሁለተኛ መንግሥት ሆነው ከመምጣታቸው ጋር በተያያዘ ባለፉት ዓመታት ጐልተው ወጡ እንጂ ቄሮ ከአርባ ዓመት በፊት የኦሮሞ ሕዝብ ትግል ሲወለድ የተወለደ ስያሜ ነው::

**ግዮን፡- ለቄሮዎች "እንዲህ አድርጉ ይህንን ፈፅሙ እያልክ መመሪያ የምትሰጣቸው አንተ እንደሆንህ ይነገራል፤**

ጃዋር፡- እኔ መመሪያ አይደለም የምሰጣቸው፤ የቄሮ አደረጃጀት ሆሪዞንታል አደረጃጀት ነው፤ ከላይ ሊ/መንበሩና ሥራ አስፈፃሚው የሚያደርጉት ሳይሆን በየዞኑ፣ በየፕሮፌሽኑ በተለያየ መልኩ የተደራጀ እንቅስቃሴ ነው::

አቀናጆች አሉት:: እኛ ደግሞ በሞራልና በተለያየ መልኩ ምክር እንሰጣቸዋለን:: አንዳንዴ መንገድ እናሳያቸዋለን::

በህቡዕ የተደራጀ እንቅስቃሴ እንደመሆኑ የጋራ ውሳኔያቸውን እኔ ነኝ በይፋ የማሳውቅላቸው፤ ለምሳሌ ዓድማው ይህን ያህል ቀን ይቆይ፣ በዚህ ቀን እንዲህ አይነት ዕርምጃ እንወስዳለን የሚሉትን ዝግጅት እኔ ነኝ የማስተዋውቅላቸው፤ እኔ በፌስ ቡክ የምለጥፈውን እንደመመሪያ ይጠቀሙታል:: ግን የዚያ መመሪያ ምንጩ እኔ ሳልሆን እነሱ ራሳቸው ናቸው:: የስትራቴጂውና የታክቲኩ ምንጭ እንዲሁም የዝግጅቱ ሙሉ አስተባባሪዎች ቄሮዎች ናቸው::

ሀሳባቸውን አቀናጅተው ሥራ ላይ ማዋል ስለሚቸግራቸው ወደእኔ ይልካሉ፤ እኔ ደግሞ ከየቦታው የሚመጣውን ከእነሱ ጋር ተወያይቼ በመግለጫና በመመሪያ መልኩ አወጣዋለሁ:: ያ ወደ ሥራ ይገባል:: የእኔ ሐላፊነት ይሄ ነው እንጂ ከላይ ቁጭ ብዬ ያንን ስበሩ፤ ይህንን ፍለጡ የሚል ትዕዛዝ አልሰጥም::

**ግዮን፡- በአጠቃላይ የቄሮ እንቅስቃሴና አደረጃጀት እንዴት ይገለፃል?**

**ጃዋር**፡- ቄሮ እኮ ሶሻል ሙቭመንት ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት አራት ዓመታት ሠው ቄሮን ለመረዳት የሚሞክረው ከዚህ በፊት በነበሩ የአደረጃጀት ዘይቤዎች ነው:: ቄሮ በዚያ መልክ ሳይሆን ሶሻል ሙቭመንትና የአግድሞሽ እንቅስቃሴ ነው:: በወታደርም፣ በፖሊስም፣ በህክምናም ይሁን በተለያየ ሙያ ውስጥ ተደራጅተው ሆኖም ግን የአመራር ብቃት ያላቸው ሰዎች የሚያንቀሳቅሱት ትግል ነው::

ገዢው ፓርቲ ከላይ ወደታች ነው የተደራጀው፤ ቄሮ ግን አግድሞሽ ስለሆነ የሥርዓቱን ቅልጥም ለመስበር የሚያስችል አደረጃጀት ሞዴል ነው:: ስለዚህ ሊቀ መንበር፣ ምክትል ምናምን የሚባል ድርጅታዊ ነገር የለውም:: ኮርድኔተር ወይም አቀናጅ የምንላቸው ሰዎች ናቸው ከመሃሉ ያሉት::

**ግዮን፡- በፌስ ቡክ በምታወጣቸው መግለጫዎች አማካይነት በርካታ አድማዎች፣ ሰላማዊ ትግሎች ተካሄደዋል፤ በትክክል ግቡን በመምታት ውጤታማ ነበር የምትለው ግን የትኛውን ነው?**

**ጃዋር**፡- በየጊዜው የትግል ስልታችንን እየለዋወጥን ነው የመጣነውና በጣም ትልቅ ናቸው ብዬ ከማስባቸው አንዱ በ2016 በኦሮሚያ ውስጥ ከሦስት መቶ በሚበልጡ በተለያዩ ከተሞች በአንድ ቀንና በአንድ ሠዓት የተደረገው ሠልፍ ከፍተኛ መሥዋእነት ቢያስከፍልም ወሳኝ ነበር:: ከዚያ ቀን በኋላ ሥርዓቱ ወደኋላ መመለስ አይችልም ነበር::

ከዚያ በፊት ትንሽ ጥርጣሬ ነበር፤ አመራር የለውም፤ ዝም ብሎ የተበታተነ ነገር ነው የነበረው:: የምሥራቁ ሲነሣ የምዕራቡ ይተኛል፤ የግል ፕሮፓጋንዳ በሥርዓቱ ይስተጋባ ነበር:: በዚያ ቀን ማሣየት የቻልነው በአንድ ቀንና በአንድ ሠዓት፣ በተመሳሳይ መፈክር ሕዝባችን ሊነሣ እንደሚችልና ሀገሪቱን ፀጥ ማድረግ እንደሚችል ነው::

ሁለተኛው እሬቻ ላይ የተደረገው ነው፤ በእሬቻ ላይ ቅድመ ዝግጅቶች ነበሩ፤ ግን ሥርዓቱ ንዴት ስለነበረውና የመጣው ሕዝብም ከፍተኛ ከመሆኑ ባሻገር በዓሉ የተቃወሞ ስለነበረ ሥርዓቱ ያንን መገልበጥ ፈለገና በመቶዎች የሚቆጠሩ ወንድም እህቶቻችንን ጨፈጨፈ …ያ ቀን ወሳኝ ነበር:: ከዚያ የጥፋት ቀን በኋላ አምስት የቁጣ ቀናት በማለት የታወጀው አዋጅ ቀላል አልነበረም::

**ግዮን፡- አምስቱ የቁጣ ቀናት ምን አይነት ገፅታ ነበራቸው?**

**ጃዋር**፡- የሥርዓቱን የመጨቆን አቅም ድምጥማጡን ያጠፋ ነበረ:: በተለይ ደግሞ ሥርአቱ ወሳኝና አስፈላጊ ብሎ የሚጓዝበትን የሥልጣን ምሰሶ አቅም መስበር የታቻለበት ነበረ:: ከ300 በላይ እርሻዎች፣ ፋብሪካዎችና የተለያዩ ቦታዎች የወደሙበት፤ ሥርዓቱ አሁን ለደረሰበት የኢኮኖሚ ውድቀት ወሳኝ እርምጃ የተወሰደው ያን ጊዜ ነበር:: በሰአቱ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለእኛ ያለውን አመለካከት የለወጠበት ነው::

አምስቱ የቁጣ ቀናት ከፍተኛ መሥዋእትነት የተከፈለበት ቢሆንም፣ አንዳንድ ስህተቶች የነበሩበት ትልቅ እንቅስቃሴ ነው:: ሌላኛው በቀለ ገርባን ለማስፈታት መጨረሻ ላይ ያደረግነው እንቅስቃሴ በጣም ወሳኝ ነበር:: ምክንያቱም ኢህአዴግ ቄሮን በስራችን ከተናል ብለው የተረጋጉበት፣ እንቅስቃሴውም በሙሉ ቀዝቅዟል የተባለበት ነበርና በሁለት ቀን ሀገሪቱን ሙሉ በሙሉ በመዝጋት የተሠራው ሥራ የቄሮ ጉልበት በከፍተኛ ደረጃ መፈርጠሙና የኢህአዴግ ጉልበት ደግሞ በጣም የተመናመነ እንደሆነ ታይቷል::

በዚያ ወቅት በቀለ ገርባና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን ባይለቋቸው ኖሮ በአራተኛው ቀን ፖሊሱን መቆጣጠር የሚያስችል ዝግጅት ነበር:: ይሄም በጣም ያዋጣ ስትራቴጂ ነው:: … ግብር እንዳይከፈል በማለት የተደረገው ሥራ ወደዳር ቆሞ የነበረውን ማህበረሰብ ወደ ቄሮ እንዲጠጋ ዕድል ከፍቶለታል:: ይህ ደግሞ ለቄሮ የሎጂስቲክና የፋይናንስ እንዲሁም የሞራል ድጋፍ እንዲያገኝ መንገድ የከፈተ ነበር:: እነዚህ ከትልልቆች መሃል የሚጠቀሱ ናቸው::

**ግዮን፡- በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዳይ በቀን ውስጥ ምን ያህል ሰዓት ትሠራለህ?**

**ጀዋር**፡- ባለፉት አራት ዓመታት ለሃያ ሰዓታት በሥራ ውስጥ የምቆይበት ሁኔታ ነበር:: አሁን አሁን ቀለል እያለ ነው፤ የዚያን ጊዜ ግን ለረዥዥም ሰዓታት ነበር የምሠራው፤ ቤትም አልገባም ነበርና ቢሮ የማድርበት ሁኔታ ነበር:: አምስት ሺህ የሚሆኑ ታጋዮቻችን እንደሚሞቱ እያወቅን፣ እያወቁ ወደ ትግል ውስጥ ገብተው እስከ አፍንጫው የታጠቀውን አግዓዚን እጃቸውን አጣጥፈው ፊት ለፊት ተጋፍጠዋል:: ውድ ሕይወታቸውን አሳልፈው ሰጥተዋል::

ቢያንስ ቢያንስ 30 እና 40 የሚሆኑ ቆስለው የአካል ጉዳተኛ የሆኑበት ሁኔታ ነው የነበረው፤ በአጠቃላይ ከፍተኛ የሆነ የአእምሮ ሥራና የማደራጀት ሥራ ነው የሠራነው:: ብዙ ሕይወትና ጉልበት ያጣንበት ቢሆንም ግን ውጤቱ ከእኛም አልፎ ለሀገሪቷ ከፍተኛ ተስፋ የፈጠረ የለውጥ እንቅስቃሴ ያየንበት ስለሆነ የእኛ ድካም ብዙም ሊሰማን አይገባም:: ውጤቱ አመርቂ ነውና::

**ግዮን፡- በትግሉ ወቅት የሚደርሱ የሞት፣ የአካል ጉዳትና የመሳሰሉ መሥዋእትነቶችን በግልፅ የሚያስረዱ ዝርዝር ዳታዎችን ትይዛለህ?**

ጃዋር፡- ሁሉን ነገር መዝግቤ ይዤዋለሁ ለማለት ይከብደኛል ግን አብዛኛው መረጃ አለኝ:: ለዓለም ሕዝብ የነበረውን እንቅስቃሴ በየሰዓቱ ለማሳየት ሞክረናል:: እኔም በፌስቡክ ከምለጥፈው ውጪ በማስታዎሻዎቼ በተለያየ መልኩ የያዝኋቸው አሉ:: በነገራችን ላይ በኢንተርናሽናል ሚዲያው ሳይቀር ሲወጡ የነበሩ ፎቶዎች፣ ዳታዎችና ቪዲዮዎች አብዛኛዎቹ ከእኔና ከሚዲያው የወጡ ናቸው:: በጣም ዶክመንት አድርገነዋል::

በቅርቡ በመጽሐፍም፣ በዶክመንተሪም ለመሥራት እየተዘጋጀን ነው ያለነው ሆኖም ግን ችግሩ በማራቶን ጉዞ ወደ መጨረሻው አንድ መቶ ሜትር ውስጥ ገባ እንጂ አልተቋጨም፤ ስለዚህ ትግሉ ወደኋላ እንዳይቀለበስ የማድረግ ሥራ እንቀጥላለን::

**ግዮን፡- ኦህዴድ ውስጥ አሁን የታየው ለውጥና የአቋም ጥንካሬ ከየት የመጣ ነው ትላለህ?**

**ጃዋር**፡- ኦህዴድን መለወጥ የስትራቴጂው አንድ ዓላማ ነበረ:: ባለፉት ዓመታት ስንል የነበረው ጉዳይ ነው:: አብዛኛው የኦሮሞ ሕዝብ ሥራ ይዞ ለመቀጠል የኦህዴድ አባል መሆን ነበረበት፤ ይህን የሠው ኃይል ወደጐን በማድረግና ለጠላት በመተው የሚደረግ ትግል የሚያዋጣ አይደለም:: ስለዚህ ከውጪ በየመንገዶቹና በየከተሞቹ የሚደረገው ትግል እንዳለ ሆኖ በኦህዴድ ውስጥ ለውጥ መምጣት አለበት የሚል ስትራቴጂ ተነድፎ ባለፉት አሥር ዓመታት ሲሠራበት የቆየ አካሄድ አለ::

ይህ አሠራር በኦህዴድ ውስጥ ጠንካራ ሰዎች የሚፈጠሩበትና ጠንካራ ሆነው ታፍነው የነበሩ ሰዎች ወደአመራር እንዲመጡ የተሠራ ብዙ ሥራ አለ:: ይህ አካሄድ በየጊዜው ኦህዴድን እየለወጠው መጥቷል:: ኦህዴድ ላይ ሁለት ነገር ነው የሆነው፤ አንደኛ ከውጭ የሕዝብ ጫና አለበት፤ ሁለተኛ ከውስጥ ዕድል እየፈጠረለት ነው የመጣው::

በተለይ እነ ለማ ወደአመራር መምጣታቸው ኦህዴድን እየቀየረውና ከሕዝብ እያቀራረበው የመጣበት ሂደት ነበረ:: ስለዚህ ለኦህዴድ መቀየር የትግሉ ስትራቴጂ በአንደኛነት የሚገለፅ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ሕዝብ እየገፋ ሲመጣ ኦህዴድ የነበረው ዕድል ወይ መለወጥ ነው ወይ መዘርጠጥ ነበረ:: ስለዚህ ለማና ግሩፑ በሚፈለገው መንገድ በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ ቻሉ:: በነገራችን ላይ ለማንም ኦህዴድንም የለወጠው ቄሮ ነው ብል ስህተት አይመስለኝም::

**ግዮን፡- አቶ ለማ መገርሳ የኦሮሚያ ፕሬዝዳንትና የኦህዴድ አመራር ከመሆናቸው በፊት ስለእሳቸው የምታውቀው ነገር ነበር?**

**ጃዋር**፡- ሰውን ማወቅ ሥራዬ ነው:: አይደለም ለማን የተደበቁትን የህወሓትን፣ የብአዴንንና በሁሉም ድርጅቶች ውስጥ ከዞን በላይ ያሉትን ሰዎች ፕሮፋይል ሲቪ ሠርተንባቸዋልና እናውቃቸዋለን:: ማን እንደሆኑ፣ አመለካከታቸው ምን እንደሆነ፣ ከየት ተነሥተው የት እንደደረሱ፣ የኑሮ ሁኔታቸው በየትኛው የፖለቲካ ሰርክል ውስጥ እንዳሉ ለእያንዳንዳቸው ያዘጋጀነውና የምንጠቀምበት ስለነበረ ለማንም ሆነ ሌሎቹን በደንብ የሚያስረዳ ትልቅ ዶሴ አለን::

ምክንያቱም ባላንጣህን ካላወቅኸው በስተቀር ልትታገለው አትችልም:: የራስህን ብቻ ሳይሆን የባላንጣህንም የሰው ኃይል ማወቅ መቻል አለብህ:: በዚህ የተነሣ የእነሱን የሰው ኃይል በደንብ ነው የምናውቀው፤ ስለዚህ ለማንም አስቀድሞ ገና ሳይመጣ ለረዥም ጊዜ ስንከታተለውና ስናጠናው ስለነበር በደንብ አውቀዋለሁ::

**ግዮን፡- አሁን እንደነገርኸኝ ስለአራቱም የኢህአዴግ ዋነኛ ድርጅቶችም ሆነ ሌሎች አጋር ድርጅቶች አውቃለሁ ብለሃል፤ ግን ሁሌም የምትናገረው ስለ ኦሮሞ ብቻ ነው::**

ጃዋር፡- በዋናነት የምሠራበት የኦሮሞ ማህበረሰብ እንደመሆኑ መጠን በስፋት

እያንቀሳቀስኩት ያለሁት ሕብረተሰብ እሱን ስለሆነ ነው ሁሌም ስለ ኦሮሞ የማወራው:: ያ ማለት ስለሌሎቹ ድርጅቶች ማወቅ የለብህም ማለት አይደለም፤ የፖለቲካ ባህርይ ሁሉን ማወቅ ያስገድዳል:: አሁን ስለብአዴን ቀረብ ብዬ ነው የማውቀው:: መጨረሻ ላይ የወጣውን የኦህዴድና የብአዴን ሕብረት በተመለተ አንዳዶቹን ለማበረታታት አንዳንዶቹን የማዳከም ሥራ መሥራት ስለነበረብን በሁሉም ፓርቲዎች አባላት ዙሪያ ጠለቅ ያለ ጥናት አድርገን ነበር::

ስለ ኦሮሞ ግን የበለጠ እናውቃለን:: ምክንያቱም ቤዝ ኦፍ ኦፕሬሽን ኦሮሞ ስለሆነ፣ እሱን በደንብ መረዳት ነበረብን፤ ግን ከኦሮሞው ባልተናነሰ ስለህወሓት፣ ብአዴን፣ ደኢህዴንና አጋር ድርጅቶች በቂ መረጃ አለን::

**ግዮን፡- በባህርዳር ኦህዴድና ብአዴን መገናኘታቸውና ጠንከር ያለ ግንኙነት መፍጠራቸው በህወሓትም ሆነ በቀሪው ሕብረተሰብ ዘንድ መነጋገሪያ ሆኗል:: የአንተ አስተያየት ምንድን ነው::**

ጃዋር፡- እሱን በሁለት ነገር ማየት አስፈላጊ ነው:: በነበረው የኢህአዴግ የውስጥ ፖለቲካና በነበረው ጊዜያዊ ፖለቲካ:: ሁለተኛው ደግሞ ለረዥም ጊዜ በነበረው የአማራና የኦሮሞ ሕዝብ ግንኙነት ላይ ወሳኝ ነበረ:: ምክንያቱም የአማራና የኦሮሞ ሕዝብ ለብዙ መቶዎች ዓመታት ጎን ለጎን አብሮ የኖረ ሲሆን፣ በአፍሪካ ቀንድ ደግሞ ሁለቱ በጣም ትልቅ ሕዝቦች ናቸው:: ሠፊ የሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቁርኝት አለው::

በዚህ ረዥም ግንኙነት ውስጥ አንዳንዴ እየተጋጨ፣ አንዳንዴ እየተባበረ የመጣ ማህበረሰብ ነው:: ከዚህ የተነሣ ህወሓቶች ሁለቱን እያጋጩ መሄድ ይፈልጋሉ:: ሁለቱ ተባበሩ ማለት ትልቅ ለውጥ ይመጣል፤ ይህ እንዳይሆን ሁለቱን እየነጣጠሉ መሄድ ህወሓቶችን ብቻ ሳይሆን ጣልያኖችን ጨምር ረድቷል:: ለውጥ እንዲመጣ ከተፈለገ ሁለቱን ማህበረሰብ ማቀራኘትና ማስተባበር ግዴታ ነው::

ይህ የእኛ እምነት ነበረ:: ኦህዴድና ብአዴን በዚህ መንገድ በመጓዝ በጣም ቆፍጣና አመራር ነው ያደረጉት:: ለማ፣ ዐቢይ፣ ገዱ፣ ንጉሡ ጥላሁን ከፍተኛ ሥራ ነው የሠሩት፤ የኦሮሞ ወጣቶች ሄደው እምቦጭን መንቀላቸውና ከዚያ በኂላ የተካሄደው ትልቁ ኮንፈረንስ ህወሓቶች አማራንና ኦሮሞን ለማጋጨት የነበራቸውን ፍላጐት ሙሉ ለሙሉ ዘጋ:: ከዚያ ቀደም ብሎ የተሠራ ትልቅ ነገር ነበር:: ኦሮሚያ ውስጥ ኦሮሞ ያልሆነው ማህበረሰብ በብዛት አማራ ነው:: ከዚህ የተነሣ ህወሓቶች ሊያጋጩ ይችላሉ ብለን ስለሰብን ከፍተኛ ጥንቃቄ ተደርጐ ኦሮሚያ ውስጥ ምንም አይነት የሁለቱ ብሔር ግጭት አልተካሄደም:: በመጨረሻ ኢሉባቦር አካባቢ ሞከሩ፤ እሱንም በፍጥነት መቆጣጠር ተችሏል:: የእነ ለማ እንቅስቃሴ የደህንነት መ/ቤቱ አቅዶት የነበረውን ተንኮልና ደባ አክሽፎበታል::

**ግዮን፡- በ27 ዓመት የኢህአዴግ ዘመን ባልታየ መልኩ ኢትዮጵያዊነትን የሚሰብኩ አዲስ ጠ/ሚኒስትር ተገኝተዋል:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ለመጀመሪያ ጊዜ በፓርላማ ንግግር ያደረጉበትን ሂደት እስኪ መለስ ብለህ አስቃኘን፤**

ጃዋር፡- እንግዲህ ዐቢይ በዚህ ለውጥ ውስጥ የመጣ ወጣት አመራር ነው:: እስካሁን እየሠራቸው ያሉ ሥራዎች የሚደነቁ ናቸው:: እንግዲህ ዐቢይ በፖለቲካ ውስጥ አልቆየም፤ ከወታደሩ ዓለም ነው የመጣው፤ ፖለቲካው ደግሞ በጣም ውስብስብ ከመሆኑ የተነሣ፣ ለዚያ ቦታ ለማ ይሻላል የሚል አቋም ነበረን:: ሆኖም ግን ዐቢይ ወደሥልጣን ከመጣ በኂላ እያደረጋቸው ያሉት እንቅስቃሴዎች የሚያበረታቱ ናቸው::

ጠንካራ የሆነ ድፍረት ያለው ሠው እንደሆነ በተጨባጭ እያየን ነው ያለነው፤ ፍጥነትም አለው:: የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለመለወጥ ከተፈለገ ድፍረት፣ ፍጥነትና ብልሀት ያስፈልጋል:: እነዚህን ሦስቱን አያይዞ በጀመረው መንገድ የሚጓዝ ከሆነ ለውጥ ያመጣል ብዬ እገምታለሁ:: እስካሁን ያለው ነገር የሚያበረታታ ቢሆንም ብዙ ያልሰማናቸው፤ ልናያቸውና ልንሰማቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ::

ለምሳሌ፡- ሀገሪቱ ወደዴሞክራሲ መሸጋገር አለባት፤ ነፃ፣ ፍትሐዊና ተፎካካሪ ወደ ሆነ ምርጫ መሄድ መቻል አለብን:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ስለዚህ ጉዳይ እስካሁን በግልፅ ያስቀመጠው ነገር የለም:: ከተፎካካሪዎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተደራድሮ ስለምርጫ ሕግጋትና ስለምርጫ አካሄድ ግልፅ የሆነ መመሪያ ማስቀመጥ መቻል አለበት::

ሰኞ ዕለት በፓርላማ ያደረገው ንግግር እስካሁን ገዢው ሥርዓት በተለይ ደግሞ ሀገር እየዘረፉ፣ ሕዝብ እየገደሉ ለመቀጠል የሚፈልጉ ሙሰኞች ላይ እያደረገ ያለው ተጨባጭ እርምጃና የቃላት ጦርነት ሊበረታታ የሚገባ ነው:: የዐቢይ ኃይል አንድና አንድ ብቻ ነው፤ የቄሮ ኃይል:: እርሱ ሕዝባችንንና ሀገራችንን ወደፊት የሚያራምድ ጠንካራ ሥራ እስከሠራ ድረስ የቄሮ ኃይል ከኂላው እንዳለ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ::

የህወሓት ሰዎች ምንም ያህል ቢፍጨረጨሩ አሁን ምንም ማምጣት አይችሉም:: ጠ/ሚኒስትር ዐቢይም ይህንንን የተረዳ ይመስለኛል:: የሕዝብን የልብ ትርታ ተረድቷል:: ከእንቅስቃሴው አኳያ በኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ይመስለኛል::

**ግዮን፡- በአንተ እምነት አሁን የታየው የፖለቲካ ለውጥ በቄሮ ብቻ የመጣ ነው ትላለህ?**

ጃዋር፡- የቄሮ ብቻ አይደለም፤ ብዙ ኃይሎች በሂደቱ ተሳትፈዋል:: ኦህዴድ፣ ብአዴን የሠራው ሥራ አለ:: ሌሎች ተቃውሞዎችን ብንመለከት አማራ ክልል ውስጥ እንቅስቃሴ ነበር፤ ኮንሶ ውስጥ እንቅስቃሴ ነበር:: ግን በተደራጀ፣ ስትራቴጂክና ዘላቂ በሆነ መልኩ ለአራት ዓመት ያላቋረጠ ጫና በሥርዓቱ ላይ በማድረግ፤ ሥርዓቱን ፍርክስክሱን ያወጣው የቄሮ ኃይል ነው፤ ይህ ማጋነን አይመስለኝም::

ጠንካራ የሆነ ለወደፊት የዓለም ምሁራን እንደ ኬዝ ስተዲ የሚያጠኑት እንቅስቃሴ ነበረ:: ለአራት ዓመታት ባልተቋረጠ መልኩ ስልቶችን በመቀያየር አቅሙንና ፍጥነቱን እየጨመረ ትልቅ ተጋድሎ ያደረገውና ሌሎችን ያነሣሣው ቄሮ ነበር:: ብቻውን ነበረ ወይ ለሚለው ግን ብቻውን አልነበረም፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሥርዓቱን ታግለዋል፤ የዚህ ሁሉ መሪ ግን ቄሮ ነበር::

**ግዮን፡- ኤች አር 128 በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ የቀየረው ነገር ያለ ይመስልሃል?**

ጃዋር፡- ድጋፍ አድርጓል:: ሁሌ እንደምለው ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ማምጣት ከፈለግን 90 ፐርሰንት የሚሆነው ሥራ ኢትዮጵያ ውስጥ በኢትጵያውያን መሠራት አለበት:: የዲፕሎማሲ ሥራ ከአሥር ፐርሰንት መብለጥ የለበትም የሚል አቋም ነበር ያለኝ:: ዘጠና በመቶውን አንተ ከሄድህበት አስር ፐርሰንቱ ሲጨመር ትግልህ መቶ በመቶ ግቡን ይመታል::

ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገውን እንቅስቃሴ የተሟላ ለማድረግ የውጭው ጫና፣ በተለይም በአውሮፓ ፓርላማ የተደረገው ሪዞልዩሽን፣ እንዲሁም በአሜሪካ ፓርላሜንት የተደረውና በውስጥም በመንግሥት ላይ ሲደረግ የነበረው ጫና ከፍተኛ ውጤት አለው:: በተለይ ደግሞ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአሜሪካ አምባሳደር ሀገራችን ወደ ዴሞክራሲ ከተሻገረች ትልቅ ሚና አላቸው ከምላቸው ግለሰቦች ውስጥ አንዱ ይሆናል:: ይህ አምባሳደር እውነተኛ የኢትዮጵያ ጓደኛ ነው፤ እንደሌሎች አምባሳደሮች ሳይፈራና ሳያስመስል ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ እንዲመጣ ቁርጥና ግልፅ የሆነ አቋም በመያዝ፤ በግልፅ በሚናገራቸው ነገሮችና በሚያወጣቸው መግለጫዎች መንግሥት ላይ የሚያደርገው ጫና ቀላል አይደለም ስለዚህ ይህ አምባሳደር ሊመሰገን ይገባል::

**ግዮን፡- ብዙ የፖለቲካ ሰዎች በኢትዮጵያ የፖለቲካ ዕርቅ ያስፈልጋል ይላሉ፤ ይህንን እንዴት ታየዋለህ?**

ጃዋር፡- ብሔራዊ ዕርቅ ያስፈልጋል ይባላል፤ ግን እኮ በብሔራዊ ደረጃ አልተጣላንም፤ ጥሉ ሁሌም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ነው:: ከብሔራዊ ዕርቅ ይልቅ ብሔራዊ መግባባት ያስፈልጋል:: ሊያስተማምነን፣ ሊያስተባብረን የሚችል ሶሻል ኮንትራት መገንባት መቻል አለብን፤ ባሉን ልዩነቶች ላይ ልዩነቶችን እንዴት አክብረን መሄድ እንችላለን? የዴሞክራሲ ሕግጋቶችና የመቻቻል ግቦች ላይ ልንግባባና ልንተማመን ይገባል::

በቅድሚያ ይህንን ነው መሥራት ያለብን:: ይህን ለማድረግ ግን በቅድሚያ ወደ ምርጫ መሄድ መቻል አለብን:: አትሊስት አሁን በምርጫ ሂደትና ሕግጋት ላይ ከተስማማን በኂላ የተመረጠ መንግሥት ይኖራል:: ከተለያየ ቦታ የሚመረጡት ተወካዮች በመደራደርና በመከራከር የብሔራዊ መግባባቱን መገንባት የሚችሉ ይመስለኛል:: አሁን ባለው ሁኔታ ወደዚያ እንሂድ ካልን ፕሮሰሱ ትንሽ አስቸጋሪ ይሆናል::

ኦሮሞን ማን ይወክላል? አማራን ማን ይወክላል? የሚለው ግልፅ አይደለም:: ሁሉንም ማህበረሰብ እንወክላለን ብለን እንታገላለን እንጂ ሕዝቡ አልወከለንም:: እኛ ራሳችን ነን ለሕዝቡ እየተናገርን ያለነው:: ስለዚህ የሕዝቡን ውክልና ያገኘው ተወካይና ፓርቲ ተቀራርበው እንዲሠሩ ማድረጉ የሚሻል ይመስለኛልና ብሔራዊ መግባባት ያስፈልጋል:: ሂደቱ ላይ ግን በስፋት መወያየት ያስፈልጋል::

**ግዮን፡- የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ካቢኔ ምን ጠንካራ ጎን አለው? ምንስ ደካማ ጎን አለው?**

ጃዋር፡- ቤትህን የምትገነባው በአካባቢው ባለ እንጨት ነው:: ኢህአዴግ ውስጥ ካለው ሰው አንፃር ነው ገለባብጦ እየተጠቀመባቸው ያለው፤ ግን አሁን ካሉት ብቃት ያላቸው በጣም ጥቂት ናቸው:: ኢትዮጵያ አሁን የምትፈልገውን አመራር መስጠት የሚችሉ በጣም ጥቂቶች ናቸው:: ስለዚህ ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል እጥረት አለበት - ዐቢይ::

አንዳንድ በጣም ጎበዝ የሆኑ ሰዎች ቢኖሩም፣ ጠ/ሚኒስትሩ እያደረገ ባለው ለውጥና ፈጣን እንቅስቃሴ ብቃት ያላቸው ሚኒስትሮች በብዛት አልተሾሙም:: ለምሳሌ፡- በኤሌክትሪክ ኃይልና በኢኮኖሚው ላይ የሚሠሩ በጣም ጎበዝ ሰዎች አሉ:: በአብዛኛው ግን ተስፋ የሚጣልባቸው ሰዎች አይደሉም::


**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

ከጃዋር መሐመድ ጋር ያደረግነው ቆይታ በዚህ አይቋጭም፤ በተለያዩ ወቅታዊና ሀገራዊ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ አነጋግረነው የሰጠንን ምላሽ በቀጣይ ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን::




ተረፈ ወርቁ

# መሪዎች ፍቅርና በጎ ሕሊና ያስፈልጋቸዋል!!



*የሕንዱ የነፃነት አባት ማሕተመ ጋንዲ*



*የአሜሪካ የነፃነት ተሟጋች ማርቲ ሉተር ኪንግ*

የዛሬውን ጽሑፌን አሜሪካዊው የጥቁር ሕዝቦች መብት ታጋይ፣ የሥነ መለኮት ምሁርና ፖለቲከኛ የነበረው ዶ/ር ማርቲን ሉተር፤ ‹The Strength of Love› በሚለው ድንቅ መጽሐፉ፤ በብዙዎች አሜሪካውያን ዘንድ እጅግ ተወዳጅና ተደናቂ በኾኑት በፕሬዚዳንት አብርሃም ሊንከን የፖለቲካ ሕይወት ታሪክ ዙርያ ባስነበበው አንድ እውነተኛ ታሪክ ለመጀመር ወደድኹ:: ማርቲን ሉተር (ዶ/ር) ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፉ በሕይወት ዘመኑ ከሚያደንቃቸው የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች መካከል አንዱ የሆነው አብርሃም ሊንከን ‹በፍቅርና በይቅርታ› መንፈስ ከወዳጆቹ አልፎ ጠላቶቹን እንኳን መግዛትና በፍቅር እንዲታዘዙለት ያደረገበትን አስደናቂ የሆነውን ታሪኩን እንዲህ ይተርክልናል::

እርስ በርስ መካሰስ፣ መጠላላትና መበላላት፤ የሌላውን ታሪክ ማጉደፍ፣ የሌሎችን ሰብአዊ ክብር መንካትና ማዋረድ እንደ ጀብዱና አሸናፊነት በሚቆጠርበት፤ ጥላቻ፣ ጽንፈኝነትና መለያየት ባየለበት የሀገራችን ፖለቲካ፤ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞቻችን ይህ በማርቲን ሉተር ኪንግ መጽሐፍ የተተረከው የአብርሃም ሊንከን ፍቅርንና በጎ ሕሊናን የተላበሰ ማንነት፣ አስደናቂ ፖለቲካዊ ሰብእናና ጨዋነት ለመሪዎቻችንም ሆነ በተፎካካሪ ጎራ ለተሰለፉ የፖለቲካ ሰዎች አንዳች ትርጉም ይኖረዋል ብዬ አስባለኹ::

ብዙዎቻችን እንደምናውቀው አብርሃም ሊንከን የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ለመሆን በተደጋጋሚ ሞክሮ በተደጋጋሚ የወደቀና ያልተሳካለት ፖለቲከኛ ነበር:: ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ ውድቀቱ ተስፋ ሳይቆርጥ በትዕግሥትና በቆራጥነት በመወዳደር በመጨረሻ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ለመሆን የቻለ መንፈሰ ጽኑ ሰው ነው:: ታዲያ ይህ ሰው በአንድ ወቅት ለአሜሪካ ፕሬዝዳንታዊ የምረጡኝ ዘመቻ በሚያደርግበት ወቅት እጅግ አድርጎ የሚጠላው ተቀናቃኝ የሆነ “ሳንተን” የተባለ አንድ ፖለቲከኛ ነበር:: ይህ ሰው አብርሃም ሊንከንን፤ ‹‹ምንም የማይረባ፣ ያልተማረ፣ በአሜሪካውያን ለመመረጥ የሚያበቃው ሚዛን የሚደፋ ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ ሰብእና የሌለው›› እያለ በአደባባይ ከማዋረድ አልፎ ብዙም ግድ ስለሌለው ስለ አብርሃም ሊንከን አለባበስና የመልኩ አስቀያሚነት እንኳን ሳይቀር እጅግ በሚያሳቅቅ ሁኔታ በየአደባባዩ ይዘልፈውና ያዋርደው ነበር:: ይሁን እንጂ እልህ አስጨራሽ ከሆነው የምረጡኝ ዘመቻና የተጧጧፈ ክርክር በኋላ በምርጫው አብርሃም ሊንከን አሸንፎ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ለመሆን በቃ::

አብርሃም ሊንከን የአሜሪካ ፕሬዝዳንትነትን ክብር ካገኘና ወደ ኋይት ሀውስ ከገባ በኋላም ከፍተኛ ባለሥልጣኖቹን ሲመርጥና ሲሾም በምረጡኝ ዘመቻ ወቅት እጅግ አድርጎ ሲጠላውና ሲያዋርደው የነበረውን ሳንተንን በአሜሪካ ከፍተኛ የሆነውን የጦር አዛዥነት ሥልጣን ሰጥቶ ሾመው:: በዚህ ባልተጠበቀ ሹመት አሰጣጥ የተደናገጡት የአብርሃም ሊንከን ወዳጆችና ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናቱ፣ በሁኔታው ግራ በመጋባት አብርሃም ሊንከንን እንዲህ ሲሉ ጠየቁት፡-

‹‹ይህ ተቀናቃኝህ የነበረ ሰው እንዴት አድርጎ ሲያዋርድህና ሲዘልፍህ እንደኖረ ትዘነጋዋለህ ብለን አንገምትም፤ ታዲያ በምን ምክንያት ነው በዘመኑ ሁሉ ጠላትህ የሆነውን ሰው ለዚህ ዓይነቱ ታላቅ ሹመት የመረጥኸው!? በአሜሪካ ወሳኝ በሆነ ከፍተኛ ሥልጣን ላይ በማስቀመጥስ እንዴት መንግሥትህን ለአደጋ ታጋልጣለህ!?›› በማለት ወቀሳና ምክር ቢጤም ለገሱት::

አብርሃም ሊንከንም ከፍተኛ ባለሥልጣናቱንና ወዳጆቹን በትዕግሥትና በእርጋታ ካዳመጣቸው በኋላ ‹‹ተቀናቃኜ የነበረው ሳንተን እንዴት ያዋርደኝና ያጥላላኝ እንደነበር አውቃለኹ:: ለሀገራችን ለአሜሪካ ግን እጅግ አስፈላጊና ለዚህ ከፍተኛ ሹመትም ከእርሱ የተሻለ ሰው አይኖርም ብዬ ስለገመትሁና ለቦታው የሚገባውና የሚመጥነው ብቸኛ ሰው ሳንተን መሆኑን አጥብቄ ስለተረዳሁ ይህን ሹመት ሰጥቼዋለሁ!›› በማለት ለባለሥልጣናቱ እና ለወዳጆቹ ነገራቸው::

ሳንተንም በሥልጣን ዘመኑ ለሀገሩና ለመንግሥቱ እጅግ ታማኝና ታዛዥ በመሆን ለአሜሪካና ለሕዝቦቿ ታላላቅ ሥራዎችን የሠራ ጀግና፣ ብልህና ትጉሕ የጦር አዛዥ ሆኖ ነበር ያለፈው:: ይህ ሰው በአብርሃም ሊንከን ድንገተኛ ሞት ዕለት እጅግ ልብን በሚነካ ኀዘንና ስሜት ውስጥ ሆኖ አሜሪካ ድንገት ስላጣችው ፕሬዝዳንቷ እንዲህ ነበር ▶

ያለው፤ ‹‹He is one of the greatest men that ever lived and said ‘he now belongs to ages’›› በእርግጥ ሊንከን ከፍቅር፣ ከሰላምና ከእርቅ መንገድ ይልቅ በሰይፍ የቀን ቅዠታቸውን እውን ለማድረግ በቆረጡ ግብዞችና ሰነፎች ነፍሱ ብታልፍም፣ ታሪኩና ሕይወቱ በታሪክ መዝገብ ውስጥ ሕያው ሆኖና ደምቆ አሁንም ድረስ በታላቅ ክብር ይነሣል፤ ይወደሳልም::

የዚህን ታሪክ ጫፍ ይዘን ወደ እኛው እውነታ ስንመለስ ግን በሀገራችን ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመታት የጥላቻ፣ የመከፋፋት፣ የመበላላትና ዘግናኝ የሆነ የእርስ በርስ እልቂት የፖለቲካ ታሪክ ነው ያሳለፍነው ማለት ይቻላል:: ይህን የሀገራችንን የፖለቲካ ሰማይ በጥላቻና በክፋት ደመና እንዲጀቦን ያደረገ ክፉ ባህል መወገድ እንዳለበት አዲሱ ጠ/ሚ ዐቢይ ደጋግመው በቃል ከመናገር ባለፈ በኢሕአዴግ መንግሥት ሥር ለዓመታት በእስርና በእንግልት የነበሩ ፖለቲከኞችን ነጻ በመልቀቅ ቃላቸውን በተግባር ጭምር አሳይተውናል:: እንደ ጠላት፣ እንደ ክፉ ባላንጣ ይተያዩ የነበሩ የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎችም ከስማቸው ጀምሮ ‹‹ተቃዋሚ›› ሳይሆን ‹‹ተፎካካሪ›› ተብለው እንዲጠሩና እርስ በርሳቸውም በጠላትነት እንዳይተያዩ ጭምርም አሳስበዋል፤ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትራችን::

ዶ/ር ዐቢይ በንግግሮቻቸው ውስጥ፤ ‹‹በመንግሥትም ሆነ በተፎካካሪ ፓርቲ ወገን ያሉ ሰዎች ዓላማቸው ለሀገራቸው ሰላምና ፍትሕ፣ ልማትና ብልጽግና ለማምጣት እስከሆነ ድረስ ሁላችንም በፍቅር፣ በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘን መቆም እንችላለን፤›› በማለት ባልተለመደ ሁኔታ ለዘመናት ጥላቻ፣ ቂም፣ በቀልና የሞት አዋጅ ሲታወጅ የነበረበትን በሀገራችን ፖለቲካ ሰማይ ላይ የፍቅር፣ የበጎነት፣ የቅንነት መንፈስ እንዲናኝበት አድርገውታል:: ይህ ሰው ሰው የሚሸት፣ በጎነትና ቅንነት የተላበሰ፣ በፍቅር የተገራ ሰብዕና በተለይ በተለይ ለአንድ መሪ በእጅጉ ያስፈልጉታል::

በሕዝባቸው ዘንድ ‹‹ታላቁ ነፍስ›› በመባል የሚሞካሹት የህንድ የነጻነት አባት ማሕተመ ጋንዲ፣ ከፍርሃት ከሚመነጭ አምባገነንነትና ጥላቻ ከሠለጠነበት ሥልጣን ይልቅ ከፍቅር የሚመነጭ ሥልጣን ውጤታማና ዘላቂ እንደሆነ በአንድ ወቅት ተናግረው ነበር:: በእውነትም ሕዝብን በመልካም ለመምራትና ለማገልገል ሥልጣንን የሚገራ፣ ልጓም ኾኖ የሚቆጣጠር የፍቅር ልብ፣ ቅንና በጎ ኅሊና ያስፈልጋል:: ይህን ቅን ልብ ያልታደሉ፣ ከበጎነት ጋር የተፋቱ፣ ፍቅርና በጎነት የጎደላቸው፣ ክፋትና ጭካኔ የነገሠባቸው መሪዎች በታሪክ ደጋግመን እንዳየነው የሥልጣናቸው ምንጭ ፍርሃት የሚወልደው ጭካኔ፣ ማን አለብኝነትና አምባገነንነት ነው::

የሥነ-አመራር ምሁራን አንድ ድንቅ የኾነ አባባል አላቸው፤ ‹‹When you lead yourself use your mind but when you lead others use your heart›› የሚል:: ይህ አባባል የሚነግረን ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር ሌሎችን ወይም ሕዝብን በመልካም ለመምራትና ለማስተዳደር አፍቃሪ፣ ቅን፣ አመዛዛኝ፣ ይቅር ባይ፣ ታጋሽ የኾነ ሰፊ ልብ እንደሚያስፈልግ ነው:: ለሕዝብ የአደራ ቃል ታማኝ የኾኑ፣ በሕዝብ ፍቅር የነደዱ፣ በሕዝባቸው ጽኑ ቃል ኪዳን የታሠሩ፣ ራሳቸውን ለመሥዋዕትነት ያዘጋጁ እንደ አይሁዳዊው ሕዝብ ነጻ አውጪ፣ እንደሊቀ ነቢያት ሙሴ፡- ‹‹ይህን ሕዝብን በምድረ በዳ ከምታጠፋው እኔን ከሕይወት መዝገብ ደምስሰኝ›› የሚሉ፤ በሕዝባቸው ስለሕዝባቸው ፍቅር በነፍሳቸው የቆረጡ፣ ጽኑ፣ ባለ ራዕይ የኾኑ ጀግና መሪዎችን ማግኘት ትልቅ መታደል ነው::

ታሪክ እንደሚያረጋግጥልን መሪ መፈለግ የሰው ልጅ የተፈጥሮ ጠባይ ነው:: ሕዝብ አንድ ድምፅ ኖሮት እንዲተዳደርና ጠላቱን እንዲከላከል መሪ ያስፈልገዋል:: መሪ የነጻነት፣ የሉዓላዊነት ምልክት ነው:: ለሕዝቡ ቢበጅም ባይበጅም፣ መሪ ያላት አገር ነጻነት እንዳላት ይታወቃል:: ገዥና ተገዢ፣ መሪና ተመሪ መሆን ግን የሥራ ድርሻ እንጂ የሰብዕና ልዩነት ግን አይደለም:: በዘመናት መሪዎች ሕዝቡ ለእነርሱ እንደተፈጠረ ያስቡ ነበር:: ነገር ግን መሪው የሕዝቡ እንጂ ሕዝቡ የመሪው እንዲሆን አይደለም እውነታው::



እናም ሕዝብ በሌለበት ወንበር አይኖርም፤ ሕዝብ ባለበትም መሪ አይቀርም:: ሁላችንም እኩል ነን የሚሉ ወገኖች እንኳን ስያሜውን አይቀበሉት እንጂ መሪ አላቸው:: ሥራው ካለ ስያሜው ትንሽ ድርሻ ነው የሚወስደው:: በእርግጥም ሥልጣን የገዢዎች የብቻቸው ደሴት አይደለም፤ እንደተፈለገ የሚሆንበት:: ስለዚህ የመንግሥትና የሕዝብ የሚባል ነገር አይኖርም:: የመንግሥት የሕዝብ ነው፣ የሕዝብም የመንግሥት ነው:: ምክንያቱም ሁለቱም አንዱ የአንዱ ነውና::

መሪን ማክበርና መውደድ ጸጋ ነው:: ለመወደድ ግን መውደድ እንጂ ምንም ቅድመ ሁኔታዎች የሉትም:: መሪዎች እጅግ ፍቅር የሚያስፈልጋቸውና ፍቅርን የተራቡ ናቸው:: ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ሕዝቦች መሪዎቻቸውን ይጠላሉ:: ማንም የመጥላት መብቱ ዲሞክራሲያዊ ነው የሚለው የምድር ሕግ ቢሆንም በትክክል ሰው የመሆን ልዕልና ግን የማፍቀርን መብት የሚጠቀም ‹የፍቅር ሕግ› ነው:: ማፍቀር ሲቻል መጥላት እንዴት ይመረጣል!? ሰዎች ነጻነት አላችሁ በተባሉበት ሀገር ሁሉ በነጻነታቸው ጥላቻቸውን ለመግለጥ መጠቀማቸው በመሪዎችና በሕዝብ መካከል ረጅም ገደልን ፈጥሯል።

በዘመናችንም በምድራችን ላይ ዓለም ኹሉ የተገረመባቸውን ጥቂት ጥሩ መሪዎችንም ተነሥተው አይተናል:: በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን ታሪክ፣ ብዙ ገዥዎችና መሪዎች ተለዋውጠዋል:: ከአውሬ በጥቂቱ የሚለዩ አምባገነኖችም ተከስተዋል:: ደጋግ ነገሥታትና መሪዎችም ራቅ ራቅ ብለው ተነሥተዋል:: የእናትን ያህል ፍቅርና ክብር ተችሯቸው ‹እምዬ› በሚል የተጠሩ እንደአፄ ምኒልክ ያሉ ደጋግ ነገሥታትም በሀገራችን ታሪክ ተከሥተዋል::

የራሳቸውንና የሕዝባቸውን እንደመርግ የከበደ የዘመናት ግዙፍና አሰቃቂ የግፍና የመከራ ታሪክ በይቅርታ ዘግተው፣ ቂም በቀል የሚያመረቅዝ ቁስልን በፍቅር ዘይት እንዲሽር አድርገው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ዕርቀ ሰላምን ያወረዱ፣ ‹‹ሬንቦው ኔሽን›› በሚል ቅፅል የገነነችውን አዲሲቷን ደቡብ አፍሪካ ዕውን ያደረጉ እንደ ማንዴላ ያሉ ብርቅዬ የሕዝብ መሪዎችን በአፍሪካ ምድር አይተናል::

በሕዝባቸው ዘንድ ‹‹ታላቁ ነፍስ›› በሚል የሚሞካሹትን የህንድን ሰላማዊ አብዮት የመሩ እንደ ጋንዲ ያሉ ብረት ሣያነሡ፣ ሠራዊት ሳያስከትቱና አንድ ጥይት እንኳን ሳይተኩሱ ሀገራቸውን ህንድን ከብሪታንያ ቅኝ ግዛት ያላቀቁ፣ በዚህም ‹‹የህንድ የነጻነት አባት›› የሚል ስያሜና ክብር የተጎናጸፉ ተመልክተናል:: በቅርብ ደግሞ እንደላቲን አሜሪካዋ ኡራጓይ መሪ ያሉ ሀብት ንብረታቸውን ሁሉ ለሕዝባቸው አድርገው እንደተራ ሰው ከሕዝባቸው ጋር ተቀላቅለው በፍቅርና በሰላም የሚኖሩ መሪንም ለማየት በቅተናል::

የእነዚህ ደጋግ ነገሥታት ወይም መሪዎች ምንጫቸው ጥሩ ሰብዕናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ክፉ የሆነ ሰብዕናንና ባሕርይን የሚለውጠው ፍቅር ነበር፤ ነውም:: በታሪካችን እንዳየነው ሥልጣን የሕዝብ አደራ መሆኑን መቀበል ከብልግናና ከአምባገነንነት አያግድም:: ሥልጣን የፈጣሪና የሕዝብ አደራ መሆኑን መቀበል ግን ጠንቃቃ ያደርጋል:: የክፉ ገዢዎች ተጽእኖም አሁን ያሉበት ወንበር ብቻ ሳይሆን ያደጉበት ቤተሰብና ኅብረተሰብ የነፈጋቸው ፍቅር ነው:: ማንም ቢሆን ያልተቀበለውን አይሰጥምና!!

ሰላም!



አካለወርቅ መንገሻ (ረ/ፕ)

# ወላይታዊ ኢትዮጵያዊነቴ፡ ክብር ለወገኔ ክብር ለሀገሬ

እኔ ተወልጄ ያደግሁት ወላይታ ነው:: ወላይታነቴ ውስጥ ኢትዮጵያዊነቴ የተዋደደ እንደሆነ አምናለሁ:: የተወለድሁበት፣ ወደዚህች ምድር የተቀላቀልኩበት፣ እንደ ሰው የተቀረጽሁበትን የባህልና የወግ ጌጥ ያገኘሁበትና ያጌጥሁበት፤ ሁሌም ሳስብ እጅግ የተለየ ስሜት፣ ትርጉምና ቦታ የምሰጠው ማንነቴ ነው:: ስለዚህ የወላይታው ኢትዮጵያዊ ስለሆንኩ ኢትዮጵያዊነቴ ካደግሁበትና ማንነቴን ካገኘሁበት ህዝብና አካባቢ የሚመነጭ ነው:: በመሆኑም ይህ ጽሑፍ አሁን ላይ እጅጉን ላሽመደመደን የዘረኝነት በሽታ ሰለባ የመሆኔ ውጤት ሳይሆን ማንነቴን፣ ሰብእናየን፣ አኗኗሬን በአጠቃላይ ሰዋዊ ምሰሶዬን በመሬት እየጎተቱት እየተሳለቁበት ለማፍረስ ብሎም በቁም ለመቅበር አሁንም ድረስ ደፋ ቀና ለሚሉት ከዚህ የቀን ቅዠታቸው እንዲነቁና ወደአእምሮአቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ነው:: በዋናነት ደግሞ ሌላውን በማዋረድ፣ በማብጠልጠል፣ በቁም በማጥፋት ከፍ ያለ ቦታ እና ክብር ለማግኘት ለሚሯሯጡ የሰው ሰብእና ለሚጎድላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች የመጨረሻውን ደወል እንዲሰሙና የትኛውም የተደገፉት ምርኩዝ ተሰባሪ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው::

እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ እጅግ የተዋቡና የተለያዩ ግን ደግሞ በጠንካራ የአብሮነትና የፍቅር ገመድ የተሳሰረ ማንነት ያላቸው ህዝቦች መጠለያ፣ መኖሪያና መቃብር ናት:: ሀገር በእናት የመመሰሏ ዋነኛ ምክንያትም እናት ልጆችን ትወልዳለች፤ ልጆችም የአንድ አብራክ ክፋይ መሆናቸውን የሚያሳይ መመሳሰል በመካከላቸው ይኖራል እንጂ አንድ ዓይነት ግን ሊሆኑ አይችሉም:: ስለዚህም የሚለያዩበት መንገድ ለቤተሰቡ ውበትና ደስታ የሚፈጥር ሆኖ እናገኘዋለን:: ኢትዮጵያችንም በውስጧ ያቀፈቻቸው የአብራኳ ክፋይ ስለሆኑ የሚመሳሰሉበት እንዲሁም የሚለያዩበት ውስጣዊ ሆነ ውጫዊ ገጽታ ተሰባጥሮና ተቀምሮ ትልቋን የተከበረች፣ የምትወደድ ሀገር ልክ እንደ አንድ በአካባቢው የተወደደና የተከበረ ቤተሰብ ትክክለኛውን ምስል ይፈጥራል:: ሆኖም ግን እስከ ዛሬ ድረስ ይህን ሀቅ ተቀብሎ ለሁሉም ምቹ እና አስደሳች የእናት/ሀገር መኖርያ ጎጆ መገንባት አልተቻለም:: በመሆኑም የሀገራችን ታሪክ በዋናነት የጦርነት፣ የጭቆናና የበደል እንዲሁም የድህነት ሆኗል:: ይህንን ሚዛኑን የሳተ ቡድናዊና ግለሰባዊ ግንኙነት በአግባቡ ተገንዝቦ ሁሉንም የምትቀበል፣ ለሁሉም የምትመች ሀገር መገንባት እጅጉን ከብዶን እንገኛለን::

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ላለፉት ሃያ ሠባት ዓመታት ታሪካዊ ጭቆናና በደል ለማስተካከል የሚል ሽፋን ተሰጥቶት ውስጣዊ ቁስልና ቁርሾ በማባባስ እንዲያገረሽ በማድረግ፤ በማለያየት የሚገኘውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማጋበስ ሲሠራ ቆይቷል:: በዚህም ሂደት ሀገራዊ አንድነትንና ፍቅርን ስጋት ላይ በሚጥል ደረጃ ስር የሰደዱ የዘረኝነትና የራስ-ተኮር ፍላጎቶች መረን ጥሰው ከሰውነት ይልቅ እንስሳዊ ባህርይ አላብሰውናል::

**ወላይታ ልዩነትን ከአብሮነት ጋር ማዋሃድና ማስተሳሰር መነሻውና መሰረቱ ስለሆነ፣ ሌላውን ሲያይ አይፈራም፤ አይደንግጥም፤ አይሰጋም:: ደግሞም ወላይታ የተለየ ኩራትና ዕርባና ቢስ ትህምክት ፈጽሞ የለበትም:: ወላይታ ሌሎችን በማክበርና በፍቅር በመኖር ገደብ የለሽ ማንነቱን እየተደበደበና እየተገደለ ጭምር እያሳየ ይገኛል**

ሆኖም ግን ለነዚህ ታሪካዊ ጭቆናዎችና በደሎች ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች በተመሳሳይ ደረጃና ጥልቀት ሰለባ ናቸው ማለት ግን ፈጽሞ አይቻልም:: በመሆኑም እናቱ የሞተችበትና እናቱ ገበያ የሄደችበት እኩል ሊጮሁ ከቶ አይገባቸውም:: በህዝብ ቁጥራቸው፣ በኢኮኖሚያዊ አቅማቸው እንዲሁም በሌሎች መመዘኛዎች የተሻለ ደረጃ ያላቸው ከእነሱ በታች ያሉትን የመጨቆንና የመርገጥ ዕድል ይኖራቸዋል:: በሌላ በኩልም ሲታይ ደግሞ እንደ ህዝብ በቁጥርና በኢኮኖሚያዊ መስፈርት የተሻሉ ስለሆኑ አይጨቆኑም ማለትም እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ለምሳሌ እንደ ህዝብ የኦሮሞ ብሄር በብዙ መልኩ የፖለቲካዊና የማህበረሰባዊ በደል ገፈት ቀማሽ እንደሆነ ይታወቃል:: በታሪክ ድርሳናትም ሆነ በተጨባጭ እንዳየነው ይህ ታላቅ ህዝብ 'መጥፎ ምስል' ሲሰጠውና በሌሎች ወገኖቹ እንዲጠላና ቅቡልነት እንዳይኖረው በጥልቀትና በስፋት ተሠርቷል:: እኔም በግሌ እንዳየሁት የኦሮሞ ህዝብ በርግጥ እንደሌሎች ጭቁን የሀገሬ ብሄሮች መበደሉን ለማወቅ የተለየ ማስረጃና ጥናት አይፈልግም:: በሌላ መልኩ በቁጥር አናሳ የሆነ ሁሉ የተጨቆነ በእርግጠኝነትም የሚጨቆን ነው ማለትም የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል:: ግን ደግሞ ከሌላው በተለየ ሁኔታ ለጭቆናና ለውርደት ተጋላጭ (vulnerable) እንደሚሆን ይታወቃል::

በዚህም ሂደት እስካሁን እጅግ በሚያሳዝን ደረጃ የጭቆና መጥፎ ምስል ሰለባ ስለሆነው ስለታጋሹ አርቆ አሳቢ ታላቁ የወላይታ ህዝብ የተወሰነ ነገር ለማለት ነው:: ወላይታ ማለት መንታ ትርጉም አለው፦ አንድም የህዝቡ መጠሪያ ስም ሲሆን፣ ሁለትም የአካባቢ መገለጫ ጭምር ነው:: 'ወላይታ' ማለት ጥሬ ትርጉሙ፤ ተቀላቀለ፣ ተዋሃደ፣ አንድ ሆነ ማለት ሲሆን፤ ይህም መነሻው ቀድሞ የብሄር ማንነት የነበራቸው የተለያዩ ጎሳዎች፣ በገዛ ፈቃዳቸው አንድ ላይ ሆነው ራሱን የቻለ ወላይታ የሚባል ማንነት መፍጠራቸው ነው:: በመግቢያዬ ላይ እንደ ጠቀስሁት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሰማሁትንና ያነበብሁትን ብቻ ሳይሆን የሆንሁትን፣ የኖርሁትንና የማውቀውን ነው ለመጻፍ የሞከርሁት:: ስለዚህ የወላይታ ህዝብ መነሻው አንድነት፣ ውህደትና አብሮነት የሆነ የፍቅር ተምሳሌት ህዝብ ነው::

ወላይታ ውስጥ ብዙ ጎሳዎች እንዳሉ ▶

ይታወቃል:: ይሁን እንጂ የእነዚህ ጎሳዎች መነሻ ብሄር እንደሆነ አሁን ካላቸው የጎሳ ስምና ስብጥራቸው መረዳት ይቻላል:: ለምሳሌ ወላይታ ውስጥ ቀድሞ እንደ አማራ፣ ትግሬ ወ.ዘ.ተ. ያሉ የብሄር ማንነት ያላቸው አሁን ደግሞ የጎሳ ደረጃ ይዘው ታላቁን የወላይታ ምስል ፈጥረዋል:: ስለዚህ ወላይታ ማለት የጎሳ ስብስብ የፈጠረው ማንነት ሳይሆን፤ ብሄራዊ ማንነት ያላቸው የራሳቸውን ማንነት ሳይጥሉ በጎሳ ደረጃ ተደራጅተው፣ ተዋደውና ተፋቅረው የሚኖሩበት ማንነት ነው:: ይህ በመሆኑ የወላይታ ህዝብ ተከባብሮ መኖርንና አንድነትን ገና የሚያስተምሩት ሳይሆን መሰረቱና ህልውናው ነው:: የስሙ ትርጉም ፍቅር፣ አንድነት፣ አብሮነት የሆነ ከዚህ ታላቅ ህዝብ ውጭ ሰምቼም አይቼም አላውቅም:: በርግጥ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በመፈጠሬና የማንነታቸው ክፋይ በመሆኔ ዕድለኛ እንደሆንኩ ይሰማኛል፤ ምክንያቱም አሁን ላለሁበት ውስጣዊ ሰላም፣ ጤነኛ አስተሳሰብና በራስ-መተማመን ትልቅ ድርሻ አለውና::

ወላይታ ልዩነትን ከአብሮነት ጋር ማዋሃድና ማስተሳሰር መነሻውና መሰረቱ ስለሆነ፣ ሌላውን ሲያይ አይፈራም፤ አይደንግጥም፤ አይሰጋም:: ደግሞም ወላይታ የተለየ ኩራትና ዕርባና ቢስ ትህምክት ፈጽሞ የለበትም:: ወላይታ ሌሎችን በማክበርና በፍቅር በመኖር ገደብ የለሽ ማንነቱን እየተደበደበና እየተገደለ ጭምር እያሳየ ይገኛል:: የወላይታ ህዝብ በውስጣዊ ማንነቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፣ በበላይነትም ሆነ በበታችነት ስሜት የማይጋልብና የማይጋለብ፣ ሰላማዊ ሚዛኑን ጠንቅቆ የሚያውቅ ህዝብ ነው:: በአንፃሩ በታሪክ እንደምናውቀው በዚያው ልክ ይህንን ትልቅ ሰብእናውን ገፎ በጉልበትና በማን አለብኝነት ለመጣበት ከቶ የማይንበረከክና ለጠላቶቹ የእሳት ረመጥ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም::

ሆኖም ግን ይህ ህዝብ በሀገራችን ታሪክ ውስጥ እጅግ የተጨቆነና ማንነቱና ምስሉ የወረደ ቦታ የተሰጠው በመሆኑ ከሌሎች ጭቁኖች ጋር በመሆን ሲታገል ቆይቷል:: በጣም የሚያሳዝነው ግን ይህ አስከፊ ምስልና ጭቆና አሁንም ከፍ ባለ ደረጃ መቀጠሉ ነው:: በዚህ ረገድ ፈጽሞ ማንነቱን በማይገልጽ ደረጃ ምስሉ የተበላሸ፣ በድህነት የሚማቅቅ የሀገሬ ህዝብ ያለ አይመስለኝም:: ይህ ደግሞ የሆነው በዋናነት እንደ ህዝብ ከድሮ ጀምሮ የማንኳሰስ፣ የማዋረድና ያልተገባ ስም የመስጠት (labeling) ሴራ በመኖሩና ማህበራዊ ስነ-ልቦናውን በማሽመድመድ አቅሙን የማዳከም ከተቻለም በሁሉም ረገድ ከጨዋታ ውጭ የማድረግ ተንኮል ስላለ ነው::

በእውነታው ግን ወላይታ እጅግ ብርቱ፣ ታጋይና ሞራላዊ እሴቱን ጠብቆ የሩቁን እያየ፣ ሩቅ እያለመ የሚኖር አስተዋይ ህዝብ ነው:: አሁንም ደግሞ ከስድብና ከዛቻ ታልፎ መንግሥትና ሕግ ባለበት ሀገር የመደብደብ፣ ያላቸውን ጥቂት ንብረት የማውደምና የመግደል ተግባር ውስጥ ከተገባ ቆይቷል::

የወላይታውን ማንነት ጠንቅቃችሁ ካላወቃችሁ፣ ወላይታዊ ማንነት ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ ማንነት እጅግ ጥልቅና ረቂቅ መሆኑን ልትረዱ ይገባል:: መሠረቱ አብሮነትና ፍቅር ነው፤ የተለያየ ቢመስልም ውስጡ ንፋስ እንዳያስገባ ሆኖ የተዋደደ ነው፤ ሲታይ ምስኪንና ትንሽ ቢመስልም በውስጡ ብርቱና ኃያል ሆኖ ይገኛል፤ የዋህነቱን ተጠቅሞ ሊበዘብዘው ለቀረበው ደግሞ እጅጉን ረቂቅ፣ አርቆ አሳቢና ብዙ እርምጃዎችን ቀዳሚ ሆኖ ይገኛል::

ዛሬ ላይ ይህ ህዝብ ሠርቼ ራሴንና ሀገሬን ልለውጥ ባለ በየቦታው ይዋረዳል፣ ይገደላል:: በዚህች ሀገር ወላይታ ሆኖ ጥሩ ስሜት ሊሰማው ቀርቶ መልካም ሥራ ሠርቶ እንኳን ፈጽሞ ሙገሳና ክብር እንዳያገኝ ሆኖ ተገንብቷል:: በቅርቡ የነበረው ሁኔታ ይህን እውነት በደንብ ያሳየናል:: አሁን ላይ የቀድሞ ጠ/ሚ የሚለውን ማዕረግ ያገኙት አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በዚህ ሴራ ያልተገባ ስምና ቦታ በማግኘት ዋነኛ ሰለባ ናቸው:: እሳቸው እንደ መሪ የራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን እንደሚኖራቸው እሙን ነው:: በዚህ በዘረኝነትና ጥላቻ በዘቀጠ ፖለቲካ ውስጥ ሰዎችን የምናይበት መንገድ ጤነኛ ባለመሆኑ እጅግ አሳዛኝ በሆነ ደረጃ እሳቸው የወጡበት ማህበረሰብ የንብረትና የሕይወት መሥዋእትነት ከፍሏል:: አሁን እያየነው ባለው የተስፋና የለውጥ ፍንጣቂ ውስጥ የእሳቸው የጎላ አስተዋጽዖ የሌለበት አስመስሎ ማቅረብና ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ጠ/ሚሩን ጨምሮ አሁን በሚዘመርላቸው ግለሰቦች፤ በተለይ ደግሞ በቁሮ ድጋፍ ብቻ የመጣ ነው ማለት የቀድሞውን ሚዛኑን የሳተ አካሄድ መድገም ከመሆኑም በላይ ያልተገባ ቦታና ስም የመስጠቱ ሂደት አሁንም ተጠናክሮ መቀጠሉን የሚያረጋግጥ ነው:: እሳቸው ጋር ያየናቸው ውስንነቶች እንደ ነበሩ ሆነው፤ በሀገራችንም ሆነ በዓለማችን በቀላሉ የማናገኛቸው እንደ ሀገርም ልናከብራቸውና ልንከተላቸው የሚገቡን የታላቅ ስብዕና ባለቤት መሆናቸውን በሚያሳዝን ሁኔታ አልሰማንም አላየንም:: ከዚህ ባለፈም የእሳቸውንና የወጡበትን ማህበረሰባዊ ስነ-ልቦና ለማሽመድመድ መሠራቱ የትም እንደማያደርሰን አልተገነዘብንም::

አሁን የመጣው ለውጥ በዋናነት የእሳቸው ትግልና ከባድ መሥዋእትነት ያለበት መሆኑን መገንዘብ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው የዘረኝነት መነጽሩን ማውለቁ ብቻ በቂ ነው:: የእሳቸው ዓላማ በህዝብ መገልገል ሳይሆን ህዝብን ማገልገል ብቻ እንደነበር ( servant leader) ራሳቸው ደጋግመው ተናግረዋል:: እንደዚህ ያለ ዕይታና አስተሳሰብ በእሳቸው ነበር የተጀመረው:: የዚህ ምንጭ ደግሞ ለሀብትና ለሥልጣን ያላቸውን የተለየ አስተሰብ መሰረት ያደረገ፤ ሥልጣንን የህዝብ ማገልገያ መሣሪያ አድርገው የሚያዩበት ከፍ ያለ ሞራላዊና ስነ-ልቦናዊ ሰብዕናቸው ነው:: ራሳቸውን ያሸነፉ፣ የሀብትና የሥልጣን ጥም ውስንነቶችን ጥሰው የወጡ፣ በኑሮአቸው በተግባር ያስመሰከሩ፣ በመልካም ስነ ምግባራቸውና ጥልቅ ዕውቀታቸው የተወደሱ፣ አርቆ አሳቢና አስተዋይ ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ናቸው:: እናም በድርጅታቸው ዘልቀው ገብተው ሰው በላ አስተሳሰብ ካላቸው፣ በሀብትና በሥልጣን ጥም ከታወሩት ጋር ተሟግተው፤ በድርጅቱ ውስጥ ለዓመታት የታፈኑትንና ቦታ ያጡትን የህዝብ ብሶቶች ከራሱ ከድርጅቱ ጀምሮ ገንፍለው እንዲወጡ በማድረግ ለውጡን በግንባር ቀደምትነት መርተዋል፤ የራሳቸውን ከፍተኛውን ሥልጣን በመልቀቅም መሪነታቸውን አሳይተዋል::

ለውጡ እንዲመጣ ድርጅቱ ችግሮችን ወደውስጥ ተቀብሎ ራሱን እንዲያጠራና ለተራማጅ ኃይሎች ዕድል እንዲሰጥ ታግለው አሳክተዋል:: አሁን የምንዘምርላቸው ሰዎች በጣም ለረጅም ጊዜ ታፍነውና ጥግ ይዘው የቆዩ እንጂ ከሰማይ የወረዱ አይደሉም:: እሳቸው አርቆ አሳቢና ራስ ተኮር ፍላጎታቸውን ያሸነፉ ስለነበሩ፣ አሁን የምንዘምርላቸውን ግለሰቦች እንዲፈጠሩ አደረጉ:: ብዙ አጨብጫቢ የማይፈልጉ፣ በውስጣቸው የረኩና ዓላማቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው:: ሆኖም ግን ከርሳቸው መልካም ግለሰባዊ ሰብዕና ከመማርና ከመጠቀም ይልቅ በማንኳሰስና በማብጠልጠል ትልቁን ምስል ለማደብዘዝ የተቻለንን በማድረግ ላይ እንገኛለን:: ስለሆነም በእሳቸው ላይ የደረሰው ሁሉ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና የህዝቡን ምስል ከማጉደፍ ጋር የተያያዘ ከመሆኑም በላይ የኔ ወገን ይበልጣል በሚል በታሪክ ከፍ ያለ ቦታ ለመያዝ የሚደረግ ሩጫ ነው::


በአጠቃላይ በዚች ሀገር በሁሉም መስክ የቻለውን ሁሉ እያበረከተ ያለ ህዝብ የማንም መሳለቂያና መዘባበቻ የሚሆንበት ምክንያት አይኖርም:: የዚህ በደል ሰለባዎች ምንም የማያውቁ ሕፃናት መሆናቸው ደግሞ ይበልጥ ያሳዝናል:: ይህም መሠረቱ የህዝቡን ምስል የማበላሸት ሴራ ውጤት በመሆኑ፣ ልጆቻችን ያልተገባ ስም እየተሰጣቸው ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ይደበደባሉ:: ሌላውን የሀገራችንን ክፍል ትተን አዲስ አበባን ብቻ ብንመለከት እንኳን፣ በየአካባቢው ትንንሽ ሥራዎችን የሚሠሩ ሕፃናት ሲሰደቡና ሲደበደቡ ማየት የተለመደ ነው:: ባለፉት ዓመታት፣ በተለይ በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች ሕፃናት እጅግ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ተደብድበዋል፣ ተገድለዋል:: ሰሞኑንም በሐዋሳ ባልታወቀ ምክንያት የሲዳማ ህዝብ አዲስ ዓመት በዓል ላይ የንጹሐን ሕፃናት ደም ፈሷል:: በሌሎች ቦታዎችም በተመሳሳይ አስጊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ:: የሕፃናት ሕገ-ወጥ ዝውውርና ጉልበት ብዝበዛ ወንጀል በሆነበት ሀገር ይህ በመሆኑ እጅግ ያማል::

ለዚህ ሁሉ ስቃይና ሞት የዳረጋቸው በዋናነት እጅግ ሥር የሰደደ ድህነትና ስለ ስደት የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ይህንን ትውልድ ገዳይ ሰንሰለት የዘረጉ ነፍሰ በላ ሰዎች ናቸው:: በርግጥ የወላይታ ህዝብ ለሌሎች የሚተርፍ ረሀብና ዕርዛት የማያውቅ ነበር:: አሁን ግን ውድ ልጆቻችን ለረሃብ፣ ለስደትና ለሞት ተጋላጭ ሆነዋል:: እጅጉን ሆድ የሚያስብሰው ይህ ሁሉ ሲሆን የመንግሥት ሹመኞች ጭምር ዝም ማለታቸው ነው:: ለሆዳቸውና ለሥልጣናቸው ያደሩ መበራከታቸው ለዚህ ውርደት ዳርጎናል::

ስለሆነም የወላይታ ህዝብ እያሳለፈ ላለው እጅግ አስከፊ ጊዜ በዋናነት ተጠያቂው መንግሥት ስለሆነ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ከለላና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባዋል:: የወላይታ ልጆች በየሀገሩ ነገን ተስፋ አድርገው የቀን ጉርሳቸውን ለማግኘት ከሰሜን እስከደቡብ፣ ከምስራቅ እስከምዕራብ ሥራ ሳይንቁ እየሠሩ ሳሉ፤ የሚደበደቡበት፣ የሚሰደቡበትና የሚገደሉበት ሁኔታ በአስቸኳይ ቆሞ ወንጀለኞች ለሕግ ካልቀረቡ እጅግ አደገኛ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ነው::

ሁላችንም የወላይታ ልጆች ብንዘገይም ከተኛንበት የምንነቃበት ሰዓት አሁን ነው:: የእኛ ሚዛናዊ መሆንና ሀገር መውደድ ለጭቆና፣ ለውርደትና ለሞት ሊዳርገን አይገባም ነበር:: ዝምታችን እንደሞኝነት፣ ትእግሥታችን እንደ`ኋላ ቀርነት ተቆጥሮ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከመንቋሸሽና ከመናቅ አልፎ ወደግድያ ከተገባ ቆይቷል:: ስለዚህ ለማንነታችንና ለወገኖቻችን ሕይወት በአንድነት ቆርጠን ልንነሣ ይገባል::

# የኢትዮጵያ ዕድሏ ያሳዝናል



ደረጄ መላኩ

የሩቁን ትተን የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን በወፍ በረር ስንቃኝ ኢትዮጵያ ስመ ገናና ሆና መቆየቷን እንገነዘባለን:: ይህች ሀገር በቀይ ባህር ላይ ከ1000 ኪ.ሜ. በላይ የሚረዝም የባህር በር ነበራት:: የኢትዮጵያ ግዛት የነበረችው ኤርትራ አንዲት ሉአላዊት ሀገር በመሆኗ ሀገራችን ያለባህር በር ቀርታለች::

እንደተርብ ይናደፉ የነበሩ ቀደምት አባቶቻችን ከኦቶማን ቱርኮች፣ ከደርቡሾች፣ ከግብጾች፣ ከእንግሊዞችና ከጣልያኖች ጋር ተፋልመው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለሺህ ዓመታት የተፈጥሮ የባህር በሯ እንዳይዘጋ አድርገዋል:: ይህ የታሪክ ሐቅ ነው:: ግብጾች አራት ጊዜ የኢትዮጵያን ተፈጥሮ ባህር በር ለመቆጣጠር ሞክረው በአፄ ዮሐንስ ፊት አውራሪነት የውርደት ሸማ ተከናንባ ተመልሳለች:: ጣልያኖችና እንግሊዞች፣ ኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በሯ ተዘግቶ እንዲቀር ያደረጉትን የረጅም ዘመን ሴራ የሚዘነጋ አይደለም::

ኢትዮጵያ፣ በምስራቅ አፍሪካ ወይም በአፍሪካ ቀንድ እጅግ ስልታዊና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ የነበራት ሀገር ሁለቱንም የተፈጥሮ ባህር በሮቿን ስላጣች ጠቀሜታዋ እየቀነሰ መጥቷል:: በዓለም ውስጥ ካሉት ሀገራት ከአንድ መቶ ሚሊዮን በላይ ህዝብ እያላትና ከባህር (ከቀይ ባህር) በ60 ኪሎ ሜትር ርቀት እየተገኘች የባህር በር እንዳይኖራት የተከለከለች ሀገር ሆናለች:: የባህር ሕግ አዋቂዎች ይህንኑ ዓለም አቀፍ ሕግ እየጠቀሱ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት እንዳለባት በተገኙት ዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ለመሞገት ቢሞክሩም ሰሚ አላገኙም:: ከዚህ አንጻር በተባበሩት መንግሥታት ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ የነበሩት ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም፣ ስመ ጥሩው የታሪክ ፕሮፌሰር ማሞ ሙጬ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም፣ ዶክተር ታዬ ወልደ ሰማያት እና አንዳንድ ኤርትራውያን ፕሮፌሰሮችን ጨምሮ ኢትዮጵያ የባህር በር እንደሚያስፈልጋት ከሙያቸው አንጻር የገሃዱን ዓለም እውነታ በማንሣት ትንታኔያቸውንና ሙግታቸውን ለተለያዩ ተቋማትና ሀገራት መሪዎች አሰምተዋል::

"ጊዜ ያመጣውን ጊዜ እስከሚመልሰው" በሚል ዝምታን ያበዛው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ዛሬ ደግሞ በታሪክ ፈተና ውስጥ ይገኛል:: ይህ ህዝብ ራሱ በመረጣቸው መሪዎች ለመተዳደር ዕድሉን ለዘመናት በመነፈጉና እድሉን መጠቀም ባለመቻሉ ጥቂት የፖለቲካ ቡድን አመራሮች በሚወስኑት የራሳቸው ውሳኔ ያለማቋረጥ ሲያነባ ቆይቶአል::

አጼ ኃይለ ሥላሴ ለአፍሪካ ሀገራት መሪዎች አርአያ በመሆን፣ በዓለም መድረክ ባደረጉት ንግግር፣ በአፍሪካ ሀገራት መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችን በመሸምገል እና በመሳሰሉት በብዙ መልኩ የሚመሰገኑ ቢሆኑም፣ ይህንን ፖለቲካዊ ጥበባቸውን በሀገር ውስጥ የኢትዮጵያን ታሪክ ለመለወጥ አልተጠቀሙበትም:: ፖለቲካዊ ተቀናቃኞቻቸውን በሙሉ ማየት አልፈለጉም ነበር:: የአክሊሉ ሀብተ ወልድን፣ የእንዳልካቸው መኮንንን፣ የዶክተር ምናሴን፣ የአቶ ከተማ ይፍሩን፣ የመኮንን ሀብተ ወልድን፣ የራስ አበበ አረጋይን፣ የጄኔራል መንግሥቱ ንዋይን፣ የአቶ ገርማሜ ንዋይንና የሌሎችንም ታላላቅ ሰዎች ምክር እና ዕውቀት በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላቸው አወዳደቃቸው አላማረም:: ኢትዮጵያ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት እንድትዘረጋ ቢመከሩ አልሰማ በማለታቸው ሀገሪቱን ለወታደሮች አሳልፈው መስጠት ግዴታቸው ሆኗል::

ከንጉሡ ሥልጣን በአመጽ በመንጠቅ የኢትዮጵያን በትረ ሥልጣን የጨበጠው ወታደራዊ መንግሥት (ደርግ) በኮሎኔል መንግሥቱ መሪነት ህዝባዊ መንግሥት ይመሠረታል፤ ኢትዮጵያም በነጻነቷ፣ በአንድነቷ ታፍራ እና ተከብራ ትኖራለች ተብሎ በብዙ መልኩ ተነግሮ የነበረ ቢሆንም፣ ቃልና ተግባር ሊገናኝ አልቻለም፤ በዚህ ምክንያትም ኢትዮጵያ በደም ታጠበች:: በማንም የማይተኩት ስልሳው ባለሥስልጣናት ተገድለዋል፤ ነጭና ቀይ ሽብር በሚል ጎራ ተለያይተው የኢትዮጵያ ልጆች አልቀዋል:: ይህም የውርደትና የሀዘን ታሪካችን ነው:: ደርግ መድብለ ፓርቲ ሥርአት በሀገሪቱ እውን እንዳይሆን በብዙ መልኩ በመከልከሉ ሀገሪቱ ነፍጥ ባነገቱ ተቃዋሚ ኃይሎች እንድትያዝ አድርጓታል::

የደርግን ሥርዓትን በመቃወም ነፍጥ ካነሡ ቡድኖች ህዝባዊ ግንባር ኤርትራ (ሻዕቢያ) አስመራን፣ ኢህአዴግ ደግሞ አዲስ አበባን በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. በመያዛቸው የደርግ ሥርዓት ፍጻሜ ሆነ::

የደርግ ሥርአት ፍጻሜ በኢትዮጵያ ላይ ታላቅ ችግር ፈጥሮ አልፎአል:: በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተለይ በኤርትራ እና ትግራይ ክፍለ ሀገሮች (በቀድሞው አጠራር) ለብዙ ዓመታት የነበረው ሥር የሠደደ ችግር በሰከነ አእምሮ እና በዲፕሎማሲያዊ ጥበብ ሊፈታ ባለመቻሉ፤ ሀገሪቱ ለሁለት እንድትከፈል፣ ኢትዮጵያም ለዘመናት ስትጠቀምበት የነበረውን የተፈጥሮ ባህር በሯን እንድታጣ ምክንያት ሆኗል::

ወታደራዊውን መንግሥት በጦር ሜዳ ያሸነፉት ኢህአዴጋውያን በሥልጣን ዘመናቸው መጀመሪያ ላይ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እንዲዘረጋ እና የነጻው ፕሬስ እውን እንዲሆን ሻማውን በመለኮሳቸው ሙገሳ አግኝተው ነበር:: በሕገ መንግስቱ የሰብአዊ እና የዲሞክራሲዊ መብቶችን የሚያትቱ አንቀጾች ቢካተቱም ሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ መብታቸው የተገደበ ነው:: በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ሰዎች አርሰውና ነግደው ከሚኖሩበት መንደር "መጤ" በሚል የዘመኑ ቃል እየተባረሩ ነው:: ከቤኒሻንጉልና ከኦሮሚያ እና ከሶማሌ ክልል የአማራ፣ የጉራጌ እና የኦሮሞ ተወላጆች እየተፈናቀሉ መሆናቸው ለዚህ ማሳያ ነው::

## የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ውሳኔ

ግንቦት 28 ቀን 2010 ዓ.ም. ስብሰባ ላይ የተቀመጠው የኢህአዲግ ሥራ አስፈጻሚ ያስተላለፈው ውሳኔ ብዙኃኑን ኢትዮጵያዊ ያስደነገጠ ነበር:: ከሃያ ዓመት በፊት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በትግራይ ክልል በባድመ፣ በዛልአንበሳ፣ በጾረና እና በሌሎች የድንበር ከተሞች ላይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮች ያለቁበት በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል የተደረገው ጦርነት ከቆመ በኋላ ሁለቱም ሀገራት ጉዳዩን ወደዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት መወሰዱ የሚታወስ ነው:: የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ደግሞ ሁለቱን ሀገራት የሚዳኙ የሕግ ሰዎችን አልጄሪያ ዋና ከተማ አልጀርስ ላይ በሰየመው ችሎት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የኢትዮጵያ መንግስት ውሳኔውን በወቅቱ አልቀበልም ማለቱ ይታወሳል:: ከሃያ አመት በኋላ ደግሞ እንደሚቀበል አብስሯል:: ለሰላም እስከሆነ ድረስ ሁላችንም የምንቀበለው ጉዳይ ነው::

ከዚህ ጀርባ ኢትዮጵያውያንን የሚያሳስበው ጉዳይ ግን የአልጀርሱን ውሳኔ ለመቀበል ይህ ቀን ለምን ተመረጠ? የኤርትራ መንግሥት ምላሽ ምን ይሆናል? ከህዝብ ጋርስ በቅድሚያ ለምን አልተመከረበትም? የሚለው ነው:: ታላላቅ የኢትዮጵያ መንግሥታዊ ተቋማት ከህብረተሰቡ ጋር ሳይመከርባቸው በከፊል ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንዲሸጡ የተወሰኑበት ሁኔታ በመጪው ጊዜ ዋጋ ሊያስከፍሉ ይችላሉ:: ያለፉት አገዛዞች ህዝብን ሳያማክሩ እና የህዝብ ይሁንታ ሳያገኙ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻቸውን በመወሰናቸው ዛሬ ለተዘፈቅንበት ችግር ዳርገውን ከማለፋቸውም ባሻገር የኢትዮጵያን ዕድልም አሳዛኝ አድርገውታል::

የዛሬዎቹ ገዢዎቻችን ደግሞ ከአለፉት ገዢዎቻችን ስህተት ለመማር ፈቃደኛ በመሆን ትውልድን ሊጎዳ ከሚችል ውሳኔ ከማሳለፋቸው በፊት ለህዝብ ውይይት አቅርበው ቢወስኑ ለሀገርም ለህዝም ታላቅ ጠቀሜታ አለው::

ቸር እንሰንብት::

# "አሥራ አንድ ቤተሰቦቼ ከግንቦት ሠባት ጋር ኤርትራ በረሃ ናቸው"

## አንዱአለም አያሌው

*አንዱዓለም አያሌው ገላው ተወልዶ ያደገው በጎንደር ክፍለ ሀገር ደርጊ በምትባል ከተማ ነው፡፡ እስከዘጠነኛ ክፍል በትወልድ መንደሩ ከተማረ በኋላ ኢህአዴግ ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት ማግስት ወንጂ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቋል፡፡ በ1991 ዓ.ም. ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በአግሪካልቸር የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል፡፡*

*በተለያዩ አጋጣሚዎች በአማራ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ጭቆናና በደል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መምጣቱን ተከትሎ ሥርዓቱን በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ቆርጦ የተነሣው አንዱዓለም፣ በ1995 ዓ.ም. ባህር ዳር ላይ ኢዴፓ መድኅንን ተቀላቀለ፡፡ በፍኖተ ሰላም ከተማ የፓርቲውን ቢሮ በመክፈት ሕዝብን በማንቃትና በማንቀሳቀስ ትልቅ ሚና ከመጫወቱም ባሻገር፣ በ1997 ዓ.ም. በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ ቅንጅትን ወክሎ በመወዳደር አሸናፊ ሆናል፡፡*

*"ኢህአዴግ በሰላማዊ መንገድ ሊለወጥ አይችልም" የሚል አቋም በጊዜ ሂደት የያዘው አንዱዓለም አያሌው ግንቦት ሠባት ፓርቲ ይዞት የተነሣው ሁለ-ገብ የትግል እርምጃ አዋጪ ነው ብሎ በማመኑ ለትጥቅ ትግል ኤርትራ ከገባ በኋላ ከድርጅቱ ጋር በርከት ያሉ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡*

*ለተልዕኮ ከተጓዘበት ሱዳን ደህንነቶች አፍነው ካመጡት በኋላ በርካታ ዓመታትን በእስርና በስቃይ አሳልፏል፡፡ ከአንዷለም ባሻገር ሦስት ወንድሞቹና በአጠቃላይ አሥራ አንድ የቤተሰቡ አባላት ግንቦት ሠባትን የተቀላቀሉበት ምስጢርና ሌሎች የትግል እንቅስቃሴዎቹን በተመለከተ የግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩ ከአንዱዓለም አያሌው ጋር ሰፋ ያለ ቆይታ አድርገዋል፡፡*



*አንዱዓለም አያሌው ከባለቤቱ ጋር*

**ግዮን፡- እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ በፓርላማ ከቆየህ በኋላ የትጥቅ ትግል የሚያካሂደውን ግንቦት ሠባትን ተቀላቅለሃል:: ውይይታችንን ከዚህ ብንጀምር የተሻለ አይመስልህም?**

**አንዱዓለም**፡- መልካም፤ እንግዲህ የመጀመሪያው ፓርቲዬ በተለይ ብርቱካን ሚደቅሳ በድጋሚ ከታሰረች በኋላ እንቅስቃሴው ሙሉ ለሙሉ ከመድከሙ ባሻገር ውስጥ ለውስጥ የነበሩት የሥልጠና ሽኩቻዎች አሳሳቢ ደረጃ ላይ በደረሱበት ወቅት ነው ግንቦት ሠባት የመጣው:: ግንቦት ሠባት ተመሥርቶ እንቅስቃሴውን ማዕከል ያደረገበት ቦታ ከመታወቁ በፊት በወቅቱ ስዊድን የሚኖር ታናሽ ወንድሜ የተለያዩ ብሮሸሮችን፣ ሳምንታዊና ወርኃዊ መጽሔቶችን እየላከልኝ ስለግንቦት ሠባት በቂ ግንዛቤ እንዲኖረኝ አድርጓል::

ይህ ወንድሜ መሳፍንት አያሌው ይባላል:: አሁን ከግንቦት ሠባት ጋር ኤርትራ ነው ያለው:: የድርጅቱ የደህንነት ክፍል ኃላፊ ነው:: የትግል ስሙ ገበየሁ ይባላል:: ግንቦት ሠባት ኢህአዴግን ሊታገል ከሚችል ማንኛውም ድርጅት ጋር በጋራ እንደሚሠራ፤ የትግል ስትራቴጂው ሁሉን አቀፍ እንደሆነ፤ በማንኛውም መንገድ ከሚታገል ኃይል ጋር የፋይናንስ፣ የሐሳብና የሥልጠና ትብብሮችን እንደሚያደርግ በማወቁ መጀመሪያ ላይ ለስምንት ወራት አዲስ አበባ ተቀምጬ አንዳንድ የድርጅቱን ሥራዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ እሠራ ነበር::

በ2003 ዓ.ም. መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ ከአቶ አንደርጋቸው ጽጌ ጋር በነበረን ግንኙነት ለተሻለ ተልዕኮ በአስቸኳይ ወደ አስመራ መምጣት እንዳለብኝ ትእዛዝ ተሰጠኝ:: በጊዜው በዚህ ጉዳይ ባለቤቴን ለማሳመን የሁለት ወር ጊዜ ወስዶብኛል::

**ግዮን፡- የባለቤትህ የመከራከሪያ ነጥብ ምን ነበር?**

**አንዱዓለም**፡- በወቅቱ ባለቤቴ "ሐሳብህን አልቃወምም፤ ነገር ግን ያለን አንድ ልጅ ብቻ ስለሆነ፣ የምትሄደውም ወደጦርነት ነውና ሌላ ልጅ ለመውለድ ማርገዝ አለብኝ" የሚል ሀሳብ ነው ያቀረበችልኝ:: በዚህ ጉዳይ ለሁለት ወራት ያህል ሳንግባባ ቆይተን፣ በመጨረሻ ምንም የገንዘብ እገዛ ማድረግ ባልችልም እምነቴን በእግዚአብሔር ላይ ጥዬ ነፍሰ ጡር መሆኗን ካረጋገጥኩ በኋላ ነው ወደ ኤርትራ የሄድኩት::

**ግዮን፡- ወደ ኤርትራ የተሸጋገርህበት መንገድ ምን ይመስላል? ማን ወሰደህ? ማንስ ተቀበለህ?**

**አንዱዓለም**፡- በዚያ ጊዜ መተማ ይኖር የነበረ አንድ ወንድሜን አስጠርቼ ሀሳቤን ነገርሁት:: እሱም ለግንቦት ሠባት ሰዎችን በማድረስ ይሠራ ስለነበረና ቋንቋውንም በደንብ ስለሚችል በደስታ ተቀብሎኝ በሁመራ በኩል አድርጌ ኡምሀጅር ከተማ ስገባ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ “ጋሎች” የምትባል ከተማ ላይ ተቀብሎ ወደ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ተቋም ወሰደኝ::

ግንቦት ሠባትን ከተቀላቀልኩ በኋላ ተልዕኮዬ አልተነገረኝም:: ምን እንደምሠራም አላውቅም:: ግን አጠቃላይ የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ እያብራራልኝ ለአንድ ወር ከሃያ ሠባት ቀን አረና ላይ አብረን ከቆየን በኋላ ከኤርትራ ቴሌቪዥን በቀረበልን ጥያቄ መሠረት እኔ፣ አንዳርጋቸው፣ ኮ/ል ፍጹምና ሌሎች ሁለት ሰዎች ሆነን ወደ አስመራ ሄድን:: አስመራ ሃያ ቀን ቆይቼ አንዳርጋቸውን ወደ ለንደን ከመሸኘቱ ከሁለት ቀን በፊት “የተጠራኸው ለኤርትራ ቲቪ ኢንተርቪው ሳይሆን ለተጨማሪ ተልዕኮ ሱዳን ካርቱም እንድትሄድ ነው” ተባልሁኝ::

ካርቱም ስደርስ የት ቦታ ማንን ማግኘት እንዳለብኝ በዝርዝር ቢገለጽልኝም፣ ካርቱም እስክገባ ድረስ ሰዎቹን ከማግኘት ባሻገር የምሠራውን ሥራ አላውቅም ነበር:: እነሱ በነገሩኝ መሠረት የተባልሁት ቦታ እያረፍሁ፤ የተባሉትን የድርጅት አባላት እያገኘሁ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ነው ካርቱም የገባሁት:: እዚያ እንደደረስኩ ከአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ትእዛዝ ተሰጥቶኝ ሥራ እየሠራሁ እያለ ካርቱም ላይ ተያዝሁ::

**ግዮን፡- ያለኸው ሱዳን ነው፤ መረጃው እንዴት ሾልኮ ወጥቶ በኢህአዴግ ሰዎች ልትያዝ ቻልህ?**

**አንዱዓለም**፡- ከዚያ በፊት ሁለት ጊዜ ተይዤ አምልጫለሁ:: ካርቱም ውስጥ ሁለቴ የያዙኝ የሱዳን ደህንነቶች ናቸው፤ ኢትዮጵያውያን ደህንነቶች አይደሉም:: እነሱ ምን ልሠራ እንደመጣሁና የማን አባል እንደሆንሁ አውቀውኛል:: እኔም ክትትል እንደሚደረግብኝ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ቦታ እየቀያየርሁ ስለምንቀሳቀስ ሊያገኙኝ አልቻሉም:: አንድ ጊዜ የሱዳን ደህንነቶች በያዙኝ ወቅት ካርቱም ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን አይተው አሸዋ ዓይኖቻቸው ላይ በመበተን እንዳመልጥ ረድተውኛል::

ሥራዬ ሌሊት ነው፤ ቀን የሆነ ቦታ በማረፍ ነው የማሳልፈው:: ከአንዳርጋቸው ጋር በቀጥታ የስካይፒ ኮንፈረንስ የምናደርገውም ሆነ፤ ሌሎች ሥራዎችን በአብዛኛው የማከናውነው ሌሊት ነው:: እንደሚባለው ከሆነ ከመካከላችን ሰዎች በመጠቆማቸው ነው የተያዝሁት፤ ሐቁን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው:: ነገር ግን እኔን የሳሉበት መንገድ በጣም የተሳሳተና የተጋነነ ነበር:: ራሴን በወታደራዊ ሥልጠና ያዳበርኩ፤ ሊይዙኝ ሲሉ ጥቃት ማድረስ እንደምችል አድርገው ስላሰቡኝ በጣም ከፍተኛ ዝግጅት አድርገዋል:: የያዙኝም ካርቱም ውስጥ ተወልዶ ያደገ የአክስቴን ልጅ አግኝተው ስልክ እንዲደውልኝ ካደረጉ በኋላ በእራት ግብዣ አማካይነት ወደእሱ ቤት ስሄድ ከበው ነው::

**ግዮን፡- በመጨረሻው ሰዓት የያዙህ ኢትዮጵያውያን ደህንነቶች ናቸው?**

**አንዱዓለም**፡- አራት ኢትዮጵያውያንና ሁለት የሱዳን ደህንነቶች ናቸው የያዙኝ:: ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ያወቅሁት ትግርኛ ሲናገሩ ነው:: በአጋጣሚ የአክስቴ ልጅ ቤት አይታወቅም ብዬ ስለማስብ ዶክመንቶቼን ያስቀመጥኩት እርሱ ቤት ነበር:: የግንቦት ሠባት ወታደራዊ አደረጃጀቱ፣ ማኒፌስቶው፣ ኮ/ል ፍጹም (የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የኤርትራ ጠርናፊ ነው) ፈርሞ የሰጠኝ የደራሲው ማስታወሻ መጽሐፍና ስለግንቦት ሠባት ዓላማ የሚገልጹ ጽሑፎችን የያዘ ስድስት ሺህ ኮፒ መጽሐፍ ካርቱም ላይ በትኜ ነበር:: ከዚያ የተረፉ አሥር መጽሐፎችንና የኤርትራ ገንዘብ አግኝተውብኛል:: ከዚህ በተጨማሪ ላፕቶፔንና ሞባይሌን ይዘውታል:: በቂ መረጃ ነው ያገኙት:: የአንዳርጋቸውም ስልክ አለ:: እነዚህን ነገሮች ስላገኙ በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው ያመጡኝ:: ማደንዘዣ መርፌ ስለወጉኝ “ገላባት” ወይም የኢትዮጵያ ድንበር ላይ እስከምደርስ ድረስ ራሴን አላውቅም::

**ግዮን፡- ለምን ያህል ሰዓት?**

**አንዱዓለም**፡- ብዙ ነው:: መርፌ ከወጉኝ በኋላ የተጓዝነው መንገድ ወደሠባት መቶ ኪሎ ሜትር ይፈጃል:: ቦታውን ስለማላውቀው ማለቴ ነው:: ገላባት ላይ ወደ ኢትዮጵያ መኪና ሲገለብጡኝ ቀዝቃዛ ውሃ ደፍተውብኝ ነው የነቃሁት:: የያዙኝ ሰዎች ወደ ሱዳን ሲመለሱና ሌሎች ደህንነቶች ሲቀበሉኝ በጣም ማገናዘብ ባልችልም በተወሰነ ደረጃ የሚያወሩት ይሰማኝ ነበር:: ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ሲመክሯቸው እሰማ ነበር:: እንዲያውም በትግርኛ “ካብ ደጀን እስካብታሀሊፉ በይዝኮነ ምክንያት በፍጹም ጠው ጠው ከይትብሉ” ይሏቸው እንደነበር አስታውሳለሁ:: ይሄ ምንም አሻሚ ትርጉም የለውም:: ደጀን ከተማ እስከሚያልፍ ድረስ በምንም ተአምር መኪናውን እንዳታቆሙ ነበር የሚባባሉት:: አማራ የሚለውን ግዛት እነሱ ለክተው መጥነው የሰጡን ከደጀን እስከ መተማ ነው:: ሌላ ቦታ የእኛ ግዛት አይደለም፤ ሌላ ቦታ ለእኛ የሚቆረቆር ሰው የለም:: ከደጀን በኋላ ተዝናንተው መሄድ እንዳለባቸው ነበር የሚነጋገሩት::

እንደገና “ዮሐንስ” የምትባለው ከተማ ላይ መርፌ ከወጉኝ በኋላ ምን እንደተፈጠረ የማውቀው ነገር አልነበረም:: ሁለት ቀንም ሊሆን ይችላል፤ አስር ቀንም ሊሆን ይችላል፤ ብቻ ስነቃ ጨለማ ክፍል እጅና እግሬ ታስሯል:: በቦታው ምንም አይነት ድምጽ አይሰማም:: በጣም የታፈነና በድንጋይ የተሠራ ቤት በመሆኑ ያኔ ነው በራሴ ግምት ከመሬት በታች እንደታሰርኩ የገመትሁት:: በርግጥም ትክክል እንደነበርሁ ከረዥም ጊዜ የምርመራ ሂደት በኋላ ተረድቻለሁ:: ምክንያቱም ወደ ምርመራ ማዕከል የሚወስዱኝ በስትሬቸር ነው፤ ደረጃ ሲወጡ፣ በኋላ ደግሞ ደረጃ ሲወርዱ ይታወቀኝ ነበር::

**ግዮን፡- ስለቦታው ምንም አይነት መረጃ የለህም?**

**አንዱዓለም**፡- ዓይኔ በጥቁር ፕላስተር ታሽጓል፤ እጅና እግሬ በሰንሰለት ታስሯል፤ ለመርመራ ሲወስዱኝ የሆነ ሰፊ አዳራሽ ይመስለኛል፤ አንዱ ከአጠገቤ፣ ሌላው ከኋላ፣ አንዱ ደግሞ ከርቀት ይጠይቁኛል:: ከሁለት ወር በላይ እዚያ ቦታ ስቆይ በምንም ተዓምር መርማሪዎቹን ለማወቅ አልቻልሁም::

ምናልባት ያንን ቦታ ስወጣ በተወሠነ ደረጃ ጠርጥሬአለሁ፤ ከምርመራ በኋላ ወደማዕከላዊ ሲያመጡኝ ሰንሰለቱን ብቻ አስቀርተው ፊቴን ሳይሸፍኑ ነው:: ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ነው ይዘውኝ የወጡት፤ ያኔ ደረጃውን በእግሬ ወጣሁት፤ መኪና ውስጥ ከገባሁ በኋላ ተኛ ብለውኛል:: ግን ዓይኔ ስላልተሸፈነ አከባቢውን ቃኘቼ ነው የወጣሁት:: በኋላ እነጄኔራል አሳምነውን፣ ጄኔራል ተፈራንና ሌሎች ሰዎችን በቃሊቲ ቆይታዬ ስጠይቃቸው ቦታው በሽግግር መንግሥቱ ጊዜ የኦነግ ዋና ጽ/ቤት የነበረና አሁን ለብሔራዊ መረጃና ደህንነት መ/ቤት የሚጠቀሙበት እንቁላል ፋብሪካ ፖሊስ ክበብ አካባቢ እንደሚገኝ ተረድቻለሁ::

**ግዮን፡- በዚያ ስውር ቦታ ላይ የነበረው የምርመራ ሂደት ምን አይነት ገፅታ ነበረው?**

**አንዱዓለም**፡- በዋናነት እነሱ የፈለጉት ኤርትራ ውስጥ የግንቦት ሠባትን ብቻ ሳይሆን የደእሚትን፣ የሲአን፣ የአርበኞች ግንባር፣ የአዲአንን፣ የቤህንንና የጋምቤላ ነፃነት ንቅናቄን የሠራዊት ብዛት፤ የሞራል ጥንካሬና ከተቻለም ዕቅዳቸውን ነው ማወቅ የፈለጉት:: እሱን ምንም ሳልዋሽ ነው የነገርኳቸው:: የነበረው ምርመራ ወንድን ልጅ በጣም የሚፈታተን ስለነበርና በጣም ከባድ ስቃይ ስላለው መቋቋም አትችልም:: በዚህ ላይ በርካታ ሰነዶች እጃቸው ገብተዋል::

በምርመራ ወቅት ከነሰንሰለቴ ይዘውኝ ይወጣሉ፤ በጣም ለስላሳ እንጨት በእግሬ መሀል አስገብተውና ጠረጴዛ ላይ አስተኝተው ትተውኝ ይሄዳሉ:: ሲመለሱ ጥምብዝ ብለው ሰክረው ነው:: ደረቅ ፓይፕ አለ፤ በእሱ መላ ሰውነቴን ያለ ርኅራሄ እንደተንጠለጠልኩ ለሰዓታት ይገርፉኛል፣ በጫማ ይረግጡኛል፤ መሬት ላይ ጥለው ይደበድቡኛል፤ አንገቴን ይረግጡኛል፤ ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ ያሰቃዩኛል:: የኤሌክትሮኒክስ ምርመራም ተጠቅመውብኛል:: እየጮኸ ወደጭንቅላትህ የሚመጣ “ካስክ” የሚመስል ነገር አለ፤ የእኔ ግምት ነው:: ዓይኔ ስለተሸፈነ ማየት አልችልም:: ይህ ነገር ሲደረግብህ ላይህ ላይ አምስት ኩንታል የወደቀብህ ያህል ነው የሚሰማህ:: እጄን እንደታሰርኩ ወደላይ ስሰድ አልነካውም፤ እንድስቅ ያደርገኛል፤ እንድጨነቅ ያደርገኛል፣ በሂደት ደግሞ ራሴን ያስተኛል:: ከሰዓታት በኋላ ነበር የምነቃው:: እሱ በጣም አስጨናቂ ነው፤ ልቤን ይጐትተኝ፣ ያመኝ ነበር:: ሌላው ወንበር ላይ አስቀምጠው በኤሌክትሪክ ሾክድ የሚያደርግ ምርመራ አለ፤ እሱን ተጠቅመውብኛል:: ከሁሉም በላይ “አማራ አህያ” እያሉ የሚሳደቡት ነገር ልቤን ይነካው ነበር::

**ግዮን፡- ማዕከላዊ ከሄድህስ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆየህ?**

**አንዱዓለም**፡- ማዕከላዊ አንድ ወር ላልሞላ ጊዜ ነው የቆየሁት:: እዚያ ስደርስ ሳይቤሪያ አምስት ቁጥር ለብቻዬ ነው የታሰርሁት፤ ዋናውን ምርመራ ደህንነት ቢሮ ውስጥ በቆየሁባቸው አስከፊ ጊዜያት ስለጨረስሁ ማዕከላዊ ስደርስ ለእኔ የፍቺ ያህል ነበር:: እዚያ እጅና እግሬ ተፈትቷል፣ መብራት ከሦስት ወር በኋላ በዓይኔ አየሁ፤ ገላዬን ታጠብሁ፤ በሳምንት አንድ ቀን ለ30 ደቂቃ ቢሆንም ፀሐይ አየሁ፤ የሰው ድምፅ ሰማሁ፤ መርማሪና ተመርማሪ ፊት ለፊት ቁጭ ብለን ማውራት ቻልን፤ እውነት ለመናገር ለእኔ ፍቺ ነው::

በኋላ ከአንዱዓለም አራጌና እስክንድር ነጋ ጋር ስምንት ሰዎች ሆነን የሽብርተኝነት ክስ ተመሰረተብን:: ያው የፍርድ ሂደቱ የታወቀ ነው:: በጊዜው ሽብርተኛ በሚለው ክስ መካተት ቢኖርብን እንኳን እኔና አንድ ዮሐንስ ተረፈ የሚባል ልጅ ነበርን:: እነእስክንድር ግን ፈፅሞ በዚህ ▶

እንቅስቃሴ ውስጥ የሉበትም:: ሠላማዊ ትግል ውስጥ የነበሩ ሰዎች ናቸው:: ግን ሥርዓቱ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚፈልጋቸው በሌሉበትና ባልዋሉበት ጉዳያቸው ከእኛ ጋር እንዲታይ ተደርጓል::

የተመሰረተብኝ ክስ የግንቦት ሠባት የሱዳን ተወካይ የሚል ነው:: እኔ ለስድስት ወር ሚሽን ነው ወደ ሥፍራው የተላክሁት:: በርግጥ የማላፍርበት ከግንቦት ሠባት ጋር ረዥም ርቀት አብሬ ተጉዣለሁ፤ በእኛ ሥራ እነዚህ ወንድሞቼ አብረውን መከሰሳቸው አግባብ አልነበረም:: እኔ ሽብርተኛ አይደለሁም:: ካሸበርኩም መንግሥትን እንጂ ህዝብን አልነበረም:: ግን አሸባሪ ተብዬ በአራት ወንጀል 55 ዓመት አሉና በኋላ 14 ዓመት ፈረዱብኝ::

**ግዮን፡- ወደ ኋላ ልመልስህና፣ ባለቤትህን አሳምነህ ወደትጥቅ ትግል ልትሄድ የነበርህበት ሰዓት ላይ እንዴት ነበር የተሰነባበታችሁት?**

**አንዱዓለም**፡- አሁን ሀገር ውስጥ ባይሆንም ያኔ እዚህ አዲስ አበባ የሚኖርና በግል ሥራ የሚተዳደር በሃይድሮሎጂ የማስተርስ ዲግሪ ያለው ወንድም ነበረኝ:: እሱ ሀሳቤን የማይቃወም ስለሆነ “ቆርጠህ ተነስተህ ከሆነ የእሷን ጉዳይ ለእኔ ተወው፤ የኢኮኖሚ ጉዳይዋን እኔ እሸፍናለሁ፤ አንተ ያዋጣኛል የምትለውን መስመር ተከተል” ሲለኝ ነው በዋናነት ዕዳው የቀለለኝ::

ለመሄድ ከወሰንኩ በኋላ አራት ጊዜ መንገድ ወጥቼ ተመልሻለሁ፤ በአምስተኛው ግን ቆረጥሁ:: ከአንዳርጋቸው ጋር በስልክ ስናወራ “መምጣት የማትችል ከሆነ ሠው እቀይራለሁ” የሚል ትዕዛዝ ሲሰጠኝ ባለቤቴ ትሰማ ነበር:: ያቺ የቁርጥ ቀን እንደማትቀር ስላወቀች በመጨረሻ እሷ ነች የገፋችኝ:: ሌሊት ተነሥቼ ስሄድ ከቤት እንድትወጣ አላደረግሁም፤ ከዚያ በፊት ባሉት አራት ቀናት ተከትላኝ እየወጣች ነው የተመለስሁት:: ስለዚህ የነበረኝ አማራጭ እሷ አልጋ ላይ እንደተኛች ትቶ መሄድ ነው:: እያለቀሰች፣ እያለቀስኩ ነው የወጣሁት:: በዚያ ሰዓት የነበረኝን ስሜት በምንም መንገድ ልገልፀው አልችልም::

**ግዮን፡- አሁን ከተፈታህ በኋላ የመጀመሪያ ልጅህን በጨቅላ ዕድሜዋ ትተሃት የሄድህበትንና የከፈልኸውን መሥዋእትነት በትክክል ተረድታለች?**

**አንዱዓለም**፡- ከመሄዴ በፊት የፓርላማ አባል ስለነበርኩ ከሰዎች ጋር አንዳንድ ነገሮችን ስናወራና ስንከራከር ታዳምጣለች:: አትረዳም ብዬ በእሷ ፊት ብዙ የተናገርኳቸው ነገሮች አሉኝ፤ ያ በእሷ ህሊና ተቀርጿል:: ወደ ትግል ስሄድ የሠባት ዓመት ልጅ ነበረች:: በርግጥ ተይዤ ከመጣሁ በኋላ እስር ቤት በወር አንድ ጊዜ እየመጣች ትጠይቀኝ ነበር፤ ነገሩ በደንብ ገብቷታል፤ አሁን የበለጠ እየተረዳችኝ መጥታለች::

**ግዮን፡- ከሱዳን ከመጣህ ከስንት ጊዜ በኋላ ነበር ቤተሰቦችህን ያገኘሃቸው?**

**አንዱዓለም**፡- ከሦስት ወር በኋላ ማዕከላዊ እያለሁ ነው ለቤተሰቦቼ ስልክ እንድደውልና እንዳገኛቸው የተደረገው:: ባለቤቴን ነፍሰ ጡር ሆና ነው ትቻት የሄድሁት፤ ስትመጣ የአራት ወር ልጅ ይዛ ነው የተገናኘነው:: ከመለያየታችን በላይ እጅግ በጣም የጎዳኝ የዚያ ቀን የነበረው ሁኔታ ነው፤ አንደኛ በፖሊስ ተከብቤ ስለነበረ ሐሳቤን መግለፅ አልቻልሁም:: ሁለተኛ የማላውቃትን አዲስ ልጄን ሳያት እጅግ በጣም ተረብሼያለሁ፤ በአንደበትህ የማትናገረው በዓይን ብቻ ሰርስሮ የሚገባ አይነት ስሜት ነው የተሰማኝ::

በወቅቱ እንዳላለቅስና ስሜቴን እንዳልገልፅ በእነሱ ፊት ሆነብኝ:: ከፍተኛ የፖሊስ አመራሮች ዙሪያዬን ተቀምጠዋል:: በእነሱ ፊት ማልቀስ፣ ስሜቴን መግለፅ አልቻልኩም፤ አፍኜው ነው ወደ ክፍሌ የገባሁት:: በዚያ ወቅት ባለቤቴ ተመላልሳ እንዳትጠይቀኝ ከባድ ጫና ይደርስባት ነበር::

**ግዮን፡- ወደ ወንድሞችህ እንምጣ፤ ከአንድ ቤተሰብ አንተን ጨምሮ አራት ሰው ነው በረሃ የገባው፤ እስኪ ስለዚህ ነገር በዝርዝር አጫውተን?**

**አንዱዓለም**፡- የሚገርመው አባቴ ገና ኢህአዴጎች እንደገቡ ነበር በተለያዩ መድረኮች ይቃወማቸው የነበረው:: ትዝ ይለኛል፤ የጎንደር ከተማ ጄኔሬተር ተነቅሎ ወደትግራይ ሲሄድ ሁለት ቀን ምግብ አልበላም:: እኔ ያኔ አልገባኝም፤ ከእናቴም ጋር ተጋጭቷል:: ጄኔሬተሩ ተነቅሎ ወደ ትግራይ ሲወሰድ ራሱን ስቶ ነበር::

ይህ የአባታችን የነፃነት ስሜት በአጠቃላይ በቤተሰቦቻችን ዘንድ ተፅዕኖ ፈጥሮብናል:: እኔና ታናሽ ወንድሜ መሳፍንት ኤዶፓ መድኅንን የተቀላቀልነው አንድ ቀን ነው:: በኋላ ሁለታችን በሌሎች ወንድሞቻችን ላይ ተፅዕኖ አሳድረናል፤ ስለዚህ ያንዱ ጉዳት ላንዱ እየሆነ ነው ሁላችንም ወደ ፖለቲካ ትግሉ የገባነው::

ወንድሜ ከስዊድን ወደኤርትራ በረሃ የመጣው እኔ በተያዝሁ በስድስት ወሬ ነው፤ እንደሚመጣ ግን አንዳርጋቸው አስቀድሞ ነግሮኛል፤ አስመራ እያለሁ እንደሚመጣ አውቃለሁ:: ከዚያ በኋላ ሌሎች ወንድሞቼንና ዘመዶቼን እሱ ነው የጠራቸው:: ምናልባት ተከታትላችሁ ከሆነ አላውቅም እንጂ በኤርትራና በኢሳት ጣቢያዎች “ከአንድ ቤተሠብ 11 ሠው” የሚል ፕሮግራም ቀርቦ ነበር:: አስራ አንድ ሆነው ከቀረቡት የኛ ቤተሠቦች ሦስቱ ወንድሞቼ ሲሆኑ፣ ሠባቱ ደግሞ የእናቴ የእህትና የወንድም ልጆች ናቸው:: ሁሉም ኤርትራ በረሃ ነው ያሉት:: ቻላቸው አያሌው፣ ንጉሡ አያሌው እና መሳፍንት አያሌው የተባሉትን ሦስት ወንድሞቼን ጨምሮ እኛ ተወልደን ካደግንበት አካባቢ በጣም በርካታ ሰው ነው ትግሉን የተቀላቀለው:: በአንድ ቀን 26 የከተማው ወጣቶች ሄደዋል::

**ግዮን፡- ወደ ትግል ስትሄድ መጀመሪያ ያገኘኸው አንዳርጋቸው ፅጌን ነው፤ ከዚያ መታሠራቸውን እስር ቤት እያለህ ሰምተሃል፤ በመጨረሻም አንዳርጋቸው ተፈትተው አግኝተሃቸዋል:: እነዚህ ሦስቱን ነገሮች እንዴት ትገልፃቸዋለህ?**

**አንዱዓለም**፡- ኤርትራ ጋሉጅ የምትባል ከተማ ላይ ስንገናኝ እኔ ስለአቶ አንዳርጋቸው ብዙ የማውቀው ታሪክ አልነበረኝም:: ግን ሁለት ወር ለሚጠጋ ጊዜ አንድ ክፍል ውስጥ ብቻችንን አብረን ነበር የምናድረው፤ ከአንዳርጋቸው ጋር ለማሣለፍ ያንን ዕድል በማግኘቴ በጣም ዕድለኛ ነኝ:: እንዳገኘሁት ልብሴን ነው ያስወለቀኝ፤ የሲቪል ልብሴንና ጫማዬን አስወልቆ ወታደራዊ አልባሳትን እንድለብስ ትዕዛዝ ሰጠኝ:: ሁለተኛ በሕይወቴ አይቼ የማላውቀው ዲሲፕሊን አጋጥሞኛል:: በሥርዓት የሚኖር፣ ለእያንዳንዷ ደቂቃ ዋጋ የሚሠጥ፣ 24 ሰዓቱን ፕሮግራም አውጥቶ በዚያ የሚመራ ሰው እንደ እሱ በሕይወቴ ዓይቼ አላውቅም::

ለምንም ነገር የማይበገር፤ በምግብ በኩል እንኳን “ወሀከር” የሚባል እንጀራ አለ፤ ላልለመደው ሰው እጅግ በጣም አስቸጋሪ የሆነ ቀይ የማሽላ እንጀራ ነው:: ለሁለት ወር አብሬው ስኖር ከእርሱ ውጭ ሲበላ አላየሁትም:: በጣም ሆድ ያደርቃል፤ ሽንኩርትና ጨው የሌለው ምስር ወጥ ነው ከወታደሩ ጋር አብሮ የሚመገበው:: ይህ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ያሉ ሰዎች በፖለቲካ ንቃተ ህሊናቸው ከፍተኛ እንዲሆኑ ሳይታክት ነው የሚሠራው:: ለሌሎች ሞዴል የሆነ መሪ ነው::

በጣም የሚገርምህ ነገር “አረና” ከሚባለው ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያችን 7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ “አሸገላ” የምትባል አዲስ የምትቋቋም ወታደራዊ ማሠልጠኛ ጣቢያ ነበረች:: በዚያን ወቅት የራሱ መኪና አለው፤ መንገዱ ለመኪና ያመቻል:: ነገር ግን በመኪና ሲሄድ አይቼው አላውቅም:: “ለምንድን ነው መኪና የማትጠቀመው?” ብየ ስጠይቀው “ወታደር ነኝ፤ በእግሬ ነው መሄድ ያለብኝ” ብሎኛል:: ሁሌ ጠዋት በእግሩ ይሄዳል፤ አሥር ሰዓት ይመለሳል:: ያ በረሃ የሙቀት መጠኑ ወደ 44 አካባቢ ነው:: በዚያ ሙቀት በየቀኑ 14 ኪሎ ሜትር መመላለስ እጅግ ከባድ የሕይወት ፈተና ነው:: ለእርሱ ግን ይህ ኢምንት ነው::


ከዚያ ውጪ ሌሎች አመራሮችን የአርበኞች፣ የግንቦት ሠባት፣ የደእሚትና የሲአን አመራሮችንና ሌሎች የፖለቲካ መሪዎችን በፖለቲካው ዘርፍ የተሻለ አመራር እንዲሰጡ ለማድረግ ገፍቶ እነሱን ሰብስቦ ሁልጊዜ ከእነሱ ጋር ሲወያይ ነው የማገኘው:: ሁሌም ሰው ስድስት ሰዓት ላይ ተኝቶ ዘጠኝ ሰዓት ላይ እንዴት ለሥራ ይነቃል? ከዘጠኝ እስከ 12 ሰዓት ሥራ ይሠራል፤ ከ12 እስከ አንድ ሰዓት ቁርስ ይቀማምስና ወደ “አሸገላ” ወታደራዊ ማሠልጠኛ ተቋም በእግሩ ይሄዳል:: እሁድ ቀን ብቻ ከሰዓት ከ8-12 ሰዓት ያርፋል::

አስመራ አብሬው በሄድኩበት ወቅት ከተማዋን ስንዞር መኪና አልተጠቀመም:: አስመራ ከተማ እንኳን ሲዘዋወር በቆንጥር ጫማ ወይንም በፕላስቲክ ጫማ ነው የሚጓዘው:: የኤርትራ ህዝብ በተለይ የአስመራ ከተማ ህዝብ አንዳርጋቸውን በደንብ ያውቀዋል:: ምግብ ቤት ገብተን “ህዝቡ እኛ ሒሳብ እንከፍላለን” ነው የሚለው::

ከእስር እንደወጣ ሳየው ሰውነቱ በጣም ተጐድቷል:: በረሃ ከማውቀው በጣም ከስቶ ተጐሳቁሏል፤ ተጠግቼ ቁጭ ብዬ ሳወራው ደግሞ መንፈሱ ልክ በረሃ ላይ በነበረበት አይነት በጣም የተረጋጋ፣ ያልፈራረሰ ሆኖ አገኘሁት:: አለመፍራቱን ያየሁት አንደኛ ከጠ/ሚ ዐቢይ ጋር ከመገናኘቱ አስቀድሞ ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ሲነጋገር ሰምቻለሁ:: ሁለተኛ የእኔ ወንድም ከበረሃ በስልክ ከ20 ደቂቃ በላይ ከአንዳርጋቸው ጋር ስልክ አውርቷል:: ኡምሃጅር የምትባል ከተማ ላይ ሆኖ ነው ደውሎ ያናገረው፤ ውስጡ ፍርኃት የሌለበት ሰው እንደሆነ አረጋግጫለሁ::

የተደበላለቀ ስሜት ነው የተሠማኝ:: ከእኔ በላይ ባለቤቴን ነው ሲያወራት የነበረው፤ “እስር ቤት ሆኜ ስለአንቺ እጨነቅ ነበር፤ ሕፃኗ አደገች?” ብሎ ነው የጠየቃት:: ሲያዝ ተስፋ የቆረጥኩትን ያህል አሁን ሲፈታ ወኔው፣ የትግል መንፈሱ፣ ቁርጠኝነቱና ጥንካሬው እንዳለ ሆኖ ሳገኘው መጐሳቆሉን ሸፍኖብኛል:: በጣም ደስተኛ ነበርሁኝ::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**



ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

# በሃይማኖት ካባ የዘረኝነት ጾብ

ካዘረኝነት መንስኤዎች ውስጥ የዘር ሐረግ፣ የቆዳ ቀለም፣ የፊት ቅርጽ፣ የአካባቢ ቡድንተኝነት፣ የትውልድ ቦታ እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው:: በጥንት ታሪኩ እንደመነሻ ገንኖ የሚታየው ዘረኝነት ግን ከቆዳ ቀለም ጋር ያለው የዘረኝነት ዓይነት ነው:: ቀድሞውኑ ነጮች በጥቁሮች ላይ ጥቁር ሰው ነፍስ የለውም ከማለት ጀምሮ የቆዳ ቀለም ጥቁረትን እንደእርግማንና እንደአገልጋይነት የሚገልጹባቸው ሥርዓተ ትምህርትና ልዩ ልዩ ጽንሰ ሐሳቦችን ፈጥረዋል፤ በአንጻሩ ደግሞ ነጮች ራሳቸው ነጭ መኾናቸውን ከበረከት ጋር አያይዘው እግዜር እጁን ታጥቦ የሠራው ትውልድ አድርገው ራሳቸውን ለይተውበታል:: እንደ እግዜር ቃል የሚታየው ይህ ጽንሰ ሐሳብ ሐሳዊ ሳይንስ ኾኖ በቅዱሳት መጻሕፍት ተደጋጋሚ ኀትመቶች ሳይቀር ስርዋጽ በመኾን እየተሰነቀረ አንዱን ባርያ ሌላኛውን ጌታ እያደረገ ተንጸባርቋል::

እንደጀርመናዊው ሔግል ላሉት የነጭ የበላይነትን እንዲያቀነቅኑ መሠረት የኾናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ “ከነዓን የተረገመ ይኹን” የሚለው ዕብራውያን ስለጥቁረትና ኢትዮጵያዊነት ያስገቡት ስርዋጽ ነው:: እንደነ ኢብን ሲና ላሉት የአረብ ጸሐፍትም፣ አረብነትን ከእስልምና ጋር ብቻ እንዲያቀነቅኑ ያደረጋቸውና “ኢትዮጵያዊም እንኳን ንጉሥ ኾኖ ቢሾምባችኹ እንኳን ታዘዙት” የሚለው ለዘረኝነት ትርጉም ተጋላጭ የኾነው የቅዱስ ቁርዓን ቃል ነበር:: ቅኝ ገዢዎች እነዚህን ገጸ ንባቦች መሠረት አድርገው አፍሪካውያን በተለይ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን በእርግማን መልካችን እንደጠቆረና ለአገልጋይነት ብቻ እንደተፈጠርን አድርገው ይተርኩልናል::

በጥንት በሳሌሙ ንጉሥ በኢትዮጵያዊው በመልከ ጼዴቅ ዘመን ኢትዮጵያውያንን በመጀመርያ ዕብራውያን በጋብቻ ወረራ ሊያጠፏቸው የሄዱበት መንገድ አልሳካ ሲል በሙሴ ዘመን ሴም፣ ካም፣ ያፌት በሚል ዕብራውያን የዘር ፍልስፍና መሠረቱ:: በኋለኛውም ዘመን የቅኝ ገዢዎች በበርሊኑ ጉባኤ ውሳኔ አፍሪካን ለመቀራመት መሠረት የኾኗቸው በሃይማኖት ስም የሚሰነቀሯቸው እንዲህ ዓይነቶቹ የዘር ልዩነት ገጸ ንባቦች ነበሩ:: ዛሬም ድረስ አውሮፓውያን በስመ ግሪክ ቋንቋ፤ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ፍቺ ሲያስቀምጡ “ፊቱ የጠቆረ” ማለት ነው በሚል ሲተረጉሙት፣ በልባቸው “ከነዓን የተረገመ ነው” የሚለውን ትርጓሜ ለመጠበቅ ነው:: በዚህም ሳይንስ ሊነግሩን ፈልገው ሳይኾን ከፖለቲካዊ ቅኝ ገዢነት በሐሳብ ስላልተላቀቁን መኾኑን ያስረዳል::

እንደጀምስ ብሩስ የታሪክ መዛግብት ምስክርነት ዕብራውያን ከግብጽ ባርነት ሲመለሱ በከነዓን፣እስራኤል የነበሩት ኢትዮጵያውያን ከዕብራውያን ጋር ባደረጉት የወሰን ግጭት በተራራ ላይ ያሉት ሁሉም ከነዓናውያን አማራዎች የሚል ስያሜ አግኝተዋል:: ዕብራውያን በጦርነት ኢትዮጵያውያንን ባለመቻላቸው በየጊዜው ልዩ ልዩ የስድብ ስም ለኢትዮጵያውያን አውጥተዋል:: ለምሳሌ ፈላሻ፣ አክያያ ከሚባል ግራር እንጨት የተገኙ ሕዝቦች፤ ጥቁር አይሁድ፣ ቡዳ፣ ፈላጭ፣ ቆራጭ፣ ፋቂ፣ ቀጥቃጭ፣ ጋፋት እና ጋ* እያሉ የቃለ ስላቅ መጠርያ እንደሰጧቸው ተጽፏል:: ይህ አይነቱ ስመ ስላቅ (Racist Jokes) በተለይም በዘመነ ክርስትና ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ አልፎ አልፎ ብቅ እያለ የዘር መገለጫና የሃይማኖት መታወቅያ እየኾነም ተንጸባርቋል:: በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያውያንን ከውጭ የመጡ መጻተኞች ለማድረግ ብዙ ሳይንሳዊ ሊባል የማይችል የፊት ቅርጽንና ፊክ ኢቲሞሎጂን መሠረት ያደረገ ብዙ የፖለቲካ አሉባልታ አለ::

ለምሳሌ ኢሮብ ማለት እኮ ኢሮፓ ወይም አውሮፓ የሚለው ስመ ተፋልሶ ያመጣው ንባብ መኾኑን የውጭ ምሑራን ጽፈዋል:: ይህም ኢሮቦችንም አውሮፓውያን ናቸው ተብሎ እንዲታሰብ በነጮች የተፈጠረ የፖለቲካ ተረት መኾኑን ግን መዘንጋት የለብንም:: እንደእውነቱ ከኾነ ኢሮብ የሚለው የአከባቢ መጠርያም ኾነ የጎሳ መጠርያ ለስሙ መንስኤ በአንድ ወቅት አውሮፓውያን በእንግድነት ተቀምጠውበት ይኾናል እንጂ፣ ኢሮቦች አውሮፓውያን ናቸው ማለት ከእውነት ያፈነገጠ የነሲብ አነጋገር ነው:: በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን የጎል ሰዎች (ፈረንሳዮች) አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ባደገበት ቤተ አምሐራ ውስጥ በእንግድነት ይመጡ ስለነበረ፤ ቦታው በእነርሱ መጠርያነት ጎል፣ መካነ ጎል፣ ደብረ ግል፣ መሀግል፣ ቀኝ ግል፣ ግራ ግል እና የመሳሰሉትን ዓይነት መጠርያ እያገኘ አከባቢው ተጠርቷል:: ይህ ማለት ግን ቤተ አማራዎች ፈረንሳውያን ነበሩ ለማለት አያስደፍርም::

እንደዚሁ ሁሉ ኢሮቦችም አውሮፓውያን ናቸው ማለት፣ ዛሬ ከአቡነ ጴጥሮስ አደባባይ በስተምዕራብ አቅጣጫ ጣልያን ሰፈር ተብሎ በሚታወቀው አከባቢ ያሉትን ኢትዮጵያውያንንም ጣልያናውያን ናቸው እንደማለት ይቆጠራል:: ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ እንደጻፉት የፈረንጅ ሀገር ሐሳቦችና ተዘዋዋሪዎች ተልእኮአቸው ከፖለቲካ የተለየ ሳይንሳዊ ብቻ እንዳልኾነ ጽፈዋል:: በውጭ ጸሐፍያን ዘንድ እንዲህ እየኾነ የሚጻፈውም የፖለቲካ ተረትና አስመሳይ ስርወ ቃላት በሚሰጡት ድምጸት መሠረት አፍሪካውያንን ለመከፋፈልና የቅኝ ግዛት ክፍል ለማድረግ የሚከወን የፖለቲካ ጥናት ውጤት መኾኑን ለመረዳት የሚሳነው ሰው ያለ አይመስለኝም::

እንደነዚህ ዓይነት የሐሰት ጽንሰ ሐሳቦችን ለማስተናገድ አሜሪካውያን ነጮች በጥቁሮች ላይ የበላይነት የሚያስገኝላቸው የሕገ መንግሥት አንቀጽ ጭምር ነበራቸው፤ እንደ ሕጋቸው አገላለጽ አንድ ነጭ ወደ አንድ ስፍራ ሲገባ፣ አንድ ጥቁር ተቀምጦ ከኾነ ቅድሚያ ለነጩ ወንበር መስጠት እንዳለበት ግዴታው መኾኑን በሕግ ያስገድዳል:: በ1929 ማርቲን ሉተር ኪንግ በተወለደበት ዘመን የአሜሪካ ነጮች ዘረኝነት በዚህ መልኩ ሰማይ ጥግ ደርሶ ነበር:: በ1955 ገደማ አንዲት ጥቁር ሴት በትራንስፖርት ውስጥ ተቀምጣ ሳለ ነጭ ሲገባ ባለመነሣቷና ቦታዋን ለነጭ ባለመልቀቋ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋለች፤ በዕለቱ ወዲያው ግን ሕጉ እንዲቀየር እኩልነት ያለው መከባበር እንዲመጣ ጥቁሮች በኪንግ አስተባባሪነት ሰላማዊ ሰልፍ አድርገዋል:: በዓመቱ በ1956 ሕጉ ፍፁም ተቀየረ:: በአሜሪካም ጥቁሮች ከነጮች እኩል በሕገ መንግሥቱ እንደሰው ተቆጠሩ:::


ይህንን የአሜሪካ ሕገ መንግሥት መሻሻል ተከትሎ በርካታ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሊቃውንትና የእስልምና ምሁራን “ብላክ ቴዎሎጂ” የሚባል የነጮች ዘርን መሰረት ያደረገ የሃይማኖት ትምህርትን የሚያርም ራሱን የቻለ ሥርዓተ ትምህርት እንዲሰጥ አድርገዋል:: በሌላ በኩልም በመጀመርያ ጥቁር ኔግሮ የነበረውን ስምዖን ሐዋርያን ለአገልግሎት እንደጠራው ሁሉ፣ በመጀመርያ አዛን ያለው ጥቁሩ ኢትዮጵያዊ ቢላል ከነቢዩ ጋር ከፍተኛ ቀረቤታ እንደነበረው መጻፉ ፈጣሪ ጥቁረትን እንደእርግማን እንደማይቆጥረው ማሳያ እየኾነ በብላክ ቴዎሎጂ መሠጠቱ ቀጥሏል:: ይህንን እውነት የተረዳው ማልኮም ኤክስ የተባለው የፀረ ዘረኝነት ንቅናቄ ታጋይ ለዚህ ትግል ዘርን ያላማከለው አስተሳሰብ እስልምና ነው በሚል ወደ እስልምና ቀድሞ ተመልሷል:: እርሱም በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ በፀረ-ዘረኝነት ትግል ከማርቲን ሉተር ኪንግ እኩል ከፍተኛ እንቅስቃሴ አካሂዷል:: ትሬቮር ሁድሌስቶን የተባለ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊ የኾነው የለንደን ቄስ፣ በደቡብ አፍሪካ ይካሄድ የነበረውን የነጭ የበላይነት በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ተጋፍቷል:: ሃይማኖትን ከብሔር ጋር የማያያዙ ስብከት ሰማያዊ ያልኾነ ምድራዊ መኾኑን አሳይቷል:: በታላቁ መጽሐፍ እንደተገለጸው ሃይማኖታቸውን ከዘራቸው ጋር ከማስተሳሰራቸው የተነሣ አይሁዳውያንና ሳምራውያን የአምልኮ መልክ እንጂ ሃይማኖት እንዳልነበራቸው ተገስጸዋል:: ምክንያቱም ሳምራዊ ሰው በመንገድ አደጋ ቢደርስበት ሳምራዊ ካልኾነ በስተቀር የሚደርስለት የለም፤ ካህናት ሳይቀሩ በዘር የተተበተቡ ስለኾኑ፣ ከዚህ አጸያፊ የዘር ▶

◀መድልዎ ውስጥ መግባታቸውን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሳምራዊው ሰው ምሳሌ ውስጥ የነበረውን አንድ ዘረኛ የሃይማኖት መሪ ጠቅሶ አስተምሯል::


እንደአሮን በዘር ሳይኾን እንደመልከ ጼዴቅ በመሐላ የመጣ የክህነት መንበር ላይ ተቀምጠናል የሚሉ የሃይማኖት መሪዎች አሉን፤ ነገር ግን መንፈሳዊነት የጎደለው ኑሮአቸውን ስንገነዘብ ከዘረኝነት የመነጨ የሃይማኖት ጥገኝነት ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ሰልፈኞች መኾናቸውን ኑሮአቸው ያሳብቅባቸዋል:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር፣ በአሜሪካ ያለው ሲኖዶስና በኢትዮጵያ ያለው ሲኖዶስ ሽኩቻና መወጋገዝ መሠረቱ ዘረኝነት እንጂ ሃይማኖት አለመኾኑን መንግሥትም ቢኾን ማረጋገጡን ሰምተናል:: እውነትም መሠረቱ ዘረኝነት ከኾነ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሀገር ሰላምና ደኅንነት ሲል በሀገረ አሜሪካ ያሉትን ፓትርያርክ ወደሀገራቸው አምጥቶ በአዲስ አበባ ካሉት ፓትርያርክ ጋር፣ ወደዱም ጠሉም ሁለቱም ፓትርያርኮች በአንድ ወንበር ላይ እንደተሰየሙት እንደሊቃነ ካሕናቱ ሐናና ቀያፋ ሊያገለግሉ የሚችሉበትን ኹኔታ ሊያመቻች ይገባል:: የሁለቱ ሲኖዶሳት ፈቃድ ኖረም አልኖረም ይህ ከመንግሥት የሚጠበቅ ሕገ መንግሥታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሕግ ነው:: ለመረጃ ያህል ማወቅ ካስፈለገ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው ክርስቶስ በተሰቀለበት በ33 ዓ.ም. ሊቀ ካህናት ሐና በፖለቲካ አመለካከቱ በ15 ዓመቱ ከሥልጣኑ ተሽሮ በምትኩ ቀያፋ የተባለው ሊቀ ካህናት ኾኖ ተሾሞበት ነበር፤ ይሁን እንጂ ሊቀ ካህናቱ ሐና በቄሳር ቢሻርም በሕዝቡ ዘንድ ያልተሻረ በመኾኑ በክህነቱ ሕዝቡን ማገልገሉን ቀጥሎ ነበር፤ በዚሁ ልክና አምሳል የኢትዮጵያ 4ኛው ፓትርያርክ አባ መርቆርዮስም በነበረው የመንግሥት ለውጥና የፖለቲካ ትኩሳት ባቀረቡት ማመልከቻ መሠረት ከፐትርክናቸው ለቀዋል ቢባልም በሚከተሏቸው ምዕመናን ዘንድና ባሏቸው የሲኖዶስ አባላት ፐትርክናቸው የጸና ኾኖ በአሜሪካ ሲኖዶሳቸውንና ሕዝባቸውን እየመሩ ይገኛሉ:: ስለዚህ ከዘረኝነት ጋር የተያያዘው ክፍተት የመንግሥት ዋስትናና ይሁንታን አግኝቶ እኚህ አባት ወደኢትዮጵያ መጥተው በመንበራቸው ተሰይመው በአዲስ አበባ ካሉት ፓትርያርክ ጋር በጋራ የቤተ ክህነቱን አስተዳደርና መዋቅር ተረክበው እንዳይሠሩ የሚያደርጋቸው ሕግ የለም:: ጉዳዩ የዘረኝነት መኾኑ ከታመነም በአሜሪካ ያሉት ፓትርያርክ ከዚህም በላይ ሊኖራቸው የሚችል መብት ይኖራቸው ይኾናል:: ከመንግሥት ዋስትናና ይቅርታ ማግኘት እንጂ የሲኖዶስ መታረቅ አለመታረቅ አጀንዳ ሊኾን የሚችልበት ሁኔታ የጠበበ ይመስላል::

ይቅርታ ባልሰፈነበት ኹኔታ ዘርን መሠረት ያደረገ የሃይማኖት እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይኾን በጊዜ ሂደት ሀገራችንን ኢትዮጵያንም በዘመነ መሳፍንት እንደኾነው አንድነቷን ያናጋዋል:: በዘመነ መሳፍንት ከወንዜው ሰውና አስተሳሰብ ጋር ሃይማኖትን አቀናጅተው እያዛመዱ ፀጋ የጎንደር፤ ቅባት የጎጃም፤ ካራ የትግራይ ሃይማኖት መገለጫ እንዲሆን የተሠራው ሥራ የፖለቲካ ዓላማ እንጂ ፍጹም ከዘር ሐረግና ከትውልድ ሥፍራ ጋር የሚገናኝ ኾኖ አልነበረም::

ከሃይማኖት በስተጀርባ ያለው ዘረኝነት ሀገር እንደሚያፈርስ ከአይሁድ ታሪክም መገንዘብ ይቻላል:: ዘረኝነትን ለጀመሩት በኤቦር ዕብራውያን ለተባሉትም ለአይሁድ እንኳን ዘረኝነት አልጠቀማቸውም፤ እነሱም



ብፁዕ አቡነ ማትያስ



ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ

በተራቸው በግብጻውያን የበላይነት ወድቀዋል፤ በረሃብና በድርቅ ተቀጥተዋል:: በየሀገሩ እየተበተኑ አሰቃቂ መከራዎችን ሲያስተናግዱ ኖረዋል:: እግዚአብሔር አብረው ከሚኖሯቸው የሌላ ብሔረሰቦች ሰዎች ጋር ግጭት እንዳያደርጉ የሚከተለውን ማስጠንቀቅያ በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ተናግሯል::

"በሀገራችሁ ውስጥ ከእናንተ ጋር እንግዳ ቢቀመጥ ግፍ አታድርጉበት:: እናንተ በግብፅ ምድር እንግዶች ነበራችሁና ከእናንተ ጋር የሚቀመጥ እንግዳ እንደ አገር ልጅ ይሁንላችሁ፥ እርሱንም እንደ ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ::"

ዕብራውያን ግን ይህንን መመርያ ስለጣሱት፣ መከራ ላይ ወደቁ፤ መጻተኞች ኾነው በሰው ሀገር እንዳልኖሩ የአዳም ዘር መኾናቸውን ክደው በየነገዳቸው ተከፋፈሉ:: በተለይም በጎረቤታቻቸው በፍልስጥኤማውያን 40 ዘመን የተገዙት በዘርና በነገዳቸው ተቧድነው በመመካታቸው ነበር:: ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸውን መለኮታዊ መመርያ በሀገራችን ተዛማጅ ሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ ልናገኝለት እንችላለን:: በሕገ መንግሥት ደረጃም ኢትዮጵያውያንን ኹሉ ይመለከታል:: እንደ መንፈሳዊነት ሃይማኖተኞች እንኳን ያገራቸውን ሰው ቀርቶ የሌላም ሀገር ሰው ወደ ሀገራቸውና ወደ ቤታቸው ቢመጣ እንደራሳቸው አድርገው መቀበል እንደሚገባቸው መንፈሳዊውም ዓለማዊውም ሕግ ያስገነዝባል:: ይህም ባለፉት ሳምንታት ውስጥ በሀገራችን ኢትዮጵያ በደቡብ ልዩ ልዩ ከተሞች የተደረገው የዘር ለዘር ግጭት መሠረቱ ምድራዊውንም ሰማያዊውንም ሕግ ካለመገንዘብ የመነጨ ዕብራውያን እንደሄዱበት ያለ ስሜታዊ እርምጃ መኾኑን ያሳየናል::

"ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?" የሚለው መለኮታዊ አገላለጽ በአንድ ነብር ላይ ያለው ዥንጉርጉርነት በአንዲት ኢትዮጵያ የሚንጸባረቅ መኾኑን የሚያስረግጥ ነው:: በኢትዮጵያዊነት ውስጥ ያሉት ልዩ ልዩ መልኮችና በኢትዮጵያ ያለው ብዝኃነት ተፈጥሮአዊ እንጂ ከጊዜ በኋላ በጥናት የተገኘ የቅኝ ገዢዎች በረከት አለመኾኑን ያሳየናል:: በሀገራችን ዘረኝነትና የሃይማኖት አክራሪነት ጥምረት ፈጥረው የኢትዮጵያዊነትን መልክ ከተፈጥሮአዊ ገጽታው ጋር አቃርነውታል:: አንድን ሃይማኖት ከአንድ ብሔር ጋር ያለምንም መንፈሳዊና ዓለማዊ አመክንዮ በግድ የማጣበቅ ክፉ የዘረኝነት አባዜ፤ "ከእኔ ሌላ ምድሪቱ መቀበል፣ ዜጎቿም መከተል የለባቸውም" የሚል የከረረ ሃይማኖተኝነት ህብረት ፈጥረው ሀገራችን እና ህዝባችን ላይ በርካታ ጉዳቶችን አድርሰዋል:: የሩቅ ዘመኖቹ

የዮዲት ጥፋት፣ የግራኝ ውድመት እንዲሁም የቅርብ ጊዜዎቹ የደርቡሽ እና የጣልያን ከሰብአዊነት መንጠፍ ጋር የተያያዙ አሰቃቂ ግፎች ለእዚህ ማሳያ ናቸው:: የእኛ ዘመኖቹ የዘረኝነትና የሃይማኖት አክራሪነት ጥፋቶች ከጥንቱ በሥጋ መገለጥን (ሰውን ማረድ፣ ቤተ እምነቶችን ማቃጠል … ወ.ዘ.ተ.) ተበድረው፤ ከዘመኑ ሳይንስ ደግሞ የሥነ ልቡናን ጫናና ጦርነት በመውሰድና በመቀየጥ የረቀቀ ጥፋትን እያደረሱ ይገኛሉ::

የዘረኝነትና የሃይማኖት አክራሪነት በጥምረት ከፈጠሯቸውና ከሃይማኖት መሠረታዊ ሕጎች ጋር ተጻራሪ ከሆኑት ተግባራት /paradoxical elements of religion/ አንዱ የሃይማኖት ተቋማት በከፍተኛ ሌብነት ውስጥ መዘፈቅ ነው:: ከሃይማታኖታዊ ዘረኝነቱ ጀርባ ሌብነት፤ ከሃይማኖታዊ አክራሪነቱም ባሻገር ደምን፣ የዘር ሐረግን፣ የቆዳ ቀለምን መሠረት ያደረጉ ማሸማቀቆች የትየለሌ ናቸው:: በርካቶች በሚከተሉት ሃይማኖት የተነሣ ከሌሎች ሃይማኖቶች የተለያዩ አሰቃቂ ግፎችን እንደተቀበሉ ሁሉ፣ የራሳቸው ሃይማኖት ውስጥ ካሉት ሰዎች (መሪዎች) በብሔር ማንነታቸው መነሻነት የዘረኝነት ሰለባ የሆኑም ጥቂት አይደሉም::

በሃይማኖት ካባ ውስጥ ያለው የዘረኝነት ደባ መልኩ ብዙ ነው:: ከተራ ማሸማቀቅ ጀምሮ በምድር ላይ መኖርን እስከአለመፍቀድ ይደርሳል:: ይህ ተግባር በበርካታ ሃይማኖቶች ላይ በጉልህ ቢታይም በተለይ ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ በጉልህ ይታያል:: ወደድንም ጠላንም፣ ቢዋጥልንም ባይዋጥልንም በሃይማኖት ካባ ውስጥ ያለው የዘረኝነት ደባ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለሁለት ከፍሏታል፤ በርካቶችን አሰድዷል፤ የሃይማኖት አባቶችን ሌብነት ውስጥ ከቷል፤ ቤተ ክህነቱን ወደሽቃጭነት አውርዶታል፤ ምእመኑን በነጣቂ ተኩላዎች አስበልቷል፤ ክብር ለሚገባቸው ውርደትን፣ ለሊቆቻችን ትንሽነትን ከፍሏል::

ህልም አለኝ - ነገ በተፈጥሮአዊ ብዝኃነታችን ውስጥ ያለውን ዥንጉርጉርነታችንን መነሻ አድርገን "ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን አይለውጥም" እንላለን!

ህልም አለኝ - ነገ ያለሃይማኖት ዘረኝነትና ያለሃይማኖት አክራሪነት እጅ ለእጅ ተያይዘን "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ተዘረጋለች" ብለን በጋራ እንዘምራለን!

ህልም አለኝ - ነገ እንደሀገሬ ልጅ ዮቶር ለዓለም ፍትሕንና አድልዎ - አልባ አመራርን እናስተምራለን! ይቆየን …

"…ኵሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንዑ…"
ገለቶማ !!

ወቅታዊ

# የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

**የኢ.ፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ "ሕዝበ ሙስሊሙ የሚያነሳቸውን ማንኛውንም ጥያቄዎች ለመመለስ ከምንጊዜውም በላይ ዝግጁ ነን" በማለት ያስተላለፉትን ጥሪ አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ምላሽ ሰጥቷል።**


ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ


ኡስታዝ አሕመድ ሙስጠፋ


ኡስታዝ አህመዲን ጀበል

ቀን፣ ሰኔ 10/2010

ለክቡር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ
የኢ/ፌ/ዴ/ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ለህዝበ ሙስሊሙ ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ተነሳሽነትዎን ይመለከታል፡፡

የተከበሩ ጠ/ ሚኒስትር፣

በሰኔ 8/2010 በዒድ አልፈጥር በዓል እለት በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግለጫ መስጠትዎ ይታወቃል፡፡ በመግለጫዎ ለወቅታዊ የሀገራችን ፖለቲካዊ ትኩሳቶች እልባት ለመስጠት እንደሚሠሩ እና በተለይም የህዝበ ሙስሊሙን ማንኛውንም ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ መሆንዎን መግለፅዎ በህዝበ ሙስሊሙ ውስጥ አዲስ ተስፋ የፈጠረ አጋጣሚ ሆኗል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ላለፉት ዓመታት መንግሥት ከሁሉም ሃይማኖቶች በእኩል ርቀት ነፃ እና ፍትሐዊ በሆነ አግባብ መቆም ሲገባው በሙስሊሙ ተቋማት እና የእምነት ጉዳዮች ውስጥ በግልፅ ጣልቃ በመግባቱ የተነሣ የመነጩ የመብት ጥሰቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመቃወም እና ለመታገል አደባባይ ከወጣን ስድስት ዓመታት ተቆጠሩ፡፡ በሙሉ የሀገራዊ ሓላፊነት ስሜት እና ኢትዮጵያ ሀገራችን የሁሉም እምነቶችና ሃይማኖቶች መብቶች የተከበሩባት ሆና ማየትን በማለም ያደረግነው ሰላማዊ ትግል እነሆ ለመሰል ትግሎች በር ከፍቶ የለውጥ ቀንዲል መሆን ቢችልም ህዝበ ሙስሊሙን ግን ያለ ስሙ ስም ያለ ግብሩም የከፋ ስቃይ እና መከራ እንዲደርስበት አድርጓል፡፡

እነዚያ ዓመታት አልፈው በሀገሪቱ ፈጣን የሆኑ የፖለቲካ ለውጦች ቢስተናገዱም ያነሣነው ጥያቄ መልስ ሊያገኝ እንደሚችል የሚጠቁም የአመለካከትም ሆነ የተግባር ፍንጭ ማየት ሳንችል እስካለፈው የረመዳን ፍቺ በዓል ድረስ ቆይተናል፡፡

ክቡር ጠ/ ሚኒስትር፣

መንግሥትዎ እና ያዋቀሩት ካቢኔ በዓይነቱ የተለየ፣ ለሀገራችን ታሪክና ለህዝባችንም ክብር የሚመጥን ምክንያታዊ ፖለቲካ ማራመድ በመጀመራችሁ መንግሥትዎ ሰፊ ተቀባይነትን ማግኘት ችሏል፡፡ የዚህ ቅቡልነት ምንጩን ጠለቅ ብለን ስንፈትሸው በዋናነት የምናገኘው ለህዝቦች ማንነት፣ ሀገራዊ ድርሻ እና ሓላፊነት በሚመጥን መልኩ ከላይ ከአመራሩ የታየው የአመለካከት ለውጥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ክቡር ጠ/ሚኒስትር፣

ከላይ በተጠቀሰው መግለጫዎ የህዝበ ሙስሊሙን ማንኛውንም ጥያቄዎች ለመፍታት ያለዎትን ዝግጁነት መግለፅዎን በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች በመልካምነት ተቀብለነዋል፡፡ በመጀመሪያ ለዓመታት በፅናት እንደህዝብ ዋጋ ስንከፍልለት የኖርነው ጥያቄ ደጋግመን እንደምንለው ያልተመለሰ ጥያቄ መሆኑ ዕውቅና መቸሩ ነው፡፡ የጥያቄያችን አለመመለስ ሳያንስ፣ ጥያቄያችን ተቀልብሶ የሚዲያ ፕሮፓጋንዳ እና የኃይል እርምጃ ሰለባ ተደርገን ከመቆየታችን አንፃር ላልተመለሰው ጥያቄያችን እልባት ለመስጠት የመጀመሪያው እርከን የሆነውን "ህዝብ ያልተመለሰለት ጥያቄ አለው" ብሎ የሚነሣን መሪ ዕውቅና ስንሰጥ ችግሩን በሚገባ የተረዳ መሪ ለመፍትሔውም ቁርጠኛ እንደሚሆን ስለምናምን ነው፡፡

ተነሳሽነትዎን በበጎ የወሰድንበት ሁለተኛው ምክንያት፣ ችግሩን ከሥሩ የመፍታት አቅም እንዳለዎ በማመን እና በመግለጫዎም ይህንኑ በመጠቆምዎ ነው፡፡ በሁለት ወራት የሥልጣን ላይ ቆይታዎ እዚህም እዚያም ለሚነሡ ጥያቄዎች እሳት የማጥፋት ሥራ ሳይሆን፣ እንደመንግሥት ለህዝብ ጥያቄ ሊኖር የሚገባውን አመለካከት ሥር ነቀል በሆነ መልኩ በመቀየርዎ ችግሮቹ በአፈፃፀም ደረጃ በቀላሉ የሚፈቱበት አየር እየተፈጠረ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ላነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ያልቻለው የመሪ ድርጅቱ (መጅሊስ) መዋቅር ውስብስብ ሆኖ ሣይሆን መንግሥት በጉዳዩ ላይ የያዘው አሉታዊ አቋም በመኖሩ ነበር፡፡

በመሆኑም መንግሥትዎ ማንኛውንም ችግር በመወያየት ለመፍታት ዝግጁ መሆኑን በሚዲያ ማሳወቁ ቀጣዩ ሂደት አተገባበር እንደሚሆን ይታመናል፡፡ የአሁኑን መግለጫ እንደከዚህ ቀደሞቹ ጊዜያዊ የፖለቲካ ግለት ማብረጃ ሳይሆን ወደመሬት ወርዶ የሚተገበር እንደሚሆን እናምናለን፡፡ በዚህም ምክንያት አተገባበሩ ለጥያቄዎቹ መሠረታዊነት፣ ህዝቡ ካደረገው ሰላማዊ ትግል እና መንግሥትም ለህዝብ ፍትሐዊ ጥያቄዎች ከሚሰጠው ዋጋና ክብደት አንፃር ተመጣጣኝ በሆነ ሂደት እና ጥልቀት እንዲከናወን እንፈልጋለን፤ አጥብቀንም እንጠይቃለን፡፡ ችግሮቹ በሙሉ የመንግሥትን ትኩረት በሚያመላክትና የባለመብቶቹን ሥነ ልቦና ሊያረካ በሚችል መልኩ ይፈቱ ዘንድ የበኩላችንን ለማበርከት በህዝበ ሙስሊሙ ተወክሎ ሲንቀሳቀስ እንደነበረ የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ ዝግጁነታችንን ስንገልፅ፣ የጥያቄዎቹ መመለስ እና የሚመለሱበት መንገድ መሠረታዊ በሆነ መልኩ የተሣሠሩ እንደሆኑ በማስታወስ ጭምር ነው፡፡ ይህንን የምንለው ለችግሩ የሚሰጠው መፍትሔ ዘለቄታዊነቱ አስተማማኝ የሚሆነው የጉዳዩን ባለቤት እና ግንባር ቀደም ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በሚደረግ ቀጥተኛ ውይይት በመሆኑ ነው፡፡

በመጨረሻም በሀገራችን ላይ አንዣቦ ከነበረው አስፈሪ አደጋ በተወሰነ ደረጃ እያገገምን ባለንበት በዚህ ወቅት የለውጥ ሂደቱን የሚያደናቅፉ ክስተቶች እዚህም እዚያም እየተስተዋሉ በመሆኑ ህዝበ ሙስሊሙ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን "ለመንግሥትዎ" ሁለንተናዊ ድጋፉን እንደሚቀጥል ልናረጋግጥ እንወዳለን፡፡

ለህዝቦች ጥያቄ መልስ የመስጠት ሂደት ውስጥ እንድንገባ ላደረገን አላህ ምስጋና እያቀረብን እየተወሰዱ ላሉ ፖለቲካዊ እርምጃዎች አክብሮታችንን ለመግለፅ እንሻለን፡፡ መንግሥታዊ ብልሹ አስተሳሰብና አሠራር የፈጠራቸውን ችግሮች በመንግሥታዊ እና ህዝባዊ ወገንተኝነት ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ከራሳችንም ሆነ ከሌሎች የሀገራችን ህዝቦች ጋር በመሆን ለስኬታማነቱ የበኩላችንን እንደምንወጣ እየገለፅን ለሀገራችን እና ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን መልካሙን ሁሉ እንመኛለን፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያን አላህ የሰላም፣ የፍትሕ፣ የነፃነትና የብልፅግና ሀገር ያድርግልን! አሚን፡፡

የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ

Flintstone Homes for you®

# Leading by example




**Address:**

Call: +251 910 903 131/2
Click: www.flintstonehomes.com
Addis Ababa,Ethiopia